ትሸሻለች። ፀሐይና ታምራት የግላቸውን ወሬ እያወሩ ነፃነታቸውን ለመስጠት ቢሞከሩም የሆነው ይኸው ብቻ ነበር።

ትሩፋት ከአባቷ እየተደበቀች  ወደ ፀሐይ ቤት እየሄደች ከፍቅሩ ጋር አንድ ሳምንት አብረው አሳለፉ፡፡ በዚህ አንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ በፍቅሩ ልብ ውስጥ ፍቅር ከድሮው መቶ እጥፍ አድጎና ድርጅቶ መሰረቱን ጥሎ ግንቡን ገነባ። ወደ ባህርዳር ሲመለስ ከመቼውም ጊዜ በላይ ትሩፋት በደም ሰሩ ገብታ ከደሙ ጋር እየፈሰሰች በሰራ አካላቱ ተሰራጭታ  ነበር።





## ጻአዳ አስመራ

የመምህራን ኮርሱን ወስደው ካለፉት ተማሪዎች አንዷ ትሩፋት ሆነች፡፡ አሰመራ መምህራን ተቋም፡፡ የትምህርት ማስረጃዋን አሟልታ ስትወለድ ያኔ እንደ መከሯት ሁሉ የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር አቶ አስረስ ትምህርቷን እንዲህ በአጭሩ ቀጭታ እዚህ ኮርስ በመግባቷ ወቅሰዋታል፡፡ ባለማወቅ የልጅ ሥራ እንደ ሰራች በመቁጠር ገስጸዋታል፡፡ ለወደፊቱም ቢሆን ከፍተኛ ትምህርት ለመማር ፍላጎቱ ካላትና ከተጋች አድሉ እንዳላት እጥብቀው መክረዋታል፡፡ መንገድ መንገዱን ጠቁመዋታል፡፡

ትሩፋት ለመጀመሪያ ጊዜ ከቤተሰቧ ተለይታ እርቃ  መሄዷ እርግጥ ሆነ፡፡ ምንም ቢሆን አንድም ሁነኛ ዘመድ በሌለበት የማታውቀው አገር መሆኑ ሆዷን ማሸበሩ አልቀረም፡፡ ነገር ግን መጽናኛ አላት፡፡ በእርግጠኝነት እንደ ተመረቀች ወድያውኑ ሥራ ይኖራታል፡፡ ታናናሾቿን እየረዳች ለማስተማር ጊዜው እየቀረበ ነው፡፡ ይህን ሰታሰብ ውስጧን ይህ ነው የማትለው ደስታ ይሰማታል፡፡

«ለዚች ልጅ ሰንቅ የሚሆን ዳቦቆሎ ነገር አዘጋጅላት እንጂ መቼስ ከሰው አገር ባዶ እጇን አትኸድ ነገር  እኔም እዚያው አድርሻት እመጣለሁ ብዬ ቁቤ  ገብቼ  የመጀመሪያውን እጣ ውሰጃለሁ።» አሉ አቶ ማንያዘዋል  ፈራ ተባ እያሉ፡፡

«ደሞ እንደ ለመዱት እዳ ውሰጥ ሊዘፍቁን ማለት ነው? የቁቤ መጀመርያ መሆን እዳውን ሲገፈግፉ መኖር ነው» አሉ ሚስት ቆጣ ብለው፡፡

«ዛዲያ የደረሰች ልጅ ዝም ብለህ መዳረሻዋን ሳታይ አግድመህ ልቀቃት ነው የምትይኝ!? መንገድ ላይም አዳር አለው እኮ! ኋላ አንድ ነገር ቢገጥማት ፀፀቱን እችለው ይመስልሻል? ይልቅስ የወሰድኩትን የቁቤ ብር እንደሚሆን እንደሚሆን እናደርገዋለን። ከሰሞኑ ደሞ ደመወዝ ይጨመራል እየተባለ ሰለሆነ አትጨነቂ» አሉ፡፡ ሚስት ነገሩ ባይጥማቸውም አልጎሞጉመው ዝም አሉ፡፡ የደረሰች ሴት ልጅ ብቻዋን በማታውቀው አገር ትሂድ ማለቱ ከብዷቸው፡፡

ትሩፋትና አባቷ ወደ አስመራ  ለመሄድ ትኬት የቆረጡት ጎንደር ከተማ ነው። ከተማዋን ለማየት ብትጓጓም እድሉን ግን አላገኘችም፡፡ ከባህርዳር የተነሳውን የመጨረሻ አውቶብስ ይዘው የገቡት ከመሸ ነበር።  ወደ አሰመራ የሚሄደው ዋልያ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብስ በጧት ነው  ጎንደር ከተማን የለቀቀው፡፡

ወጣ ገባና ጠመዝማዛ የበዛበት የጎንደር-- አሰመራ መንገድ አላሰለቻትም። ተፈጥሮን እያደነቀች ከአባቷ ጋር ሰትጓዝ። የሊማሊሞ ተራራን ከሩቁ ስትመለከተው ግን እንደ ቀለበት ዞሮ የገጠመ የሚመስለውን  ዙሪያ ጥምጥም መንገድ-- መኪናው በሰላም ወጥቶ

ለመጨረሱ ኦርግጠኛ አልነበረችም። ፍርሀት ገብቷት ልቧ ናድ ናድ ማለት ጀምራ ነበር። ከጎኗ የተቀመጡትን አባቷን ቀና ብላ አየቻቸው። በራሳቸው ዓለም ጭልጥ ብለው ጠፍተዋል:: ተራራውን ቀና ብለው ሲመለከቱት ከላይ ሊወድቅ የተንጠለጠለ ናዳ መስሎ ዐይን ላይ ይጋረጣል:: ወደ ታች ሲመለከቱ ደግሞ ገደሉ አፉን በሰፊው ከፍቶ የሚውጥ ይመስላል:: አውቶብሱ ተራራውን የሚዞረው እንጂ የሚሄድ አይመስልም:: መጨረሻ ላይ ግን መንገዱን ጨርሶ ወጥቶ በሰላም ረባዳው ላይ ደረሰ:: ቀዝቀዝ ያለው ነፋሻማ አየር ተቀበላቸው:: ከጭንቀታቸው የተነሳ ለታቦት የተሳሉ ሰዎችም እንደ ነበሩ ከወጡ በኋላ ሲያወሩ ትሩፋት ሰምታቻዋለች::

አውቶብሱ አስመራ ከተማ የገባው በሁለተኛ ቀኑ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ ነበር:: ትሩፋትና አባቷ መናኸሪያው አካባቢ አንድ አነስተኛ ሆቴል ውስጥ አልጋ ይዘው አደሩ:: በነጋታው አቶ ማንያዘዋል የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋሙን ለማግኘት አድራሻውን ሰው መጠየቅ ነበረባቸው:: የሆቴሉን አስተናጋጅ ጠየቋት:: አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋዋ መሆኑ ቢያስታውቅባትም አቀላጥፋ ትናገራለች:: እንዲገባቸው አድርጋ አመላከተቻቸው:: ዋና ምልክት አድርጋ የነገረቻቸው ሳባ ሲታድየምን ነበር:: ብዙ ሳይንገላቱ ተቋሙን አገኙት:: ትሩፋት የያዘችውን የትምህርት ማስረጃ አቅርባ ምዝገባዋን አጠናቀቀች:: አቶ ማንያዝዋን ተቋሙ ውስጥ ለአገኙት ሰው ሁሉ ልጃቸውን አደራ ሰጥተው ልባቸው ወደ ኋላ እየተጎተተ ግቢውን ለቀው ወጡ::

አስመራ ውብ ከተማ ናት። መንገዶቿ-- ቤቶቿ ሁሉ ጥሩ መሀንዲስ የቀየሳቸው ያያት ሁሉ የሚመሰክርላት-- እንደ ፈንድሻ ፍንድቅድቅ ያለች ቅልብጭ ያለች ከተማ። የመንገዱን ጠርዝ ተከትለው የተተከሉት ዘንባባዎች ሳይቀር ደስ ይላሉ። በተለይ በምሽት ኮምፐሽታቶ የገባ ሰው እንዲህ በቀላሉ አይወጣም። ቆነጃጅቱ አፍንጫን በሚያውደው ሽቷቸው የሰው ቀልብ ይሰርቃሉ። በዘንባባዎች መሀል በሚፈሰው የኤሌክትሪክ ብርሃን ሲታዩ እንደ ፈርጥ የሚንቦገቦገው ዐይናቸው የሁሉንም ወንድ ልብ ያማልላል:: የሚገርመው ደግሞ አንደኛዋን ከሌላዋ መለየት እስኪሳን ድረስ ሁሉም ውቦች ናቸው::

ትሩፋት አስመራን የመሰለ ከተማ ስታይ የመጀመሪያዋ ነው። የምታውቃቸው አዲስ ዘመንና ደብረታቦር ከከተማነት ይልቅ ገጠራማነታቸው ያይላል:: ለመምህራን ኮርስ ሰልጠና አስመራ መምህራን ተቋም ባትመደብ ኖሮ ምን እልባት ለዘላለሙ አታያትም ነበር። የህፃዎቿን አሰራርና የከተማዋን ጽዳት አድንቃለች። ከተመረቀች በኋላ መኖሪያዋ አስመራ ከተማ እንድትሆን ሁሉ ተመኝታለች።

የአስመራ መምህራን ተቋም ሴት ሰልጣኞችን የኪስ ገንዘብ እየሰጠ በተመላላሽ እንዲማሩ ያደርጋል። አስካለ፣ አዚዛ፣ ትርሀስ፣ ሰላማዊትና ሴንሳ ከሚባሉ ልጆች ጋር ተዳብላ ኑሮን በአስመራ ከተማ አንድ አለች:: ሁሉም አይተዋወቁም:: አዚያው ተቋሙ ውስጥ ነው የተገናኙት:: የገንዘብ አቅማቸው የሚመጣጣን በመሆኑ ድንገት ተሰባሰበው ቤት





ለመከራየት ጊዜ አልወሰደባቸውም:: እንዳጋጣሚ ሰላማዊት ከምትባለዋ ጋር ደግሞ ክፍልም አንድ ላይ ተመደቡ:: ግንኙነታቸው ከሌሎቹ ይልቅ ጠበቅ ያለ ሆነ:: አንድ ማለዳ

«እናቴ ከእናትነቷ በላይ በጣም ታሳዝነኛለች:: አለች ሰላማዊት ጉርድርድ ያለውን ቀይ ፊቷን ከፍት አድርጋ::

«አንቺ ብቻ አይደለሽም ሰላምየ ሁሉም ሰው እናቱን በጣም ስለሚወድ ለእናቱ ያዝናል» አለች ትሩፋት::

«የእኛ እናት ግን ከሌሎቹ እናቶች ሁሉ ለየት የምትል ይመስለኛል:: ያለ አባት ስላሳደገችን ሳይሆን አይቀርም::»

«እናትና አባታችሁ ተለያይተውባችሁ ነው?» ጠየቀች ትሩፋት ሰላማዊትን ሽቅብ እየተመለከተች::

«አይደለም፤ አልተለያዩም:: አባቴ የሐረር ከተማ የመሀል ዳኛ ነበር:: በሕዝብ የተወደደ እንደ ነበርም ይወራል:: እናታችን እንደ ነገረችን ከሆነ በንጉሡ አስተዳደር አይደሰትም ነበር አሉ:: በነ መንግሥቱ ንዋይ የመንግሥት ግልበጣ ጊዜም ተጠርጥሮ ታስሮ ነበር ብላናለች:: ከዚያ በኋላም ከበላይ አለቆቹ ጋር ዘወትር እንደሚጋጭ ነግራናለች:: አንድ ቀን አዲስ አበባ ለስራ ጉዳይ እንደሚፈለግ ተነገረውና ሄደ:: ከዚያ በኋላ አልተመለሰም:: እንደ ዋዛ ወጥቶ ደብዛው ጠፍቶ ቀረ» አለች ሰላማዊት እምባዋ ዐይኗ ሞልቶ::

«ከቤተሰብ የሚያስደብቅ ምን ጥፋት ተገኝቶባቸው ነው ግን?» አለች ትሩፋት የሰላማዊት ሀዘን ተጋብቶባት::

«በኋላ እንደተወራው ከሆነ የንጉሡን አስተዳደር ከሚቃወሙ ከነደጃዝማች ታከለ ወልደሐዋርያት ጋር አብሮ አሲሯል፤ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን የመንግሥት ለውጥ እንቅስቃሴ ይደግፋል:: ተብሎ እንደ ተጠረጠረና በድብቅ ቦታ እንደ ታሰረ ጭምጭምታ ሰማን:: እናታችን አዲስ አበባ አለ የተባለ እስር ቤት ሁሉ አንድ አልቀራትም:: የነበራትን ጥሪት ሁሉ አሟጣ እስከትጨርስ ድረስ ፈለገችው--አስፈለገችው:: የወደቀበትን ቦታ ማግኘት ግን ሳትችል ቀረች» ስትል ተንቀርዞ የነበረው እንባዋ ዠርግፍ ብሎ ጉርድርድ ያለውን ቀይ ፊቷን አለበሰው:: ትሩፋትን ድንገተኛ ሁኔታዋ አስደነገጣት::

«አንድ ቀን ይለቋቸው ይሆናል ሰላማዊት ተስፋ አድርጊ» አለቻት:: ምን ብላ እንደምታጽናናት እየጨነቃት::

«አ---! እሁንማ ብዙ ጊዜ ሆነው እኮ ትሩፌ! እናታች ጌጧን ሁሉ ሸጣ አይሆኑ ሆና ተንከራታ ፈልጋዋለች:: ድብቅ እስር ቤቶች የተባሉ ሁሉ አንድ አልቀራትም ግን ምንም ፍንጭ ሳታገኝ ቀረች:: ተስፋዋ ጨርሶ ሲሟጠጥ ነው አርፋ እኛኑ ወደ ማሳደግ ሥራ የተሰማራችው:: እባታችንስ መቼም እንዱን ሆኖት ይሆናል:: አሁን አሁን በጣም የምታሳዝነኝ እናቴ ናት:: 'አለ' አትል ነገር መኖሩን እታውቅ:: 'ሞተ' አትል ነገር ሞቱን በይፋ ተረድታ ዘመድ ወዳጅ አጽናንቷት እርሟን እላወጣች:: እንዲሁ 'እህ ህ ህ' ስትል ትኖራለች:: አንቱ ተብላ ተከብራ በኖረችበት እገር ተዋርዳ በየሰው ቤት የሙያ ዋለች:: ስድስት ሕፃናት ልጆቿን ማሳደግ ነበረባት» ስትል እንባዋ እንደ.ገና መገንፈል ጀመረ::

«በእናትሽ ሰላማዊት አታልቅሺ:: በማልቀስ ራስሽን አትጉጂ» አለች ትሩፋት የአሷም እንባ እየተናነቃት::

«የመጀመርያ ልጅ እኔ ነኝ:: አስረኛ ክፍል መቼ ደርሼ--- ይህንን ኮርስ መቼ ወስጄ--- ለእናቴ እንደምደርስላት ሳልም ነው የኖርኩት» አለች ሰላማዊት ሳግ እየተናነቃት:: «አሁን-አሁን ምን እንደምመኝ ታውቂያለሽ ትሩፌ?» አለች ቀጠለችና::

«ተምሮ ከመመረቅ ሌላ ምን ትመኛለች ሰላምዬ?»

«አገሩ ሁሉ የሚያወራው ወሬ እውነት በሆንና የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥስት በተገለበጠ ስል እመኛለሁ:: ምን እልባት እባቴን አንዱ እስር ቤት ውስጥ ዘግተውበት ከሆን የመውጣት እድል ይኖረው ይሆናል እያልኩ እጉል ሕልም እልማለሁ:: ካልሆነም እርማችንን አውጥተን ይቆርጥልን ነበር:: አንዳንድ ጊዜ አፈር ያላለበሱትን ሰው ሞት አምኖ መቀበል ያቅታል፤ ያሞኛል መሰለኝ::» አለች ሰላማዊት አጠቃላዩን የአገሪቱን ለውጥ እየናፈቀች::

«የት ይቀራል ብለሽ ነው ሰላምዬ:: እንደሚነፍሰው ንፋስና እንደሚወራው ወሬ ከሆነ ንጉሡ ይህን ዓመት እንኳ የሚቆዩ አይመስልም:: የፖሰቲካው ወሬ ያስፈራል:: የታክሲ ሹፌሮች ስራ እቆሙ፤ የሠራተኛ ማኅበር ሰላማዊ ሰልፍ ጠራ፤ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የርሀብ አድማ መቱ፤ መምህራን የስራ ማቆም አድማ ሊያደርጉ ነው፤ ወታደሩ የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ አቀረበ .....የማይወራ የፖለቲካ ወሬ የለም እኮ!» አለች ትሩፋት:: የክፍል መግቢያ ሰዓት ደርሶ ወደ ክፍል ሲገቡ ሁሉ የሚያስቡት ስለሚነፍሰው የለውጥ ነፋስ ነበር::

******

ትሩፋትና ጓደኞቿ ከተለያየ የአገሪቱ ክፍል የተሰባሰቡ ናቸው:: ሁሉም ይህንን ኮርስ ቶሎ ጨርሰው ለቤተሰቦቻቸ መድረስ ይፈልጋሉ:: ለስድስት የተከራዩዋት ቤት ስድስት አልጋ ተጥሎባት የሐኪም ቤት የህሙማን ክፍል ትመስላለች:: ያውም ሦስተኛ ማዕረግ::





በእረፍት ጊዜያቸውና ማታ ማታ ስድስቱም እንደ ዶሮ አልጋቸው ላይ ሰፍረው ወሬያቸውን ይቀዳሉ::

ጨዋታው ሞቅ ባለ አንድ ምሽት ትሩፋት በአካል እንጂ በሐሳብ አብራቸው አልነበረችም:: አስካለ እውቃባታለች::

«ትሩፌ የቅድሙ ልጅ ሐሳብ እስካሁን አለቀቀሽም እንዴ ምነው ዝምታ አበዛሽ? አለቻት::

«አያዳመጥኩ እኮ ነው አስካለ:: መቼም ያለአድማጭ ሁላችንም በአንድ ጊዜ አንናገር ነገር» አለች ትሩፋት::

«እሱን እንኳ ተይው:: ብቻ አይዞሽ ሐሳብ አይግባሽ» አለች እስካለ ፈገግ ብላ::

«ምን የሚያሳስብ ጉዳይ አለኝ ብለሽ?» አለች ትሩፋት::

«የልጁ ሁኔታ ሳያሳስብሽ አልቀረም:: ዓይነ ውሃውን ሳየው ደግሞ ዘመድሽ አልመሰለኝም» አለች እስካለ።

«ዘመዴ ካልሆነ ታድያ ሌላ ምኔ ሊሆን ይችላል?» አለች ትሩፋት ዐይኗን ጠበብ አድርጋ እየተመለከተቻት::

«አውነቱን ልንገርሽ ትሩፋ ልጁ በፍጹም ዘመድሽ አይደለም:: ሁኔታውን ላስተዋለው በጣም በፍቅርሽ የተያዘ መሆኑን ነው የሚሳብቅበት:: ዐይኑን ከዐይንሽ ላይ መንቀል አቅቶት እንዴት ይንከራተት እንደ ነበር እስተውየዋለሁ» ብላ ትከዝ እለች አስካለ:: አዚዛ፣ ሌንሳ፣ ትርሀስና ሰላማዊት ጆሮ ብቻ ሆኑ::

«የተሳሳተ ግምት ነው» አለች ትሩፋት ለዘብ አድርጋ::

«አባክሽ ተይኝ ትሩፋት:: የፍቅርን ነገር ለእኔ አትነግሪኝም:: ሰፍሰፍ ብሎ ዐይን ዐይንሽን እንዴት በስስት ያይሽ እንደ ነበር ተመልክቼዋለሁ:: የፍቅርን ክፉ ጨካኝ ዱላ የደረሰበት ብቻ ነው የሚያውቀው:: እንዴት እንዳሳዘነኝ አትጠይቂኝ» አለች እስካለ ከልቧ::

«ዛሬ የፊቅሪን ፊሊሲፊና በደንቢ መማር አለቢን» አለች ሌንሳ::

«ስለፍቅሪስ ሙንም አላውቁም ለማለት ነው? ሌንስ ወይ?» ጠየቀች ትርሀስ ፊቷን ከአስካለ ወደ ሌንሳ መልሳ

«አቦ በእናታችሁ ወሬ አታቆርፍዱ:: ቀጥይ እቴ እስካለ» ብላ ትርሀሰንና ሌንሳን ገላመጠቻቸው አዚዛ:: መቼም ወሬው ሁሉ ስለ ፍቅር ብቻ ቢሆን የሁልጊዜ ምርጫዋ ነው:: የፍቅረኛዋን ወሬ ማውራት ከጀመረች አሷም ማቆሚያ የላትም::

«ምን ይገባቸዋል ብለሽ ነው:: በእነሱ ቤት እኮ ማሾፋቸው ነው:: ገና እልተገኙም መሰል:: ፍቅር ደርሶባቸው ቢሆን ኖሮ ባልቀለዱም ነበር:: በተለይ በምንም ከማይገጣጠሙ ሰዎች ላይ ሲጥል» አለች እስካለ::

«ይቅርታ እስካለ! አንቺ ደርሶብሻል ማለት ነው?» ጠየቀች ትሩፋት::

«ዘጠነኛ ክፍል እያለሁ ሲፈርድብኝ አንድ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ወደድኩ:: የትምህርት ቤቱ የእግር ኳስ ቡድን በረኛ ነበር» አለች:: ሁሉም አፋቸውን ከፍተው ማዳመጥ ጀመሩ::

«የትምህርት ቤቱ የእግር ኳስ ጨዋታ ሲኖር የምሆነውን አትጠይቁኝ:: እሱ ባለበት ግብ ስር ሆኜ እስከ ጨዋታው ፍጻሜ ድረስ ሳንቃዬ እስኪሰነጠቅ ድረስ ድጋፍ ስሰጥ እውላለሁ:: ለአፍታ እንኳን ዐይኔን ከላዩ ላይ ሳላነሳ:: ያፈረጠመ ጡንቻውን ከለበሰው ማልያ ጋር ሳደንቅ---- ኳሷ ጋር በተነሳ በወደቀ ቁጥር በሐሳብ አብሬው ስነሳ ስወድቅ::» አለች ፊቷ ላይ ቅሬታ እየታየ:: «የሚያሳዝነው» አለች ቀጠለችና «የሚያሳዝነውና የሚገርመው ነገር ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? እኔ እንዲህ ስሆንለት እሱ በዚች ምድር ላይ ከነመፈጥሬ እንኳን ጨርሶ እያውቅም ነበር::» ብላ ደረቅ ሳቅ ተንከትክታ ሳቀች:: ሳቋ ሲበርድላት:: «እሱ ለካ የሚወዳት ሌላ ልጅ ነበረችው:: ይህንንም እያወኩ ዝም ብዬ በየሄደበት ስሄድ-- በተገኘበት ቦታ ሁሉ ስገኝ ያ ዓመት ከእሱም ከትምህርቴም ሳልሆን በከንቱ ባከኖ ቀረ:: ክፍል በመድገሜ አባቴ በጣም አዘነብኝ፤ አፈረብኝ» አለችና አንገቷን ደፋ አድርጋ ትከዝ አለች:: ሁሉም አዘኑላት::

«በሚቀጥለው ዓመት እማርበት የነበረውን ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ቀየርኩና ቀ.ኃ.ሥ ገባሁ:: ቀስ በቀስ ከያዘኝ ከፉ ፍቅር እያገገምኩ ብመጣም ልጁን ጨርሶ መርሳት ግን አልቻልኩም ነበር:: ይገርማችኋል የመጀመሪያ የልጅነት ፍቅር ከፉ ነው አይረሳም:: ልብ ውስጥ ር---ቆ ተቀብሮ ይኖራል:: ዛሬም እንኳ ልጁን ባስብኩት ቁጥር ፍቅር ያገረሽብኛል» አለች እስካለ በትካዜ::

«እስካለ በ--ይ ባታነሽው ይሻልሻል:: እዚህ ተቋም ውስጥ ብትወድቂ መባረር እንጂ መድገም የለም» አለች ሰላማዊት::

«ትሩፋት ዘመዴ ነው ያለችው ልጅ ያሳዘነኝ ችግሩ ስለገባኝ ነው::» ብላ ትሩፋትን በጠያቂ ዓይን ትኩር ብላ ተመለከተቻት:: «ደግሞስ የሚፈቀር ልጅ ነው:: ምን





ይወጣለታል?» አለች እስካለ አንገቷን እየነቀነቀች:: ይህን ጊዜ ሰላማዊት፣ ሌንሳ፣ አዚዛና ትርሀሰ በሳቅ ፍርስ አሉ:: ትሩፋት ኮሰተር እንዳለች ነበር::

«ምን ያስቃችኋል? የተናገርኩት እውነት አይደለም?» አለች እስካለ ሁሉንም አፈራርቃ እየተመለከተች::

«እቦ እኛን ለቀቅ አድርጊንና እንደ ጀመርሽ ትረካሽን ጨርሽ!» አለች አዚዛ::

ትሩፋት ከነዚሁ ጓደኞቿ ጋር ሆና ወደ ተቋሙ ሲቃረቡ ፍቅሩን ድንገት በር ላይ ስታየው በህልም ዓለም ያለች ነበር የመሰላት። እንደ መሮጥ ካለች በኋላ ቀጥ ብላ ቆመች:: ሰሚን ጠርቶ ጎተት አድርጎ ጉንጯን ሲስማት እንኳ ገና ከሰመመኗ አልወጣችም ነበር።

ከጎንደር ደብረታቦር ድረስ ቢመጣ ቅርብ ነው። ባህርዳርም ቢሆን ለጎበዝ ተጓዥ በእግር እንኳ የውሎ ገብ መንገድ ቢሆን ነው። በትራንስፖርት መኪና ሶስት ቀን የሚወስደውን መንገድ ተጉዞ አስመራ ድረስ ይከተለኛል ብላ ግን ጨርሶ ልታስበው ቀርቶ ልታልመው አትችልም:: እነእስካለ ቆም ብለው ጥቂት ጠብቀዋት ነበር። የመግቢያ ሰዓቱ መቃረቡን ሲያዩ ጥለዋት መግባት ግድ ሆነባቸው። ትሩፋት-- ፍቅሩ ያናዳት--ያስገርማት ወይ ያሳዝናት ሰሜቷን እንኳ በቅጡ ለይታ አላወቀችውም:: ራሷን መግዛት ተስኗት ባለችበት ድርቅ ብላ ቆማ ነበር:: የግቢው በር ሲንገጫገጭ ድንገት ከእንቅልፉ እንደ ነቃ ሰው ብንን አለች። የተቋሙ ዘበኛ በሩን በመዝጋት ላይ ነበር:: በደመነፍስ ሮጥ ብላ ገባች።

«ተምረሽ እስከምትወጭ እዚሁ እጠብቅሻለሁ» ሲላት እንኳ አልሰማችውም ነበር። ክፍል ከገባች በኋላም እንደ ሌላው ጊዜ ተረጋግታ መማር አልቻለችም:: ሐሳቧ ሁሉ ፍቅሩ ሆኖ ነው የዋለው። ከትምህርት በኋላ ስትወጣ እውነትም በር ላይ ቆሞ እየጠበቃት ነበር። በቆመበት ጥላው ብትሄድ በወደደች-- ግን ልጁ እንዲሁ በዋዛ የሚተዋት እንዳልሆነ ታውቃለች:: የሚለውን ልትሰማው እጠገቡ ስትደርስ ቆመች:: ሰላምታ እንኳ አልሰጠችውም:: ማን ቀድሞ ይናገር? ዝምታ ሆነ:: እነእስካለ ትንሽ ፈቀቅ ብለው እየጠበቋት ነበር። በቶሎ እንደማይለያዩ ሲገነዘቡ ግን ወደ ቤት መሄዱ እንደሚሻል አምነው ሄዱ። ፍቅሩ ነበር የሞት ሞቱን ከባዱን ዝምታ የሰበረው::

«ትሩፋት እንደምን አለሽ? አስመራ ከተማ የተስማማሽ ትመስያለሽ» አላት። «ምን አገባህ?» በሚል አይነት ፊቷን ከስከስ አድርጋ ማዶ ማዶ እያየች ዝም አለችው:: ፍቅሩ ግራ ገባው። በፊትም ቢሆን እንዲሁ ስር ስሯ ይከተላታል--- ዐይን ዐይኗን ያያል እንጂ ከሷ ጋር ሲሆን ዝምተኛ እንደበቱ ይበልጥ ይዘጋል:: ዐይኑን ግን ቢወጉት እላዩዋ ላይ አይነቅልም::

«ትናንት ነው ገና የመጣሁ። ያረፍኩትም ከአንዲት ዘመዴ ቤት ነው። ስመጣ ከእናቷ ላይ እድራሻና ስልክ ቁጥር ውሰጂ ነበር» አለ። ዐይኗን ተከትሎ እሱም ማዶ ማዶውን እያየ።

አይመለከተኝም በሚል ዓይነት አሁንም ዝም አለችው:: ተጨነቀ። ዝምታዋ ቢያስጨንቀውም ንግግሩን ቀጠለ::

«እሷም ቢሆን የተመቻት አይደለችም። ቡና ቤት ውስጥ ነው የምትሰራው። የምትኖርባት ቤት ደግሞ አንድ ጠባብ ክፍል ናት። እዚያም ሰዎችን ሳታስተናግድ አትቀርም መሰለኝ የሆኑ ሰዎች ከመሸ መጥተው ነበር:: እኔ በመኖሬ ይመስለኛል ማስተናገድ የማትችል መሆኗን ነግራ ስታሰናብታቸው ሰምቻለሁ። እንዴው ከአንቺ ጋር እንመካከ...» አላስጨረሰችውም።

«ለመሆኑ ምንህ ስለሆንኩ ነው ከኔ ጋር የምትመካከረው!? እጮኛህ ነኝ!? ሚስትህ ነኝ!? እስቲ ንገረኝ በምን ሂሳብ ነው ምክክር ውስጥ የምንገባው!?»

«ሁሌም እንደምታደርጊው እውቀሽ ልታሳዝኚኝ ነው እንጂ ከምንም በላይ እንደምወድሽ ታውቂ....»

«አላውቅም በቃ!» ሐሳቡን ሳታስጨርሰው በድጋሚ ጮኸችበት::

«እባክሽ ትሩፌ ሌላው ቢቀር ቀስ ብለን ለመነጋገርና ለመመካከር እንሞክር:: አድገናል እኮ! ትልልቆች ሆነናል እኮ!»

«ትሩፋት አስመራ የመጣችው ልትማር እንጂ ስራ ይዛ ነው ለሉህ!? በአንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ ለስድስት ተፋፍነን ነው የምንኖረው። እኔ ሰራሴ ያልሆንኩ ለአንተ ምን ልተርፍህ ነው የምንመካከረው!? እዚህ ድረስ ስትንተት የመጣህብኝ ምን ልትሰራ አስበህ ነው? ሁሉም ነገር በኋላ ይደር....» እንባ ተናነቃት። ትሩፋት መከፋቷ ጣራ ካልነካ ወይ ደግሞ እጅግ አሳዛኝ ነገር ካልገጠማት በስተቀር ውሃ ቀጠነ ብላ በሆነ ባልሆነው አታለቅስም። እንባ ለእሷ የንዴት ወይም የብሶት ማስተንፈሻ አይደለም። ለቅሶ ለእሷ የጥቃት ምልክት ነው---የመሸነፍ--- አሁን ግን ሆድ ባሳት። አለቀሰች::

ፍቅሩ ምንም አላለም:: ጭንቅ ብሎት ሁለት እጁን እያፋተገ ይመለከታታል::

«ቆይ ግን! እኔና አንተ አሁን ተመካከረን ምን የምንፈጥረው ነገር ያለ ይመስልሃል? ዳሩ ማሰብ ካቆምክ ቆይተሃል። የምታስብ ቢሆን ኖሮ ከጎንደር ትምህርትህን አቋርጠህ ደብረታቦር ስትመጣ የደረሰብህ ችግርና ፈተና ትምህርት ሊሆንህ ይገባ ነበር:: ማሰብ የሚችል አእምሮ ያለው ሰው ብድግ ብሎ ጉም ሲጨብጥ አይነሳም» አለች እንባዋ በወፍራሙ እየወረደ::

መንገድ ላይ መሆናቸውን የሚያስታውስ አቅል አልነበራትም። እላፊ አግዳሚው ሁሉ ዞር ዞር እያለ እስከሚያያቸው ድረስ ጮኸችበት። ፍቅሩ ግራ ገባው። ዝም ብሎ ከንፈሩን





እየነከሰ ሊያደማው ደረሰ። እጇን ያዝ ሊያደርጋት ሲል «አትያዘኝ» ብላ በኃይል ስትነጥቀው እጇ አየር ላይ ተወናጨፈ። በሁለት እጇ ፊቷን ሸፍና ስቅስቅ ብላ ሳግ እስኪተናነቃት ድረስ አለቀሰች።

«ከልጅነት የጀመርከ እንደ ጥላ እየተከተልከ ስታሳቅቀኝ ኖርከ። ተምሬ መድረስ ካሰብኩበት ዓላማ እንዳልደርስ ነው አይደል ፍላጎትህ!? ትምህርቴን አቋርጬ እንደ አንተ ከርታታ እንድሆን አይደል ምኞትህ!? በቃ ደስ ይበልህ!! ከነገ ጀምሮ አልማርም!! ትምህርት ብሎ ነገር እርግፍ አድርጌ ትቼ የትም እሄድልሃለሁ። የልብህ ይድረስልህ!» አለችው ምርር ብላ።

«ትሩፌ በዓለም ላይ ስትኖሪ ፈጽሞ ተከፍተሽ ማየት አልፈልግም:: እኔም እኮ የማደርገው ጨነቀኝ:: ፍቅርሽ ናላዬን እዞሮት የምሆነውን አሳጣኝ:: ግራ ገባኝ! እንዲህ ስታለቅሽ ማየት ራሱ ምን ያህል ህመሙ እንደሚያሰቃየኝ ምነው ውስጤ የሚታይሽ በሆነ?» አለ እሱም እንባው እየተናነቀው። የእሷ እንባ አሁንም እየወረደ ነው።

«እባክሽ ትሩፌ! እባክሽ አታልቅሽ! እንዲህ ከፍቶሽ ከማይ አንድ ጊዜ አይደለም-- ሺህ ጊዜ ብሞት እንደሚሻለኝ እንዴት አድርጌ ልቤን ላሳ...» ንግግሩን መጨረስ አልቻለም:: የእሱም እንባ መውረድ ጀመረ።

«እግዚአብሔር ነው የፈረደብኝ። መጀመሪያውኑ አንተን ሲልክብኝ» አለች እየተማረረች።

«እኔስ ወድጄና ፈልጌ የማደርገው ይመስልሻል ትሩፋት? እስችሎኝ ተረጋግቼ ብማር ወይ ስራዬን ብሰራ አይሻለኝም ነበር:: በራሱ ፈቃድ እንዲህ የሚሰቃይና የሚንከራተት ሰው በዓለም ላይ ይኖራል ብለሽ ታስቢያለሽ? ራሱ ፈልጎ ከቦታ ቦታ እየተንከራተተ እድሜውን በከንቱ የሚጨርስ ሰው ይኖር ይመስልሻል? ከነፍሱ በላይ ወዶና አፍቅሮ በራሱ ላይ ስቃይና መከራ የፈጠረ ከኔ በቀር ሌላ ሰው አይተሽ ታውቂያለሽ ትሩፌ? እኔንም እኮ ያልፈለኩት ፍቅርሽ አዞብኝ ነው:: ያልመረጥኩት ፍቅርሽ ገዝቶኝ ነው:: ሌላው ቢቀር ይህን እንኳ ብትረጅልኝ ምን አለበት?»

«በአንተ ጉዳይ እኔን ምን አገባኝ! የሚገባኝ ነገር ቢኖር አልፈህ ተርፈህ እኔንም መኖሪያ እንዳሳጣኸኝ ነው:: ለራስህ ተንከራረህ እኔንም ጨምረህ ከርታታ ልታደርገኝ መነሳትህን ነው:: ከልጅነት እስከ ዛሬ በየሄድኩበት እየተከተልከ እላስቀምጥ እላስቀምጥ ያልከኝ መሆኑን ብቻ ነው።» አለች ከልቧ እያነባች::

«እሺ አሁን ሁሉንም ነገር ተይውና ወደ ቤትሽ ልሸኝሽ::»

«አልፈ---ልግም!! አልፈ---ልግም!! ሸኚ አያስፈልገኝም!! አብረውኝ የሚኖሩት ጓደኞቼ እንዲያዩህ ጨርሶ አ-ል-ፈ-ል-ግም!!

«አይተውኛል እኮ» አላት እንደ ሁልጊዜው ረጋ ብሎ።

«እቤት ድረስ እንድትከተለኝ አ-ል-ፈ-ል-ግም!!» አለች በንዴት፡፡ በልቧ የምትኖርበትን አካባቢ እንዳያየው አስባ ነበር። ቢቸግራት ነው እንጂ ፍቅሩ ጠና--ትሩፋት ትኖርበታለች የተባለን ቦታ ፈልጎ አያጣውም። ከባህርዳር አስመራ ድረስ እንኳን መጥቷል፡፡ ሲያገኛት ደግሞ አልተቸገረም፡፡

«በፈጠረህ እዚህ ትምህርት ቤት በር ድረስ አትምጣብኝ፡፡ የእጬ መምህራን ሁሉ መጠቋቆሚያና መተረቢያ አታድርገኝ፡፡»

«ሌላ የምንገናኝበት አመቺ ቦታ ከተገኘ እዚህ ድረስ ለምን እመጣለሁ? ላንቺ የሚመችሽ ቦታ ካለ ንገሪኝ።»

«ተመርቄ እስከወጣ ድረስ እንዳገኝህ አልፈልግም። እውነት ከልብህ የምትወደኝ ከሆነ ይህን ብቻ ልለምንህ» አለችው።

«ብችል ባደርገው ደስ ባለኝ። እሺ አሁን ወደ ቤትሽ ሂጂ። ብሸኝሽ ጥሩ ነበር። ካልፈለግሽ ግን ምን ማድረግ እችላለሁ? ደህና እደሪ» ብሎ እጇን ሊጨብጥ ሲል «አትንካኝ» ብላ ተወራጨች። ተሰናብቷት ከሄደ በኋላም እዚያው ባለችበት ፍዝዝ ብላ እንደ ቆመች ነበር። አንድ በብስክሌት የሚሄድ ወጣት

«አጀሂ ዘሁብተይ! ዓለም ተሸዓተ፤ ብዙህ አይትሰበ፡፡» (አይዞሽ እህቴ ዓለም ዘጠኝ ናት ብዙ አትሰቢ) ባይላት ኖሮ ከገባችበት ጥልቅ የሀሳብ ባሕር ውስጥ የምትወጣ አትመስልም ነበር። እቤት ስትደርስ እንደ ፈራችው ጓደኞቿ ደግሞ ርዕስ ጉዳያቸው አድርገው ጠበቋት፤ ጥያቄ በጥያቄ አዋከቧት። ብዙ የማትናገረው ሌንሳ እንኳ በጥያቄ አፋጠጠቻት፡፡

«ውነቲ ዘመድሽ ነው ትሩፌ? በመሊከ ጊን ሚናችሁም አይመሳሰሊም» አለች ሌንሳ፡፡

«ዋይ! ሌስወይ ዶሞ ደህና ሰው አልነበርሽ። ሙን ማለትሽ ነዎ? ትከ እሷን ነዎ። ዐይኑ---ስኑ---ጨጉሩ --አፍንጫው» አሾፈች ትብለጽ።

«አቦ ልጅቷን ለቀቅ አድርጓት 'ዘመዴ ነው' ብላለች ዘመዷ ነው በቃ!» አለች አዚዛ፡፡

«'ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው' አሉ እማማ ማሚቴ። ልጅቷን ምን ፍጠሪ ነው የምትሏት? ዘመዷ አለመሆኑን ዘር ቆጥራችሁ ሐረግ መዛችሁ የደረሳችሁበት አትመስሉም? ይልቅስ የሚያዋጣችሁን ጥናታችሁን ጠበቅ እሷን ለቀቅ» አለች እስካለ።





ሁሉም መጽሐፎቻቸውን ገለጡ። ትሩፋት ማጥናት አልቻለችም። ተሸፋፍና ጥቅልል ብላ ተኛች፡፡ እንቅልፍ ግን በዐይኗ አልዞረም። ፍቅሩ ከሚባል ልጅ ጋር የምትገላገልበት መንገድ ብታውጠነጥንም ምንም ዘዴ አላገኘችም፡፡ እንዲሁ በሐሳብ ስትባዝን ነበር ያደረችው፡፡ ቧት ስትነሳ ከብድ ብሏታል፡፡ ፍቅሩ በር ላይ እንዳይጠብቃት ተመኘች፡፡ እትቀር ነገር ሰሞኑን ፈተና ይሰጣል፡፡ ወደ ተቋሙ ሲሄዱ መንገዱን ሁሉ የምታስበው ፍቅሩ ከሚባል ልጅ ጋር እንዴት መገላገል እንደምትችል ነበር፡፡

******

ትሩፋት አስመራ መምህራን ተቋም ያሳለፈችው ጊዜ የተሰፋና የሰቀቀን ጊዜ ነበር፡፡ ተመርቃ ስራ የምትይዝበትን ቀን ስታስብ ተስፋዋ ይለመልማል፡፡ የፍቅሩ አስመራ ከተማ ውስጥ መኖር ደግሞ ያሳስባታል፡፡ ቅዳሜ ቅዳሜ የእስካለ መዋያ አይታወቅም። አስመራ ከተማ አትበቃትም--ትጠባታለች፡፡ ቀኑም አይበቃትም-- ያጥርባታል፡፡ አምሽታ ነው የምትገባው። አንድ ቅዳሜ እንዲሁ እንደ ልማዷ ከመሸ ነበር እቤት የገባችው፡፡ የሚገርመው ግን እንደ ሁልጊዜው ብቻዋን አልነበረችም።

«ደህና አመሻችሁ ልጆች? እንግዳ ይዤላችሁ መጣሁ» አለች፡፡ አንገቷን እየነቀነቀችና እየተፍለቀለቀች። የሁሉም ዐይኖች እንግዳው ላይ ተወረወሩ። የትሩፋት ዐይኖች ፈጠጡ። ፈጽሞ ማመን አልቻለችም። ያየችው እውነት ግን ያው ነበር፡፡ ፍቅሩ ጠና ራሱ በአካል ከፍሉ መሀል ቆሟል።

«ትሩፋት- እኔና አንቺ ከእኔ አልጋ ላይ እንተኛለን፡፡ ይኸ ዘመድሽ ደግሞ ካንቺ አልጋ ላይ። መቼም በአገር ሰላም ሰው ማደሪያ አጥቶ እየተንከራተተ ጅብ ይብላው አይባልም። ማደርያ ያጣን ሰው ቤት ያለው ሁሉ አስገብቶ ማስተናገድ ደግሞ መቀጠል ያለበት ጥሩ የቆዬ ባህላችን ነው። ‹ቤት የእግዚአብሔር ነው› ይላል አይደል ትልቁ መጽሐፍ» አለች እስካለ ለማሳመን እየሞከረች። ማንም ምንም አላለም። ሁሉም ባዩት ነገር የተደመሙ ይመስላሉ። እስካለ አልፋ ወደ አልጋዋ ስትሄድ ፍቅሩን ከትሩፋት አልጋ ላይ እንዲቀመጥ ጋበዘችው። ትሩፋት ምንም ምርጫ አልነበራትም። ሰቅቅ ብላ አልጋዋን ለቀቀች።

ትሩፋት የእሷና የፍቅሩ ሁኔታ መጨረሻው ምን ሊሆን እንደሚችል መላው ጠፍቷታል፡፡ ጨርሶ ግራ ገብቷታል፡፡ ሌሊቱን ሙሉ ሲያሳስባትና ሲያስጨንቃት ነው ያደረው፡፡ እስከ መቼ እንዲህ በየሄደችበት እየተከተለ በጓደኞቿ ፊት እንደሚያሳቅቃትና እንደሚያሳፍራት አታውቅም፡፡ ፍቅሩ እያለ በሰላም መማር እንደማትችል እየተገነዘበችው መጥታለች፡፡ መኖሯን እስከትጠላ ድረስ አስመርሯታል፡፡ ይባስ ብሎ አለችበት ድረስ ሰተት ብሎ መምጣቱና ማደሩ ደግሞ አሳፍሯታል። በዚህ ሁኔታ ከነዚህ ደባሎቿ ጋር መቆየት አልፈለገችም፡፡ ሌላ ቦታ መሄዱ የሚሻል መስሏታል፡፡ ፍቅሩ ያለችበትን ቦታ ፈልጎ

እንደማያጣው ብታውቅም ለጊዜውም ቢሆን ከሌላ ሰው ጋር ተዳብላ ከዚህ ሰፈር መውጣት እንዳለባት ወሰነች።

አበራሽ ተሰፋዬ ከጋይንት መጥተው ደብረታቦር ከሚማሩት ልጆች አንዷ ነበረች። ከትሩፋት ጋር የጠበቀ ግንኙነት አይኑራቸው እንጂ ደብረታቦር አንድ ከፍል ውስጥ ተምረዋል። አሁን ደግሞ ለመምህራን ኮርስ ስልጠናው እሰመራ ከተማ ትገኛለች። ዘግይታ ነበር የመጣችው። እሺ ብትላት አብረው እንዲሆኑ ልትጠይቃት አሰባለች። ተቋሙ ውስጥ ሲገናኙ ጉዳዩን እነሳችላት። አበራሽ ራሷ ያለችበት ሁኔታ አልተስማማት ኖሮ በደስታ ነበር ሐሳቧን የተቀበለችው። ሁለቱም ለደባሎቻቸው ምክንያት እየፈጠሩ ተለዩዋቸው። ቪላጆ በሚባለው ሰፈር ቃኘው ሰቴሽን የጦር ካምፕ አካባቢ በሚገኝ አንድ ትልቅ ግቢ ውስጥ የምትከራይ አንዲት እነስተኛ ከፍል አግኝተው ገቡ። ትሩፋት እስከ ተቋሙ ያለውን ቀጥ ያለ የማይገፋ የአስፋልት መንገድ ርዝመት ብትጠላውም ከአበራሽ ጋር መሆኗን ወዳዋለች:: ሆኖም እነ እስካለም ቢሆኑ የሚረሱ ልጆች አልነበሩም:: በተለይ የሴንሳ ጭኮና የትርሀሰ ጥህሎ እንዴት ይረሳል? አብራቸው መኖር ቢቀርም በፍቅር መጠያየቁን ተስማማት::

******

ትሩፋት በአሰመራ ቆይታዋ ግርም የሚላት የአሰመራ ሰው ሁሉ ለኢትዮጵያ ባንዲራ ያለው ከልብ የመነጨ ፍቅር ነበር:: በእያንዳንዱ ሰው ቤት ሲገባ አረንጓዴ--ቢጫ--ቀይ ባዲራ ይታጣል ማለት ዘበት ነው:: የሰርግ ድንኳን የሚያሸበርቀው በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ መሆኑን አስተውላለች:: አስከሬን የሚሸኘው እንዲሁ በኢትዮጵያ ባንዲራ ተውቦ ነው:: ባንዲራ ጧት ሲወጣና ማታ ሲወርድ እንኳን ሰው ከብቶች ቀጥ ብለው ይቆሙ እንደ ነበር የዐይን ምስክር ናት:: «ለባንዲራዋ ክብር እረኛቸው ሲቆም የሚነዱ ከብቶች ሳይቀሩ ቁሙ የተባሉ ይመስል እንደ ሰው ባሉበት ይቆማሉ» ብሎ ሌላ ሰው ቢነግራት እሷም ላታምን ትችል ነበር፤ ግን እውነት ነው በዐይኗ በብረቱ አይታለች::

ተቋሙ ውስጥ እንዲሁ የባንዲራ ሥነስርዓት ጥብቅ ነበር:: ሁሉም የተቋሙ እጩ መምህራን ጧት ሰልፍ ላይ ተገኝተው «ኢትዮጵያ ሆይ ደስ ይበልሽ......» በሚለው መዝመር ባንዲራ የማውጣትና ማታም ላይ ደግሞ « ተጣማጅ አርበኛ ደሙን ያፈሰሰው....» በሚለው መዝሙር የማውረድ ግዴታ ነበረባቸው:: ከባንዲራ ሥነ-ሥርዓት በኋላ አስተዳደራዊ መልእክቶች የሚተላለፉት እዚሁ ሰልፉ ላይ ነበር:: የተለያዩ መጣጥፎችና ግጥሞችም ይቀርቡ ነበር::





« ስለማይጥማቸው የፍቅር ድግሱ፣

ውሾች ብቻ ናቸው የሚነካከሱ::» ዓይነት የእጩ መምህር ወልደማርም የስንኝ ቋጠሮ

አበራሽ አመሏ ሸጋ ነው:: ቶሎ አትቆጣም:: ትሩፋት በተለይ በጣም የምትወድላት ጸባይዋ ደግሞ አታኮርፍም:: ትሩፋትም ብትሆን ከሰው ጋር በቀላሉ የምትግባባ ፍልቅልቅ ያለች ልጅ ናት:: አንዳንድ ጊዜ አለመግባባት ቢከሰትም ሁለቱም ግን ወድያውኑ ስምምነት ላይ ለመድረስ ችግር የለባቸውም:: በተለይ ይቺ የወልደማርያም ግጥም ደግሞ ዋና እርቀ ሰላም አውራጅ ሸማግሌያቸው ነበረች:: ትሩፋት ራሷ በዚህ የጧት ሰልፍ ላይ የግጥም ጊዜ እየተሳበች--እየተሳበች መጣች:: ለሙከራ ያህል ሦስት መጣጥፎችን አቀረበች:: «እናት፣ እንቅልፍና ነፃነት» በሚሉ ርዕሶች ላይ የተገጠሙ:: እንደ አጋጣሚ ሆኖ «ነፃነት» የሚለው ግጥሟ ለጠቅላይ ግዛቱ መምህራን ማህበር ቀርቦ ሦስተኛ በመውጣቱ ተሸላሚ አደረጋት::

«ነፃነት»

ሰለማምላከ ብሎ-- የሰውን ፊት ፈርቶ፣
የትም የሚወድቀው --ያገኛትን በልቶ፣
ለዚህ ሰው ምድነው?
መኖር —እለመኖር ነፃነትሰ ከቶ!?
አገሬ በሚላት --አትብቱ ተቀብሮ፣
እኩል ካልኖረባት ሙብቱ ተከብሮ፣
ታድያ ለዚህ ሰው
ምንድነው ነፃነት? ምን ያደርጋል ኑሮ!?
እሚበላው የለው—ወይ ይጠለልበት፣
ተናግሮ አይደመጥ —ፍርድ ተጓሎበት፣
ታድያ ለዚህ ሰው---ምንንድነው ነፃነት?

ከዚያ በኋላ በተቋሙ መምህራንና ተማሪዎች ሁሉ «ነፃነት» ሆኖ ነበር መጠሪያዋ::

******

እለተ እሁድ--ትሩፋት ተኝታ የምታረፍድበት፤ ጥሎባት አልጋዋ ውስጥ እየተንከባለለች መቆየት ከምንም በላይ ያሰደሰታታል:: እንግዲያው በጠዋት ነው የምትነቃው:: እንደ አበራሽ እንደ ነቃች ወድያው ብድግ ብላ አልጋዋን መልቀቅ ግን አይሆንላትም:: አበራሽ በጧት ተነስታ ለቁርስ ጉድ ጉድ ስትል እሷ እንደተኛች ትቆያለች::

«በእናትሽ ትሩፋት ተነሽና ቁርሳችንን በልተን በአሰመራ ከተማ ሸር ብትን እንበልባት» አለች አበራሽ:: ከምፕሽታቶ ያለችውን ዘመዷን ጠይቀው እንዲመጡ ስትለምናት አሁን ሁለተኛ ጊዜዋ ነው ::

«ነገርኩሽ እኮ አበራሽ:: ቅዳሜንና እሁድን እንዴት በናፍቆት እንደምጠብቃቸው ስታውቂ» አለች ትሩፋት አልጋዋ ውስጥ እንደ ሆነች::

«ከነቁ በኋላ አልጋ ውስጥ መጋደም እስቲ ምን የሚሉት አባዜ ነው? በሽተኛ ብቻ ነው ተኝቶ የሚውል:: ይልቅ ተነሽና የአሰመራ ከተማን ውበት እያደነቅን ቆንጆጅቷንም እንመልከት:: በኮምፕሽታቶ ዘንባባዎች ውስጥ መዳዝ ለእኛም ሽርሽር ነው» አለች አበራሽ አሁንም ተስፋ ባለመቁረጥ::

«ከፈለግሽ ነገ ከትምህርት በኋላ እንሂድ:: እንዴውም ኮምፕሽታቶ የምታምረው በምሽት ነው:: ዛሬ አልሄድም አልኩሽ::

«ሞዛዛ ነሽ እሺ! የሰው ሞዛዛ! እዚህ አልጋ ላይ ተጋድመሽ የድብርት መጫወቻ ከምትሆኚ ላንቺም ወጣ ማለቱ ይሻልሽ ነበር:: ልንገርሽ! መንፈስሽንና አካልሽን ከማድቀቅ ሌላ ትርፍ አታገኚም!» አለች አበራሽ ተናዳ::

አበራሽ አብራት እንደማትሄድ ስታውቅ እየተነጫነጨች ወጥታ ሄደች:: ትሩፋት አልጋዋ ውስጥ ሆና እንዲሁ ስትታሽ ቆይታ የተነሳችው ሲርባት ነበር:: ምሳ ለመብላት ጉድ ጉድ ስትልና ፍቅሩ «እንደምን ዋላችሁ» ብሎ ሲገባ እንድ ሆነ:: ገና ሲታየው «ከአበራሽ ጋር ሄጄ በነበር» ስትል ተቆጨች:: እንዲው ዝም ብላ ነው እንጂ ፍቅሩ ቅዳሜና እሁድ ወደ እሷ ያልመጣበት ጊዜ ውስን ነው:: ግባ ባትለውም ገብቶ አልፎ ሄዶ ከእሷ አልጋ ላይ ተቀመጠ:: ሙርሙር ሲያደርጋት የነበረው ርሀብ ጠፋ:: ከአበራሽ አልጋ ላይ ሄዳ ተቀመጠች:: ውስጧ ብሽቅ እያለ የሚለውን ለማዳመጥ ተዘጋጀች:: ትንሽ ዝም ዝም ተባብለው ከቆዩ በኋላ

«አበራሽ የለችም እንዴ? ዛሬ ብቻሽን እንዴት ተገኘሽ?» አላት ትክ ብሎ እያያት::

«ወጣ ብላ ነው አሁን ትመጣለች» አለች ደጅ ደጁን እየተመለከተች::

«ኖረችም አልኖረችም ዛሬ እኔና አንቺ ተነጋግረን አንዱን ወስነን መለያየት ይኖርብናል:: አላት ፍርጥም ብሎ:: እሷም በጥያቄ አተያይ አይታው ዝም አለች::

«ግን ለምን ችግሬ አይገባሽም ትሩፋት? እንደው አንቺን ብዬ እንዲህ ስንከራተት ትንሽ እንኳ አላሳዝንሽም?» ሲላት ድምጹና አስተያየቱ አንጀት ይበላ ነበር::





«ይገባኛል----ታሳዝነኛለህ:: ግን ምን ማድረግ ነበረብኝ? ገና ደብረታቦር እያለን ሁለታችንም ተረጋግተን መማር እንዳለብን አጥብቄ ለመንኩህ፤ መከርኩህ:: ያለንበትን ሁኔታ መገንዘብ አቅቶህ እኔንም ጨምረህ ግራ አጋባኸኝ እኮ ፍቅሩ»።

«ምን ተስፋ ስጥተሽኝ ምን ተስፋ ይዤ ልረጋጋ ትሩፊ? ወደድኩህ የለ--አልወደድህም የለ ከአለት የከበደ ዝምታሽ 'ላም አለኝ በሰማይ..'ሆኖብኝ ተጨነቅሁ እኮ! ገና በጧቱ የለከፈኝ ፍቅርሽ ደግሞ መቆሚያ መቀመጫ አሳጣኝ:: አንቺ በሄድሽበት ሁሉ ያንከራትተኛል:: ይኸው እንደምታይኝ ትምህርቴም ቀረ። እድሜዬም በከንቱ እያለፈ ነው::»

«ሰው መሆን ማለት ራስን መቆጣጠርና ወደ ፈለጉበት ዓላማና ግብ ማምራት መቻል ነው:: ልቦናችንን የምናዘው እኛው ነን:: አንተ ልቦናህን ማዘዝ ያቅትሃል? ራስህን ማሸነፍና መግዛት እንዴት ይከብድሀል? መቼም አንተ ከሰው ሁሉ የተለየህ ፍጡር አይደለህም እኮ ፍቅሩ::»

«አንግዲያው መንከራተት ወዶልኝ ነዋ! እንዲህ የምሰቃየው! ተምሬ ለዚያች ባተሌ ድሀ እናቴ መድረስና የራሴንም ሕይወት ማሻሻል ጠልቼ ነዋ! እንዲህ ከስር ሰርሽ የምኳትነው የሰው እጅና ፊት ማየት ፈልጌ ነዋ!» ፍቅሩ ተናደደ:: ትሩፋት ደንገጥ አለች:: ዛሬ የፍቅሩ ሁኔታ ከሁልጊዜው ተለይቶባታል:: እንዲህ እምርሮና ጮሆ ሲናገር ሰምታው አታውቅም::

«የሆንኩትን እኔ አላውቅም:: ያለ አንቺ በዚች ዓለም ላይ መኖርን ገና ሳስበው ጭን---ቅ ይለኛል:: ቀኑ ይጨልምብኛል። በዓለም ላይ ብቻዬን የቀረሁ-- በጨለማ የተዋጥሁ--- በርሀ ውስጥ የተወረወርኩ ያህል እፈራለሁ:: የማደርገውን የማላውቅ መላ ቅጡ የጠፋብኝ ከንቱ ፍጥረት ሆኛለሁ:: ገና በልጅነቴ መድሀኒት የሌለዉ የፍቅር አሳት እያቃጠለኝ ያለ መፍትሄ ይኸው እስካሁን አለሁ» አለ ፍቅሩ ከፍት ብሎት::

«አንዳንድ ጊዜ ምን እንደማስብ ልንገርሽ ትሩፊ» አለ ፍቅሩ:: ቀና ብላ አይታው ዝም አለች::

«ይገርምሻል! አንዳንድ ጊዜ አጥፍተሃት ጥፋ!--- አጥፍተሃት ጥፋ! የሚል ሰይጣናዊ ሐሳብ ይመጣብኛል:: አነቃት --አነቃት!--ግደላት!--ግደላት!' የሚል ስሜት ይፈታተነኛል:: እንዲህ ከምሰቃይ ለምን አላደርገውም? ለምን የማይቀረውን ሞት ሞቼ አልገላገልም? ብዬ አዝታለሁ! እውነቱን ልንገርሽ ብዙ ቀን ላደርገው አሰቤያለሁ ግን የሚቆርጥ ልብ አጣሁ:: በራሴ ላይ አደርገው ይሆናል:: በአንቺ ላይ ግን የሚጨከን እጅ አጣሁ:: ወንድ ወጥቶኝ ባደርገው በጣም ደስ እንደሚለኝ ግን አልደብቅሽም» ብሎ እጆቹን አተኩሮ ተመለከታቸው:: ትሩፋት ድንግጥ አለች:: ፍቅሩን ባታፈቅረውም ፈርታው አታውቅም:: ዛሬ ግን ፈራችው---በጣም ፈራችው::

«ምነው ከአበራሽ ጋር ሄጂ በነበር» ስትል ለሁለተኛ ጊዜ ተፀፀተች::

«ዛሬ ግን ቁርጡን ማወቅ እፈልጋለሁ ትሩፋት። ገና ለገና 'አልወድህም፤ አልፈልግህም' የሚሉ ሁለት ቃላት ከአንቺ አፍ ሲወጡ ላለመስማት ፈርቼ ለሸሸ ኖሬያለሁ፤ ግን እስከመቼ ዝም ብዬ ከስር ስርሽ እንደጥላ አንቺን ስከተል እኖራለሁ? ትሩፋት ቁርጥ ያጠግባል:: ያልተጨበጠ ተስፋ ጉም ነው:: ጉም እንደ መዝገን:: ያደከማል-- ያናውዛል:: ደከመኝ! ሰለቸኝ! ሞቴን ወይ ሽረቴን ዛሬ ማወቅ አለብኝ» አለ ፍርጥም ብሎ። ሲጋራ አውጥቶ ለኮሰ።

«እ--ም ሲጋራም ማጨስ ጀምሯል ለካ! መግዣውንስ ከየት እያመጣው ይሆን? ፓ! አያያዙ እንኳን ቄንጥ አለው። ከመቼው እንዲህ ተካነው?» አለች ትሩፋት ገርሟት:: «አስመራ ከተማ እኮ ሀሺሽ በድብቅ ይሸጣል ይባላል። እነዚህ ሱሰኞች ደግሞ ምንም ቢሆን አይጨካከኑም። እንደ ሲጋራው ሐሸሹንም ለምዶ ይሆናል። ካለነገር እንዲህ እፉ አልሰላም» አለች አሁንም በልቧ:: ሐሺሽ ያጨሱ ሰዎች ደግሞ ሰው ከመግደል አይመለሱም ሲባል ስምታለች። ዛሬ ያ የምታውቀው እርግት ያለው ፍቅሩ አይደለም። ለመናገር መፍጠኑ-- ከእፏ እየነጠቀ ማውራቱ:: እንደ አሁኑ ሁኔታው ሀሺሽ ወስዷል ብላ ብትጠረጥርና ብትፈራው አይፈረድባትም:: ያለወትሮዋ ለንግግሯ ሁሉ ጥንቃቄ ማድረግ ጀመረች። ያለወትሮዋ ረጋ ብላ ልታግባባው ሞከረች። ለከፋቱ አበራሽ ደግሞ አሰመኖሯ:: የኮምፕሽታቶ ጅብ በልቷታል:: በጧት የወጣች ይኸው እስከ አሁን አልተመለሰችም።

«አንቺን የሚያስጠላ መድሀኒት አለ ቢሉኝ እስከ ዓለም ዳርቻ ተጉዤ በወሰድኩት ነበር። ከአንቺ ፍቅር የሚፈውስ ጸበል ባገኝ እንደ ደንቡ አንድ ወይ ሁለት ሰባት ሳይሆን አስር እጥፍ በተጠመኩ ነበር» አላት። እውነቱን ነው:: ከትሩፋት ፍቅር መገላገያ ዘዴ ቢያገኝ በዓለም ላይ የማያደርገው ነገር አይኖርም ነበር::

«ፍቅሩ ሁለታችንም ከደላው ቤተሰብ የወጣን አይደለንም። ወደድንም ጠላንም መጀመርያ ራሳችንን መቻል ይኖርብናል:: የእኛን እርዳታ የሚጠብቁ ብዙ ነፍሶች አሉ:: በኋላ ልንደርስበት በምንችለው ጉዳይ ላይ ጊዜ ባናጠፋ ይሻላል:: በእናትህ ፍቅሩ! ተጨንቀህ አታስጨንቀኝ» ስትል በእንጀራ እናት ምላስ የሚንገበገቡት ራሔልና ድልነሳ ታሰቧት:: ከእናታቸው ጋር ያሉት እህቶቿ ከፊቷ መጥተው ድቅን አሉ። በሐሳብ ልትነጉድ ስትል የተከፋው የፍቅሩ ድምጽ መለሳት::

«እንዴት ውስጤ ገብተሽ እንደተቀበርሽ እንኳ አላውቅም:: ብዙ ጊዜ ላወጣሽ ታገልኩ! አልቻልኩም:: የፍቅር በሽታ በጠና አምኝ መድሀኒቱን እጥቼ ተጨንቂያለሁ:: መውጫ ቀዳዳው ጠፍቶኝ እንደ አበደ ውሻ ተክለፍልፌያለሁ:: አንቺ ዘዴ ካለሽ እባክሽን መላ በይኝ ትሩፌ። አንቺን ሳስብ ለምመገበው ምግብ-- ለምለብሰው ልብስ-- ለምኖርበት ዓለም-- የሚያስብና የሚያመዛዝን አዕምሮ የለኝም። ብቻ እያት--- እያት--- ብረር-— ብረር





የሚለኝ ነገር ይመጣብኛል። ብድግ አድርጎ በየሄድሽበት ያከንፈኛል። አስመራ ከተማ ገብቼ አንቺን ሳገኝሽና ሳይሽ የተሰማኝን ስሜት ከቶ ምን ቃላት ሊገልጸው ይችላል? አንቺ አይገባሽም!--- አይገባሽም!!---ከቶ ሊገባሽ አይች--- ልም!! መቼም ጊዜ ገብቶሽ አያውቅም!!» ከጣራ በላይ ጮኸ። ጩኸቱ ፍርሃት ለቀቀባት። ለደቂቃዎች ሁለቱም በየራሳቸው ሐሳብ ተጠምደው ዝም አሉ::

«ታውቂያለሽ ትሩፋት» ሲላት ከሐሳቧ ብንን ብላ እ.. አለች:: ቀጠለና «በዚች አጭር እድሜዬ ውስጥ ብዙ ሴቶች አውቃለሁ። በጸባይም በመልከም ካንቺ የተሻሉ። ከአንቺ የሚበልጡ....»

ትሩፋት ከማንም የበለጠ መልከኛ የምትባል አይነት አይደለችም። እውነት ለመናገር ግን ያስደንግጥ አለባት:: ያያት ወንድ ሁሉ አያልፋትም። ትላልቅ አፋራም ዐይኖቿ ሆን ብለው ሰው የሚሸኙ ስለሚመስሉ ድንገት ያያትን ወንድ ሁሉ የሚስብ አንዳች ምትሀታዊ ኃይል አላቸው። የበሰለ እንጆሪ የመሰለው ከንፈሯ ሽሽት ብሎ እንደ በረዶ የነጣው ጥርሷ ሲታይ እንኳን የወንድ--የሴት ልብ ወከክ ያደርጋል። እርጥብ ሀር መሰሎ ጀርባዋ ላይ የተኛውን ጽጉሯን በእጁ ሊዳብስ የማይመኝ ወንድ የለም። ቁጥር መልከ ከታየ ግን ልቅም ያለች ቆንጆ የምትባል ዓይነት አይደለችም:: ብቻ የደስ ደስ አላት:: ደሙን ፍስሰሰስ ያደረገባት የደም ገንቦ የሚሏት ዓይነት። አበራሽን የጠየቀ ወንድ በሌላ ጊዜ ትሩፋትን ሲያይ ይገለበጥና እሷን ማሰቡ የተለመደ ነገር ነበር። አበራሽ ታድያ

«ማ-ይሙት አሁን አንቺ ከማን የበለጠ ቆንጆ ሆነሽ ነው? እኔን ጠይቶ አንቺን መመኘቱ? እንዴው ተወደጂ ሲልሽ ቀዩን ጭቃ ቀብቶሽ ነው እንጂ-- ተሰፋዬ ይሙት አፍንጫ እንኳ የእኔን ያክል የለሽም» ትላንትና በወንዶቹ ግብዝነት ይሳሳቃሉ። ፍቅሩ ቀጠለ::

«ለአቅመ አዳም ከደረስኩ ጀምሮ በሴት ላይ ሴት እያማረጥኩ ከልቤ ፍቄ ላወጣሽ ሞክርኩ:: የፈረንጅ ሴት እንኳ አልቀረችኝም።» ብሎ አይታውን ከአሷ ላይ አንስቶ አይኖቹን በዘዝ አድርጎ እንሸ እልሾ ላይ ለቀቃቸው:: ዝም ብሎ ቆይቶ ከሱ የወጣ በማይመስል ሩ----ቅ ድምጽ ንግግሩን ቀጠለ::

«ከሁሉም ትዝ የምትለኝ በተለይ ርቻል የምትባለዋ አሜሪካዊት ሴት ናት። ባህርዳርንና አካባቢዋን እንዳስጎበኛት የቀጠረችኝ ነጭ:: ከአስጎብኝና ጎብኝ ባለፈ ተወዳጀን:: ጥሎባት በምንም የማልመጥናትን ሰው ደርሳ ልጥፍ አለችብኝ። በእውነቱ ጥሩ የፍቅር ጊዜ አሳልፈን ነበር» ብሎ ፈገግ አለ:: አንገቱን ደፋ አድርጎ ግንባሩን በእጁ አሻሸ:: ትሩፋት በፀጥታ ታዳምጣለች የአበራሽን መመለሻ ጊዜ በናፍቆት ትጠብቃለች::

«አግብታ ልትወስደኝ ያላደረገችው ጥረት አልነበረም:: ቤተሰቦቿ ጥቁር እንድታገባ ፈቃደኞች ባይሆኑም እንኳ እሷ ለፍቅር እንጂ ለቀለም ግድ እንደ ሌላት ደጋግማ ትነግረኝ

ነበር:: ትምህርት ለመማር የተሻለ ዕድል እንደሚኖረኝ፤ ጥሩ ጥሩ ልጆች ወልደን የደስታ ኑሮ መኖር እንደምንችል እየገለጸች ልታግባባኝ ብዙ ጣረች:: ይሄ ጥሩ አጋጣሚ እንዳያልፈኝ ለመነችኝ፤ ተማጸነችኝ» አለ በፀፀት ::

«ቢደፈናው አገሬን ለቅቄ መሄድ እንደማልፈልግ ገለጽኩላት። ዛሬ እኔ ላንቺ እንደማነባው እንብታ ተለየችኝ። ባልተጠቀምኩበት እድሌም እዘነችልኝ» አለ:: አውራ ጣቱን ከአገጩ ስር ጠቋሚ አጣቱን ደግሞ ጉንጩ ላይ አሳርፎ በትካዜ ወደ ውጭ እየተመለከተ::

«ስትለየኝ ምን እንዳለችኝ ታውቂያለሽ?» ብሎ ትኩር ብሎ ተመለከታት:: ዐይኖቻቸው ተጋጩ:: ቶሎ ዐይኗን ሰበረች::

«'አንተ ገና ጥሬ ነህ:: አልበሰልክም:: ዓለም ምን ያህል ሰፊና ውብ እንደ ሆነች አታውቅም:: የአንተ ዓለም ይቺ ያላደገችና ያልሰለጠነች ጠባቧና ትንሿ ኢትዮጵያ ብቻ ናት:: አብረኸኝ ለመሄድ ብትፈቅድ ኖሮ ብዙ-- ብዙ አገር አብረን የማየት እድል ይኖርህ ነበር:: እርግጠኛ ነኝ ይሄን አጋጣሚ መቼም ቢሆን አታገኘውም:: ጅል ስለሆንክ ግን የምልህ ሁሉ አይገባህም:: ደንዝዘሃል፤ ተኝተሀል:: አንድ ቀን ከእንቅልፍህ ስትነቃ አሁን የምነግርህ ሁሉ ትክክል መሆኑን ትገነዘባለህ::ያኔ ደግሞ ጊዜው አልፏል:: ትርፉ ፀፀት ብቻ ይሆናል:: አድሜ ልክህን በፀፀት አለንጋ ስትገረፍ ትኖራለህ በቃ!' ነበር ያለችኝ» አለ በሀዘን:: «አውነት ግን ያኔ ሄጄ ቢሆን ኖሮ ትሩፋትን ከልቤ ፍቄ ማውጣት እችል ነበር ይሆን?» ሲል በውስጡ ራሱን ጠየቀ:: መልስ አላገኘም::

«ትክክል ነበረች ሪቻል:: ሲፈቀር ማፍቀር ያልቻለ--- ሳይፈቀር ሙሉ ልቡን አስረክቦ ስቃይ ላይ የወደቀ--- በአንድ አጅ እያጨበጨበ ለሚ ያጣ:: ብኩንና ከርታታ ሰው ማለት እኔ ነኝ!» አለ:: ሲጋራዉን ምጥጥ አድርጎ ሳበና ጢሱን በረጅሙ አስወጣው:: ትሩፋትን ደግሞ የሲጋራው ሽታ ከጭንቀቷ ላይ ተጨምሮ የባሰ ብጥብጥ አደረጋት:: ፍቅሩ ዛሬ ሐሺሽ ለመውሰዱ አልተጠራጠረችም። ታሪክ እሳከቶ ሲተርከና እንዲህ እንደ ዛሬው ብዙ ሲያወራ ሰምታው አታውቅም። የምታደርገው ግራ ግብት አላት:: ዝም ብላ የሚሆነውን በፍርሃት ትጠባበቅ ጀመር።

የአስመራ ሰው ደግሞ «ከቤትህ አትዋል» የተባለ ይመስል በጧት የወጣ በሌሊት ይገባል። ሴቶቹም ቢሆኑ የሚጠይቁት ዘመድ አያጡም። የቤት ውስጥ ስራቸውን የሚያጠናቅቁት ሌሊት ነው። ጧት ሲነሱ የልብስ ማስጫ ገመዱ ሁሉ ሲታጠብ ባደረ ልብስ ጨረቃ መስሎ ይገኛል። በሌሊት ወጣቸውን ይሰራሉ:: በሌሊት አንጀራቸውን ይጋግራሉ። መቼ እንደሚተኙ እግዜር ይወቅ። ብቻ ፀሐይ ብልጭ ስትል ቤት ያፈራውን ቀማምሰው ሴት ወንዱ ውልቅ ነው። ሴቶቹ ሹርባቸው ላይ ጻአዳ ነጠላቸዉን ጣል አድርገው-- እንሶስላ በሞቀ እግራቸው ላይ ሰንደል ጫማቸውን ሰካ አድርገው--ጻአዳ ሆነው--ጻአዳ ለብሰው-- በጻአዳዋ አስመራ ቀጭ ቀጧ ሲሉ ውለው የማታ ማታ እቤታቸው ይገባሉ። ከትሩፋትና





ከፍቅሩ በስተቀር ግቢው ውስጥ ለምስክር ሰው የለም:: እሷ ከአበራሽ አልጋ ላይ---ፍቅሩ ከእሷ አልጋ ላይ ፊት ለፊት ተፋጠው ተቀምጠዋል። ብትፈራ ተፈርዶባት ነው? አበራሽን የበላ ጅብ ደግሞ አልጮህ አለ። ቶሎ እንድትመጣላት ያልተሳለችለት ታቦት የለም።

ፍቅሩ ድንገት አንድ ቦርሳ ከኪሱ አወጣ። ትሩፋት ሲጋራ የሚያወጣ መስሏት ነበር። ቦርሳው ውስጥ ካሉት ፎቶግራፎች መርጦ አንዱን ሰጣት። ባለ ቀለም ፎቶግራፍ ነው:: አየችው። ጥቁር ሀር የመሰለ ጸጉር ጀርባዋ ላይ ተኝቷል። ደስ የሚል ጥቁር ሰማያዊ ዐይን አላት:: ሲያይዋት የደስ ደስ ያላት ለግላጋ ወጣት ናት። ፎቶዋን አይታ እሷ እንኳን ወዳታለች።

«ይቺ ነበረች» አላት በትካዜ። «ነጮች ለፍቅር ስስ ልብ አላቸው። ስሜታቸውን አይደብቁም። ሳይሳሱ ይለጣሉ። የሚሰጣቸውንም ከልብ አመስግነው ይቀበላሉ። እንደ እኛ የጠቆረ እለት ልብ የላቸውም። በተለይ ደግሞ እንደ አንቺ!» አላት ጠቋሚ ጣቱን ቀስሮባት:: ምንም መልስ አልሰጠችውም:: ፎቶግራፉን ከእጇ ላይ ወሰደው። አይቶት እንደማያውቅ ሁሉ ትኩር ብሎ በተመስጦ ተመለከተው።

«ተስፋ የሌለው ነገር» ሲል ሰማችው። ከኪሱ ውስጥ ክብሪት አውጥቶ ጫረ። ሲጋራ ሊለኩስ መሰሏት ነበር:: እሱ ግን ፎቶግራፉን አቀጣጠለው:: ትሩፋት ሽምቅቅ አለች። ልታስጥለው ፈልጋ እጇን ዘርግታ መልሳ ሰበሰበች። ነበልባሉን በትካዜ እየተመለከተ እንባው መንታ መንታ እየሆነ ይወርድ ጀመር። ነበልባሉ እልቆ አመድ ሲሆን በረጅሙ ተነፈሰ። ከተቀመጠበት ከትሩፋት አልጋ ላይ ወደ ኋሰው ሰጠጥ ብሎ ግድግዳውን ተደገፈ:: ፊቱን በሁለት እጆቹ ሸፍኖ ዝም አለ። ትሩፋት አሁንም በጸጥታ ለቅሰውን እንደ ቀጠለ ገብቷታል።

«ምነው እምላኬ ለሁለታችንም የሚበጀንን ነገር ብትገልጽልን። እኔ የአናቴ አደራ አለብኝ። ከዓላማዩ እንድሰናከል ፈቃድህ አይሁን አባከህ ...» በልቧ የምታነበንበውን ጸሎት አልጨረሰችም::

«የደሃ ልጅ ነኝ» የተከፋው ድምጹ ጸሎቷን አቋረጠው። ከእንቅልፉ ድንገት እንደ ነቃ ሰው ብንን ብላ ተመለከተችው። ትናንሽ ዐይኖቹ ድብልቅልቅ ብለው ቀልተዋል::

«አንቺም ታውቂያለሽ። ግን ከምታውቂውና ከምትገምችው በላይ ነጭ ድሀ:: ከሚበላበት ቀን ጦም የሚታደርበት ከበዛበት ቤተ-ሰብ ውስጥ የወጣሁ ነኝ። ከአብናት ከተማ ወረድ ብሎ ወደ ቆላው በምትገኝ ትንሽ የገጠር መንደር ውስጥ ሰባት ሆነን እንኖር ነበር። ያ ኑሮ-- - መኖር ከተባለ::» ትናንሽ ዐይኖቹን አጥብቦ ከጠባቧ ከፍል ውጭ ላካቸው። የትልቁ ግቢ ግንብ አጥር ተቀበለው። ሐሳቡ ግን ርቆ ሄዷል። ከግንቡ አጥር ወዲያ ማዶ---

ከአስመራ እድማስ ማዶ--- ብ—ዙ በጣም ብ—ዙ ኪሎ ሜትሮች ር--ቆ:: ዐይኑን በዘዝ አድርጎ በሕሊናው ርቆ አንደ ሄደ መተረኩን ቀጠለ::

«ለቤተሰቦቼ አራተኛ ልጅ ነኝ። ከኔ በታች ሁለት አሉ። አባታችን የሞተው ለስራ ያልደረስን 'እህል እህል' የምንል ስድስት ህጻናት ለእናቴ ትቶላት ነበር። ድንበርተኛ ገበሬዎች ሁሉ ደግሞ ሁነኛ ሰው ስላጡባት መሬቷን እየገፉ እየገፉ ወሲደውባት የቀረቻት የበሬ ግንባር የምታክል መሬት ብቻ ነበረች። ለማን አቤት ትበል? ደግሞስ ማን ሊሰማት? ሰው የላት--ገንዘብ የላት:: ስድስት ሕጻናት የሙት ልጆችን ይዛ የት ትሂድ? ግራ ግብት ብሏት የተረፈቻትን ቁራሽ መሬት ይዛ ዝም ብላ ተቀመጠች። ሲገኝ እየበላን ሲታጣ ጦም እያደርን» ብሎ ትክዝ አለ:: ትሩፋት ፍቅሩ ከድሀ ቤተሰብ የመጣ መሆኑን ታውቃለች:: እሷ ብቻ ሳትሆን ድፍን የአዲስ ዘመን ተማሪ ሁሉ ያውቃል:: በአርዳታ መማሩ አየታወቀ ይህን ማን ይስተዋል? ታሪኩን ሲተርክላት ግን አንደ አዲስ አሳዘናት:: ጎስቋላ እናቱ በዓይነ-ሕሊናዋ ታዩዋት:: ዐይኗን ቆጠቆጣት::

«ይበልጥ የሚያሳዝነው ደግሞ የአካባቢው ምሰለኔና ጭቃ ሹም ለዚያች የበሬ ግንባር ለምታክል መሬት ግብር የጣሉባት ያላቅሟ ነበር:: ይባስ ብለው ለረባውም ላረባውም ሥራ በመጡ ቁጥር በሌለ ቤቷ ያገኙትን ሁሉ በጭካኔ አዳፍተው አሟጠው በልተውና ጠጥተው ሲሄዱ እግዚአብሔርን እንኳ አይፈሩም ነበር:: መጡ በተባለ ቁጥር የምትደነግጠው ድንጋጤና ፍርሀቷ አንኳን በሕይወት እያለሁ ሞቼም አጥንቴ የሚረሳው አይመስለኝም» አለ ገጽታው ኩምትርትር ብሎ:: ትንፋሽ ወስዶ ንግግሩን ቀጠለ::

«ይገርምሻል እናታችን ጠንካራ ሴት ነበረች። የቤተሰቡን ጉሮሮ ለመድፈን ቀን ከሌት ደፋ ቀና ጎትል ትውላለች። ሰማይና ምድር ሲላቀቅ የተነሳች ስትማስን ውላ ምሽቱን አንኳ አታርፍም ነበር። ጨለማው ደግሞ የራሱን ሥራ ይዞላት ይመጣል:: ምድጃው ላይ እሳቷን ፏ! አድርጋ አንድዳ ስትፈትል ሌሊቱን ታጋምሰዋለች። ለነገ ሽያጭ በሚውል ልቃቂት አገልግሏን መሙላት ይኖርባታል:: ልጅ ለማሳደግ ያለ እድሜዋ አርጅታ፤ ያለእድሜዋ ጎብጣ ያለመልኳ መልክ አውጥታ የወንዱንም የሴቱንም ሥራ ታከናውናለች። ምስኪን! የምታሳዝን ባተሌ ብቸኛ ሴት::» እንባው በዐይኑ ሙልት ሲልበት እንደ ምንም ታግሎ ኮሰል ብሎ ከመውረዱ በፊት ዋጥ አደረገው:: ትሩፋትም እንባዋ አየታገላት ነው:: አልቃሻ ባትሆንም የሚያሳዝን ነገር ስትሰማ ወይም ስታይ ግን ልቧ አይችልም:: አሳዛኙ የፍቅሩ ትረካ ደግሞ ገና አላለቀም::

«አንድ እሁድ ቀን የነብስ አባቷ ቄስ ገብረማርያም መጡ። የፈረደባት እናቴ በሌላት አቅም ቤት ያፈራውን ለማቀራርብ ጉድ ጉድ ማለት ጀመረች። ቡና ለማፍላት እቃ ስታቀራርብ .





'ወለተማርያም በሰንበት ቀን የተወቀጠ ቡን አልጠጣም ልጄ:: ተይው አትቸገሪ' አሏት:: ነጭ ጭራቸውን አየነሰነሱና በሌላኛው እጃቸው ደግሞ ቁልል የሻሸ ጥምጥማቸውን እያስተካከሉ።

'እረገኝ አባቴ ተዘንግቶዎ እንደሆነ ነው እንጂ እኔም እኮ በሰንበት የተወገጠ ቡን አልጠጣም። አንኳን ቡን ውሃውንም ቢሆን አርብ አርብ ነው የምቀዳው:: በውሃ ጥም የምሞት ቢሆን እንኳ በሰንበት ቀን የተቀዳ ተሆነ አልቀምሰም:: ከአንግዲህ ለየትኛው ዓለም ብዬ:: ለነዚሁ የሙት ልጆች ስል ነው እንጂ እኔስ የዚች ከንቱ ዓለም ነገር በቅቶኛል አባቴ:: መልኩሼ ከአንዱ ገዳም ብገባ ፈቃዴ ነበር' አለች::

'እረ ገና ነሽ! ለምንኩስናውስ ገና አልደረሽም ልጄ! ብቻሽን ልጅ አሳዳጊ ሆነሽ ቀድመሽ በለተትሽ እንጂ እድሜሽማ የቱን ያህል ይሆን ብለሽ? የሆነው ሆኖ ደህናውን መንገድ ይዘሽዋል ልጄ። እንደእውነቱ ከሆነማ የዚች ከንቱና ቀሪ ዓለም ነገር ምን ይበጅ ብለሽው:: ድንግል ውላዲተ አምላክ የልጅን ነገር ታውቀዋለችና ልፋትሽን ትቁጠርልሽ:: እነዚህን ያለ አባት ብቻሽን የደከምሽባቸውን ልጆችሽን አሳድጋ ለፍሬ ታብቃልሽ':: ምርቃን ቸሯት ቄስ ገብረማርያም:: 'አሜን' አለች እናቴ ከወገቧ ዝቅ ብላ። ቡናው ደርሶ ወርዶ እየሰከነ ነው፤ ቁርሱ ቀርቦ ጨዋታው ደርቷል።

'እንዴው አባቴ ዛሬ ህልም አይሉት ቅዠት በውል ያልተለየኝ ቀጥቃጤ ሲያባክነኝ ነው ያደረ' አለች እናቴ በሌሊቱ ህልሟ ቅሬታ ገብቷት:: ከቄሱ አንዳች መፍትሄ በመሻት።

'እግዚአብሔር ከሰው ጋር መገናኛ መንገዱ ብዙ ነው:: ዋናው ደሞ ህልም ነው:: ማስተዋል አየተሳነን ነው እንጂ እሱ ፈጣሪያችን ከፉም ሆነ ደግ ህልም ሳያሳልም በፍጡሩ ላይ አንዳች ነገር አይፈጽምም። ለመሆኑ ህልሙ ምንድን ኑሯል?'አሉ ቄስ ገብረማርያም::

'ህልም መፍታት ይችላሉ አባቴ?' አለች አንገቷን ወደ ቄሱ ዘንበል ዐይኗን ቀና አድርጋ። በትህትናና በጉጉት::

'መቼስ ምን ይጠፋ ብለሽው:: አሁንም የሆነ እንደ ሆነ ህልም እንደ ፈቹው ነው። ሆነም ቀረ እስቲ እንስማው' አሉ ቄስ ገብረማርያም:: እናቴ አቀማመጥዋን አስተካከላ ዐይኗን በዘዝ አድርጋ በበሩ ወደ ውጭ በረጅሙ ላከቻቸው:: ሕልሟን ለቄሱ ስትነግራቸው ሁሉ በሌሊቱ ስሜት ውስጥ ያለች ትመስል ነበር::

'በዚችው ደሳሳ ጎጆ ውስጥ ሰባታችንም ያለን ይመስለኛል' አለች እናቴ። ህልሙን ለቄስ ገብረማርያም ስትጀምር:: 'እኔና አምስቱ ልጆች መደብ ላይ ተኝተናል:: ፍቅሩ ግን ለብቻዉ አልጋ ላይ ተኝቶ ይመስለኛል። የዚያ አልጋ በዚች ደሳሳ ጎጆ ውስጥ መገኘት ሲገርመኝ ወተት የመሰለ ነጭ ጋቢ ደሞ ለብሷል። የጋቢዉ ንጣት አሁንም ዐይኔ ላይ አለ' አለች ዐይኗን ጠበብ አድርጋ ከፊት ዘጋ አያደረገች።

‹የህልምሽ አጀማመር ጥሩ ይመስላል እስቲ ጨርሽው› አሉ ቄሱ፡፡ አየሩን በነጭ ጭራቸዉ እየመቱ፡፡

‹የእኛ ያልሆነ ጋቢና አልጋ ከየት እንዳገኘ ልጠይቀው ሰል ፍቅሩ ፍቅሩ የሚል የሴት ድምጥ ጥሪ እሰማ የመሰለኛል። የበራ ፋኑስ በጇ እንጠልጥላ ይዛለች፡፡ መልኳን ግን በውል አጥርቼ ማየት አልተቻለኝም፡፡ በፋኑሱ የብርሃን ውጋገን ትንሽ ትንሽ እንዳየኋት ግን ቀይ መልከ መልካም ልጅ እግር ሴት ትመስለኛለች።' ብላ ትከዝ አለች፡፡

'ማለፊያ ነው' አሉ ቄሱ፡፡

'ፍቅሩ ጥሪዋን ሲሰማ ይነቃ ይመስለኛል፡፡ በዚህ በደረቀ ለሊት የማን ሴት ናት ልጄን የምትጠራው? ብዬ ለማጣራት ወደ እሷው አትኩሬ ተመለከትኩ፡፡ ልትከሰትልኝ ግን አልቻለችም፡፡ ፍቅሩ ከአልጋው ላይ ተነስቶ ያን ነጭ ጋቢ አጣፍቶ እንደ ለበሰ ወደ እሷው የሄደ ይመስለኛል፡፡ በዚያ ዐይን ቢወጉ በማይታይ ጨለማ ከምኝታዬ ለመነሳት ገና ስንደፋደፍ እሷ በፋኑሱ ብርሃን እየመራችው እሱ እየተከተላት እየራቁ --እየራቁ ከዐይኔ ተሰወሩ' አለች በቅሬታ፡፡ ዐይኗን በበሩ ልካ አሻግራ ሩ---ቅ እየተመለከተች፡፡

'በጄ! የህልሙ መጨረሻ ዛዲያ ምን ሆነ?' አሏት፡፡ ርቃ ከሄደችበት ሐሳቧ ሊመልሷት አሰበው፡፡

'የማላውቃትን ሴት ተከትሎ መሄዱ አስደንግጦኝ እንደ ምንም ተነስቼ በጨለማው ውስጥ ልጠራው ስሞክር ድምጤ ይሰልና አልሰማ ይለኛል፡፡ ለመሮጥ ስሞክር ጉልበቴ ይብረከረካል፡፡ የጭንቀቴን እየወደኩ እየተነሳሁ ለመከተል ሞከርኩ፡፡ ዛድያ ምን ያደርጋል? በዜት በኩል እንደ ኸዱ ደብዛቸው ይጠፋብኛል፡፡ በዚያ ጨለማ የት ብዬ ልፈልገው? መኸጃው ጠፍቶኝ ሰንበጃበጅ ሳላገኘው ብንን አልኩኝ' ብላ ሰትነግራቸው በውኗም ተጨንቃ ነበር፡፡ ቄሰ ገብረማርያምም ጆሮ ሰጥተው ካዳመጧት በኋላ ለማጽናናት ይሁን ወይ ከልባቸው አላውቅም

‹ኧረ አይዞሽ ! እሁንም የሆነ እንደ ሆነ ማለፊያ ህልም ነው፡፡ ይህን ያህል የሚያሳስብ አይደለም› አሏት፡፡

'እንዴው የቤታችን በጨለማ መዋጥና የሴትዮዋ አለመከሰት--- ፍቅሩ ደም ወጥቶ መቅረቱ......' ብላ ዘወር ስትል እኔ ቁጭ ብያለሁ፡፡ የትልቅ ሰው ጨዋታ እያዳመጥኩ መሆኔን እውቃ እንዳትቆጣኝ ምንም ያልሰማሁ መስዬ አንገቴን ደፋሁ፡፡

'አንተ ኸድ ውጣ ደጅ ከወንድሞችህ ጋር ተጫወት፡፡ ተዚህ ተትልቅ ሰው ጋር ምን ትሰራለህ?' አለችኝ፡፡ እኔ ግን የህልሙ መጨረሻና ትርጉሙ አጓጉቶኝ ሰለነበር ቶሎ አልወጣሁም ነበር፡፡ ሰምቼ እንዳልሰማሁ ሆኜ እዚያው እቤት ውሰጥ ዝም እልኩ፡፡





እሷም ትኩረቷ ሁሉ ህልሙ ላይ ስለ ነበር ፊቷን ወደ ቄሱ መልሳ 'ተያ ወድያማ እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር እንዲሁ እንዳፈጠጥኩ ነጋልኝ፡፡ ለነገሩ ወፍ ሳይንጫጫ ተነስቼ ከሰው ጋር ሳልነጋገር ህልም እልም---ህልም እልም እያልኩ ሦስት ጊዜ በእጄ መሬት መትቻለሁ' አለች፡፡ ጭንቀቷን ማቃለያ መንገድ መፈለጓ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ቄስ ገብረማርያ እግዜር ይስጣቸው፤ ነገሬ ብለው በጽሞና ነበር ያዳመጧት። የተከፋን ሰው ብሶት ጊዜ ሰጥቶ ማዳመጥ ግማሽ ህክምና ነው ይባል የለ፡፡ በኋላም ያችኑ ነጭ ችራቸውን ግራ ቀኝ ያሰውን አየር እየመቱባትና በአንደኛው እጃቸው እየላጓት ረጋ ብለው

'ማለፊያ ህልም ነው ልጄ። አሁንም የሆነ እንደ ሆነ ዋናው ሚሥጢር ያለው አልጋውና ጋቢው ላይ ነው። የፍቅሩ ነጭ ጋቢ ለብሶ አልጋ ላይ መተኛቱ ነው መልእክቱ። አልጋ ትልቅ ደረጃን– ስልጣንን ያመለክታል። ነጩ ጋቢ ደግሞ ፀጋ ነው፤ ሀብት ነው። ይኸ ልጅ ከልጆችሽ ሁሉ እንጀራና ሀብት ያለው ሳይሆን አይቀርም። የፋንሱ ብርሀንም እውቀትን ትምህርትን ይጠቁማል። ልጅ እግሯ ሴትም 'ቀይ ናት' ብለሽም አይደል?'

'በመብራቱ ወጋገን እንዳየኋት ቀይ ትመስለኛለች' አለች ከሰጋቷ ሳትወጣ፡፡ ከቄሱ አንዳች በጎ ነገር ለመስማት እየጓጓች፡፡

'እሷ የእመቤታችን የድንግል ማርያም ተምሳሌት ናት፡፡ እመቤታችን እኮ ቀይ መልከ መልካም ሴት ናት፡፡ በውል ያልተከሰተችልሽ የጻድቅነቷ ከብር-- የግርማዋ ኃያልነት ነው፡፡ እንደ ተራው ሰው ቁልጭ ብላ አትታይሽም፡፡ መለኮታዊ ከብሯ ይጋርዳታል፡፡ አትሰጊ እሷ አመብርሃን ናት የመራችው፡፡ የፋንሱ ብርሀን ተቤታችሁ ደርሶ ቢሆን ኖሮ ደሞ የበለጠ መልካም ይሆን ነበር፡፡ ማለፊያ ህልም ነው፡፡ ቁልጭ አድርጎ ነው ያሳየሽ 'አሉ፡፡ ቀዝቀዝ እንዲል ያስቀመጡትን የቡና ስኒ ብድግ እያደረጉ፡፡ እናቴ ሙሉ በሙሉ ስጋቷ ባይለቃትም

'አስቲ እንዳፊዎ ያድርግልኝ አባቴ' አለች ሦስተኛውን ቡና ምድጃው ላይ እየጣደች፡፡

'እስቲ ይህን ፍቅሩ የምትይውን ልጅ ከመርጌታ ላቀው ውሰጅውና ፊደል ይቁጠር፤ ዳዊት ይድገም። የልጅና የጢስ መውጫው አይታወቅም። ምናልባት ከአንችም አልፎ ወገን የሚያኮራ አገር የሚያስጠራ ቄስ፣ አቡን፣ ጳጳስ ይሆን ይሆናል' ብለው በተሰፋ አጥለቀለቋት። በቄስ ገብረማርያም ተደፋፍራ መርጌታ ላቀው ፊደል እንዲያስቆጥሩኝ ስትወሰደኝ ውላ አላደረችም። እኔም አላሳፈርኳትም። እሳት የላስኩ ተማሪ ሆንኩ፡፡ መርጌታ ላቀው እንኳ እያያዜን አይተው ደጋግመው

'ፍቅሩ ብሩህ አዕምሮ አለህ ተግተህ ተማር ልጄ! ትልቅ ሊቅ ይወጣሃል' የሉኝ ነበር። እኔ ግን ከመንግሥት ትምህርት ቤት ገብቼ ያስኳላ ተማሪ መባል በጣም እመኝ ነበር። ያን ጊዜ በእኛ መንደር የመንግሥት ትምህርት ቤት ገና መከፈቱ ነበር፡፡ አንድ ዘበኛና አንድ አስተማሪ ብቻ ነበሩት፡፡ የአስኳላ ተማሪ መሆን የተለየ ሰው የሚያደርግ እየመሰለኝ በጣም

እጓጓ ነበር:: በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ጎረቤታችን ከሆነው አስተማሪ ቤት ያጠመደ አያጣኝም ነበር:: መምህር ከፍሌ ይባላል:: በጣም ጥሩ ሰው ነበር:: ከእኔም ጋር ስንግባባና ስንለማመድ ጊዜ አልወሰደብንም:: እላላከዋለሁ፤ ልብሱን አጥባለሁ፤ ቤት አጸዳለታለሁ--- ምን አለፋሽ ያዘዘኝን ሁሉ በደስታ ነበር የማከናውንለት። እብናት ድረስ እየሄድኩ የቤት አስቤዛውን ሁሉ እገዛለት ነበር:: አንድ ቀን ሻይ በዳቦ መከሰስ ነገር እየበላን 'ፍቅሩ መንግሥት ትምህርት ቤት ብትገባ ይሻልሃል። የመሪጌታ ትምህርት ብዙም አይጠቅምህም። ለምሳሌ እንግሊዘኛና ሂሳብ ማወቅ አትችልም።' አለኝ::

«ደብተርና እስክርቢቶ ማን የገዛልኛል እንጂ እኔማ በጣም እፈልግ ነበር» አልኩ ያስኳላ ተማሪ መሆን እያጓጓኝ። 'ዘንድሮ የመመዝገቢያ ጊዜው አልፏል። ከርሞ ከእኔ ጋራ ሆነህ ትማራለህ' ሲለኝ ተንደርድሬ ጫማውን ልስም ሰል ቶሎ በእጁ ቀለብ አደረገኝ። ከልቤ ተደሰትኩ። ለቤተሰቦቼ ስነግራቸው ሁሉም እንደኔ ተደሰቱ። እናቴማ ከመደሰቷ የተነሳ 'አይ! አንተ ፍጡርህን የማትረሳ እምላክ! እውነት አልዘነጋኸኝማ!' ብላ መሬት ስትስም ትዝ ይለኛል።

መምህር ከፍሌ ቃሉን አላጠፋም:: በሚቀጥለው ዓመት ትምህርት እንድጀምር አደረገ:: ዓመቱ አልቆ ወደ እብናት ተዛዉሮ ሲሄድም አልተወኝም:: እብናት ይዞኝ ገባ:: እኔም አላሳፈርኩትም:: በዓመት ሁለት ጊዜ የማለፍ እድል እያገኘሁ ገሰገስኩ። በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ ችግር ተፈጠረ። መምህር ከፍሌ ወደ አዲስ ዘመን ተዛወረ። ጨነቀኝ:: እናቴም ትምህርቱ መቋረጡ ነው ብላ ሀሳብ ገባት። 'እናትህ ፈቃደኛ ከሆኑ ትምህርትህን አዲስ ዘመን እብረን ሄደን መቀጠል ትፈልጋለህ' ሲለኝ ጫማውን ብስም በወደድኩ ነበር:: ለጥ ብዬ እጅ ነሳሁ። ለእናቴ ከመምህር ከፍሌ ጋር አዲስ ዘመን ልገባ መሆኑን ስነግራት- ምንም ቅርታ አልገባትም፤ እንዴውም ቄስ ላቀው በፈቱላት መሰረት ህልሟ እውን የሆነ ነበር የመሰላት።

«ከመምህር ከፍሌ ጋር ሆኜ አዲስ ዘመን መማር ጀመርኩ:: መቀጠል ግን አልቻልኩም:: መምህር ከፍሌ ሚስት አገባ።እንዳለመታደል ሆኖ ሚስቱና እኔ ኮከባችን ሊገጥም አልቻለም። ያስደስታታል ብዬ የምሰራው ነገር ሁሉ አስቆጥቶ አራስ ነበር ያደርጋት ጀመር። እኔም ተጨነቅሁ:: መምህር ከፍሌም ተቸገረ:: አሁን አሁን ሲገባኝ ገጠር እያለ የወለደኝ ልጁ ሳልመስላት አልቀረሁም። መምህር ከፍሌ እኔን ይዞ ትዳሩን አይፈታ ነገር ምን ያድርግ? ምርጫ አልነበረውም። እብናት ተመልሼ ሄጄ እንድማር መከሮኝ-- ስንቅ የሚሆነኝ ገንዘብ ሰጥቶ አሰናበተኝ። በኋላም በአዲስ ዘመን ጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በተቋቋመው የእርዳታ ድርጅት ውስጥ እየተረዳሁ እንድማር ሁኔታዎችን ያመቻቸልኝ እሱ ነበር።

እብናት ተመልሼ ስሄድ ግን የድሮው ትንሹ ልጅ ፍቅሩ ብቻ አልነበርኩም። እንዴት እንደሆነ ባልውቅም በትንሿ ልቤ ውስጥ እንዲት ትንሽዬ ልጅ ተቀርጻ በታውን ሁሉ





ተቆጣጥራው ነበር። ባልተረዳሁት ምሥጢር ከእሷ መለየቴ እያስጨነቀኝና እያባባኝ ነበር ወደ እብናት የተመለስኩት። እውነት ነው የምልሽ ትሩፌ ከአንቺ መለየቴ ያሳዘነኝን ያህል የትምህርቴ መቋረጥ አላሳዘነኝም:: መምህር ከፍሌ ሲሸኘኝ እንባዬ እንደ ሀምሌ ዝናብ ሲወርድ ሲያይ በትምህርቴ መቋረጥና ከሱ በመለየቴ አዝኜ መስሎት እንዴት ተከፍቶ እንደ ነበር አልረሳውም። እንኳን እሱ እኔም ፍቅር መሆኑ የገባኝ ቆይቶ ነው። ያኔ እንደ ተለያየን በቀረሁ ኖሮ ጥሩ ነበር። አዲስ ዘመን ተመልሼ እንደ ገና ሳይሽ የአንቺ ነገር በእጥፉ አገረሸብኝ። ድሮም በአገራችን ከዋና በሽታ ይልቅ ለሞት የሚያደርሰው ግርሻ ነው ይባላል። ይኸው ፍቅርሽ እያደር እያገረሸ ሊገለኝ ተነስቷል» ብሎ እንባቱን ደፋ አደረገ::

«ተስፋ የጣለችብኝ እናቴ ዛሬ ልሙት ልዳን የምታውቀው ነገር የለም። እንቺን እፍቅሬ ከስር ስርሽ እየተከተልኩ እኔም እናቴም የጓጓንለት ትምህርት ውሃ በልቶት ቀረ:: እናቴን ከዳኋት--! ተስፋዋን ሁሉ ቀበርኩት! እንዲህ አውታታ ሆኜ መቅረቴን ብታውቅ ሀዘኗ ምን ያህል መሪር ይሆን? ታድያ እኔ መኖር ይገባኛል?» ብሎ ዝም አለ:: ትሩፋት ጨነቃት:: በእሷ አቅም ልትመክረውና ልታስረዳው የምትችለውን ሁሉ ነግራ ጨርሳለች:: ቅድሚያ ቤተሰቦቻቸውን ማሰብ እንደሚገባ ደጋግማ ነግራዋለች:: ከሁሉም በፊት ራሱን ተቆጣጥሮ ትምህርቱ ላይ እንዲያተኩር መክራዋለች:: እስተዛዝና ለምናዋለች:: አሁን ግን የፍቅሩ ነገር ደከሚታል:: ስልችቷታል:: ዝም ብላ ማዳመጥ ብቻ ሆኗል ምርጫዋ::

«ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ማን ይመስልሻል?» አለ ተስፋ በቆረጠ አስተያየት ተመለከታት። ሰምታ እንዳልሰማች ዝም አለችው። ኪሱን ፈትሾ ሲጋራ አወጣ፤ በአፉ ያዘው፤ ክብሪት ፍለጋ ኪሱን ይፈተሽ ገባ። ባዶ እጁን ያወጣል ያገባል። ከጥቂት ዝምታ በኋላ እንደገና

«ለጥያቄዬ እኮ መልስ አልሰጠሽኝም» አላት ሲጋራውን በአፉ እንደ ያዘ::

«እኔ እንዳልሆንኩ አውቃለሁ» አለችው ፈርጠም ብላ «በሞቴ— አፈር ስሆን— እፍቅረኝ ያልኩት አይመስልም፤ እንዲህ በጥያቄ ሲያፋጥጠኝ» አለች በውስጧ ደግሞ::

«ታድያ ማን ሊሆን ይችላል?» አፈጠጠባት።

«ምን አውቅልሃለሁ? ከልጅነቴ የጀመርከ የማንም መጠቋቆሚያ አድርገኸኝ ነው የኖርከው:: እኔስ ብሆን እንዲህ በየሄድኩበት እየተከተልክ መቆሚያ መቀመጫ ስታሳጣኝ በሰላም እየተማርኩ ይመስልሃል? በጓደኞቼ ፊት ሳይቀር መዘባበቻ ስታደርገኝ የማልሳቀቅ ይመስልሃል?» አለችው ቆጣ-- ደፈር ብላ። «አሁንስ እበዛው» አለች ለራሷ ።

«ለሁለታችንም ፈዋሽ መድሀኒት በማንም እጅ ላይ ሳይሆን በአንቺ እጅ ውስጥ ነው ያለው» አላት እንደ ልማዱ እረጋ ብሎ። ክብሪቱን ኪሱ ውስጥ ፈልጎ አወጣ፤ ሲጋራውን ለኮሰ፤ በከብ በክቡ ያቦነው ጀመር:

«እውነቱን ልንገርሽ ትሩፊ! ብትፈልጊ እብድም በሽተኛም በይኝ:: በእርግጠኝነት የማውቀውና ውስጤን የሚሰማኝ አንድ እውነት አለ:: በዚች ዓለም ላይ በሕይወት ካለሁ ያለአንቺ በጭራሽ መኖር አልችልም! አብረን በሕይወት እንድንኖር የማትፈቅጅ ከሆነ ደግሞ ግብአተ-መሬታችን አንድ ላይ ይሆናል! ይህንን አስረግጬ እነግርሻለሁ ትሩፋት» አላት ጠንከር አድርጎ::

«ፍቅሩ ብዙ ተነጋገርን አንድ መፍትሔ ላይ ግን አልደረስንም:: አሁን ገና ተማሪ መሆኔን ታውቃለህ:: በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ ምን እንዳደርግልህ ነው የምትፈልገው? ይህንን ብቻ ነው ማወቅ የምፈልገው። ምን ላድርግልህ? ምን ልሁንልህ?»

«ቃል ግቢልኝ»

«የምን ቃል? ምን ብዬ?"

«የሌላ የማንም እንደማትሆኚና እንደምታገቢኝ ቃል ግቢልኝ» አላት:: ዐይን ዐይኗን እያዬ::

«ወደፊት ልንጋባ ማለትህ ነው?» አለች ግራ ተጋብታ::

«አሁን--- በዚች ሰዓት ችለን ብንጋባማ ደስታውን አልችለውም ነበር-- አይሆንም እንጂ::»

«አባክህ አታሹፍ ፍቅሩ:: እኔ የቤተሰቦቼ ነገር ያስጨንቀኛል:: የአደራ ቃል አለብኝ:: አባክህ! እባክህ በፈጠረህ ልማርበት!» ስትለው እንባዋ መውረድ ጀምሮ ነበር::

«አታልቅሽ ትሩፋት! አታልቅሽ! በምወደው ገጽታሽ ላይ እንባ ሲወርድ ማየት ያስጨንቀኛል፤ ሆድ ይብሰኛል:: ስታለቅሽ ማየት አልችልም:: አንጀቴ ይላወሳል» ሲላት የአሱም የድምጽ ቃና ተቀያይሮ ነበር::

«ታድያ ምን ላድርግ? አስጨነቅኸኝ እኮ!» አለች እየተነፋረቀች::

«ቀላሉን ነገር እኮ ነው ያከበድሽው ትሩፊ:: ቃል ግቢልኝ እንደ አዳምና ሄዋን--እንደ አብርሃምና ሳራ ከሞት በቀር የሚለየን ሌላ ነገር ላይኖር:: በእግዚአብሔር ስም ቃል ኪዳን ግቢልኝ:: ለወደፊት ባልና ሚስት ሆነን ልንኖር መጽሐፍ ቅዱስ መተሽ ማይልኝ። ለሌላ ላትሆኝ-- ላትከጅኝ ቤተክርስቲያን ደጅ ቆመን በመሀላ አጽኚልኝ:: በቃ! ይኸው ነው:: ቃልሽን ብቻ ነው የጠየኩሽ:: ቃልሽን ብቻ ስጭኝ::

«መጽሐፍ ቅዱስ መትቼ!!» አለች ጮክ ብላ:: «ትሩፋቴ መፅሐፍ ቅዱስ አትዋሹ ይላል። እንዳትዋሽ። አትማሉ ይላል እንዳትምይ....» የአባባ መሳይ ምክር ትዝ አላት መጽሐፍ





ቅዱስ መጥቶ የመማሉን ነገር ሲታሰበው አሁን እንኳ የምትቀሰፍ መሰሏት ዝግንን አደረጋት::

ፍቅሩ ማንም ወንድ አንዲትን ሴት ከሚያፈቅረው በላይ እንደሚያፈቅራት ታውቃለች። ለእሷ ሲል የማይሆነው ነገር እንደማይኖር ትገነዘብለታለች:: አለከወዲያኛው እንደማይለወጥባት እርግጠኛ ናት:: የማታውቀው የራሷን ስሜት ነው።

«ሳላውቀው የማፍቀሪያ ጊዜዬ ተላልፎኝ ይሆን? ወይ ደግሞ በእናቴ ማሕፀን ስፈጠር አንድ የጎደለኝ ነገር ይኖር ይሆን?» ምንጊዜም ራሷን የምትጠይቀው ጥያቄ ነው:: ሩቅ ሳትሄድ አበራሽ እንኳን የወንድ ጓደኛ እንዳላት ታውቃለች። እሷ ግን ለፍቅሩም ሆነ ለማንም ወንድ ዓላማዋን የሚያስት የፍቅር ስሜት በውስጧ አድሮባት አያውቅም:: አንዳንዴ ታድያ የጤና አይመስላትም:: ጭራሽ ፍቅሩን እንደሚያደርገው አቅል አሳጥቶ እንዲህ ቅጥ ያጣ ነገርማ አልሞከራትም። እርግጥ ነው ከሰር ስሯ እየተከታተለ በሄደችበት ሁሉ ስለማታጣው ከሌሎች የከፍል ወንዶች ልጆች ሁሉ ለየት አድርጋ ፍቅሩን ማየቷ አልቀረም:: እርግጥ ነው ባየችው ቁርጥ ሰውነቷን ርብሽ የሚያደርጋት ስሜት እንደ ነበራት ይገባታል:: ይህ ሊሆን የቻለው ግን እሷ በተገኘችበት ቦታ ሁሉ እየተገኘ ስለሚከታታላት ይመስላታል። ከዓመታት በኋላ ዛሬም ሌላ የተለየ ስሜት አልተፈጠረባትም::

«ፍቅሩ ምናለበት እስከመረቅ ድረስ ብቻ ብትታገሰኝ። እግዚአብሔር አንድ ላይ እንድንኖር ፈቃዱ ከሆነ እኮ ባንማማልም አንድ ላይ መሆናችን አይቀርም። ምን አለበት ባታስጨንቀኝ?» አሳዝና ነበር የጠየቀችው::

«ከኮርሱ ጋር ምን ያገናኘዋል ትሩፋት? ዛሬ የመጨረሻ ውሳኔሽን መስማት አፈልጋለሁ:: አልፈልግህም የሚል ቃል ከአንቺ አንደበት ወጥቶ ላለመስማት ፈርቼ ስሸሽ ኖሬያለሁ:: አሁን ግን መሸሻ የለኝም:: ለብዙ ዓመታት በዝምታ እሰር እሰርሽ እየተከተልኩ ተንገላትቻለሁ:: የተጨበጠ ነገር ሳይኖረኝ በሕይወቴ መልሼ የማላገኛቸው ብዙ ነገሮች አምልጠውኛል:: ዛሬ ግን በቃኝ! በ---ቃ!» አለ በምሬት እየተንገሸገሸ:: በእጁ ይዟት የነበረችውን ቁራጭ ሲጋራ ወለሉ ላይ ጥሎ በእግሩ ደፈጠጣት። ለጥቂት ግዜ ዝም ዝም ተባብለው ሁለቱም በየግል ሐሳባቸዉ ነጎዱ። ያች ጠባብ ክፍል የዝምታ አዘቅት ዋጣት:: ይበልጥ ጠበበች።

«አንደ ምን ዋላችሁ?» የአበራሽ ድምጽ ነበር። ሁለቱም ከሀሳባቸዉ ባነኑ:: በፍቅሩ ፊት ላይ የመከፋት---በትሩፋት ገጽታ ላይ ደግሞ እፎይታ ተነበበ። አበራሽ ሁኔታቸውን አይታ ደንገጥ አለች። ጥቂት ቆይቶ ፍቅሩ ለመሄድ ተነሳ።

«ምነው ፍቅሩ? ተጫወት እንጂ:: እኔ ስመጣ ነው አንዴ የምትሄደው?» አለች አበራሽ ከአንገት በላይ::

«ትሩፋት ብቻዋን እንዳትሆን ብዬ ከአሁን -አሁን ትመጫለሽ እያልኩ ብዙ ቆየሁ። ሳይመሽብኝ ማደሪያዬን ላፈላልግ» ብሎ ሲሰናበታቸው ትሩፋትን ትኩር ብሎ ተመልከቷት ወጥቶ ሄደ። ማስጠንቀቂያው ገብቷታል። እንድታስብበት መሆኑ ነው።

«አንድ ነገር ብለሽ አታስናብቺውም። ልጁን እኮ አንከራተሽ በቁመናው ገደልሽው» አለች አበራሽ ትላልቅቅ አይኖቿን ጥላባት። ረዘም ስልክክ ያለው ጥይም ፊቷ ጠቆር ብሎ ታያት ለትሩፋት።

«ምን ብዬ እንደማሰናብተው ጨነቀኝ እኮ አበራሽ?»

«ምን ያስጨንቅሻል? ሳይቸግርሽ ነገር ማከበድ ትወጃለሽ እንጂ!»

«እስኪ በእናትሽ አበራሽ እንዴት ነው ነገር የማከብደው? አልፈልግህም-አልለው ነገር ከልጅነት አስከ አሁን ሲከተለኝ የኖረ ልጅ እንዲህ በዋዛ ይለቀኛል ብዬ የጅል ሐሳብ አላስብም። የዛሬ ሁኔታውን ብታይ ደግሞ አባባሌ ይበልጥ ይገባሽ ነበር። ባይገርምሽ ሲጋራ ሁሉ ለምዷል። እንደውም ያን ሐሺሽ የሚባል ነገር ሳያጨስ ሁሉ የቀረ አልመሰለኝም። እንደ ዛሬ ፈርቼው አላውቅም።»

«ለምን 'አልፈልግህም' ትይዋለሽ ትሩፌ?»

«አበራሽ ደግሞ ቀልደኛ ነሽ። ይልቅስ ከመፍራቴ የተነሳ ቶሎ አንቺን እንዲያመጣልኝ ያልተሳልኩለት ታቦት የለም።

«የምሬን ነው ትሩፋት አልቀለድኩም። ባይገርምሽ ፍቅሩን በተመለከተ እንደ ዛሬ ከአንጀቴ አውርቼሽ አላውቅም። ፍቅሩ ማንም ወንድ አንዲትን ሴት ከሚወደው በላይ ይወድሻል። የእሱ ዓይነት ፍቅር በፊልም ወይም በልብ ወለድ መጽሐፍ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በእውኑ ዓለም ታይቶ አይታወቅም። ፍቅሩ አንቺን ብሎ ከቦታ ቦታ እየተንከራተተ ከመንሳቆሉ በስተቀር ምን ይወጣለታል? በትምህርቱም ቢሆን ጎበዝ ተማሪ እንደ ነበር አንቺው ራስሽ ነግረሽኛል።»

«አላውቅም አበራሽ! የእኔንና የፍቅሩን ሁኔታ ለብዙ ቀን-- ለብዙ ሌሊት---ለብዙ ወር-- ለብዙ ዓመታት አስቤበታለሁ። ስለዚህ ልጅ ያለኝን ስሜት እንኳ በትክክል አላውቀውም። ልውደደው--ልጥላው--ወይም ደግሞ ፍቅር የሚባል ነገር ጨርሶ አይገባኝም ማለት ነው።»

«እውነቱን ልንገርሽ ትሩፋት? ፍቅሩ አይለቅሽም ያጠፋሻል! ልጁ በአንቺ ምክንያት ራሱን እየጠላ ነው። ሲጋራ ማጨስ መጀመሩ የምን ምልክት ይመስልሻል? ተስፋ የመቁረጥ። ተስፋ የቆረጠ ሰው ደግሞ ጨካኝ ነው።»





«ካልሽስ ዛሬ እሱንም ሲነግረኝ ነበር። ልቡ እልጨከን ብሎት እንጂ ብዙ ጊዜ ሲገለኝ ማሰቡን አልደበቀኝም።»

«አላልኩሽም ትሩፌ! አልነገርኩሽም! ፍቅሩ አንቺን ከሚያጣ ሕይወቱን አንድ ጊዜ አያደለም ሺህ ጊዜ ቢያጣ ይቀለዋል። እስካሁንም ዝም ያለሽ አውነትም መጨከን አቅቶት ሳይሆን አይቀርም። አትጠራጠሪ አንድ ቀን ግን ይጨክናል።»

«ታድያ ምን አድርጊ ነው የምትይኝ አበራሽ?»

«ሙቼም ሞትን ምርጫሽ አታደርጊም። ፍቅሩ በዓለም ላይ ያለ ነገሩን ሁሉ ለአንቺ ሲል አጥቷል። ከእንግዲህ ለየትኛው ኑሮውና ሕይወቱ የሚጨነቅ ይመስልሻል? ይልቅስ አጉል ድርቅና አያዋጣሽም። 'ዓላማዬ--የአደራ ቃል ምናምን...' የምትይውን ነገር የምታሳኪው ስትኖሪ ብቻ ነው። ታናናሾችሽን የምትወጃቸው ከሆነ መኖርሽ ያስፈልጋቸዋል።» አለቻት አበራሽ ከረር አድርጋ። የፍቅሩን ሁኔታ ካየች አንስቶ እጥፍቷት ይጠፋል አያለች ሁሌ ትሰጋለች።

«የጠየቀኝ ጥያቄ እኮ እንዲህ በዋዛ የሚመለስ አይደለም።»

«ምን ጠየቀሽ በሞቴ? 'አሁኑኑ እንጋባ' አለሽ? ወይስ 'አልጋ ላይ እንውጣ' አለሽ'?» አለች አበራሽ ችኩል ብላ።

«ው--ይ! አበራሽ ደግሞ፤ ከምኔው ሮጠሽ አልጋ ላይ ደረሰሽ?» አለቻት ትሩፋት። እልጋን በማሰቧ ገርሟት።

«ታድያ ምን ጠየቀሽ? ልሳምሽ አለሽ? የአንቺ ወግ አጥባቂነት እኮ ከነእማዬም ብሷል። እንኳን ጠይቆ ሳይጠይቅ ግመጡኝ ግመጡኝ የሚል የብርቱካን ፍንካች የመሰለ ከንፈር አለው። ምናለበት ቢስምሽ» አለች አበራሽ ንግግሯን በሳቅ አጅባ።

«ኧረ በፈጠረሽ አበራሽ! ደግሞ ቀስ በይ! ውጭ ላለ ሰው እኮ ይሰማል ጩኸትሽ።»

«ይልቅ ንገሪኝ ሆዴን አታስቆርጭኝ። ምን ጠይቆሽ ነው በሞቴ? ለመልሱ እንዲህ የተቸገርሽው?

«ስንት መልስ የሌለው ጥያቄ ሞልቶለት እሱ እንዳንቺ አልጋንም መሳሳምንም አላነሳም።» አለቻት ትሩፋት ለመስማት መጓጓቷን ስታውቅ ወሬ እያራዘመች፡

«አሁን ይኸ ሁሉ መሟዘዝ ምን የሚሉት ነው? ዝም ብለሽ የጠየቀሽን ነገር ብቻ አትነግሪኝም ይልቅ።»

«ወይኔ አበራሽ! እስከ ዛሬ እንዲህ ያለሽ ለወሬ ሞትኩ መሆንሽን በፍጹም አላውቅም ነበር፡፡» የመገረም ሳቅ ሳቀች ትሩፋት፡፡

«ኡህ በቃ! አትንገሪኝ! ለመስማት ሰጓጓ ጊዜ ነው እይደል አውቀሽ የምትሟዘዥው፡፡ ሙች ትሩፌ መሟዘዝ ደግሞ እንዴት እንደሚያስጠላብሽ ብታውቂ! እንደውም በቃ! ተይው አትንገሪኝ፤ ከዚህ በኋላ መስማት አልፈልግም፡፡ እማ---ማ ትሙት!» አለች አበራሽ የውሸት ቁጣ እየተቆጣች፡፡

«አንቺን ከሚከፋሽማ ለምን ኢትዮጵያ በመርፌ አትታረስም፡፡ ቃል እንድገባለት ነው የጠየቀኝ።»

«የምን ቃል?» ጠየቀች አበራሽ፡፡

«ቃል ነዋ! እገባሀለሁ የሚል ቃል፡፡ ወይም ቃልኪዳን ልበልሽ፡፡ ቃልኪዳን እንድገባለት ነው የጠዬቀኝ፡፡»

«እስቲ ሙች በይኝ! ጥያቄው ይሄ ብቻ ነበር በእናትሽ ትሩፋት!? ቃል-ኪዳን እንድትገቢለት ብቻ!?» ብላ እጇን ዘረጋችላት፡፡

«ሙች እበራሽ ቃልኪዳን እንድገባለት ብቻ ነው የጠየቀኝ» ብላ መሀል እጇን በትንሹ መታ አደረገቻት፡፡

«እማማ ትሙት! እንዴት ጨዋ ልጅ ነው። ለምስክር ሰው በሌለበት በዚህ በተዘጋ ግቢ--- በዚች ጠባብ ክፍል ውስጥ ሁለታችሁ ብቻ ተፋጣችሁ ስትውሉ ጥያቄው ቃል እንድትገቢለት ብቻ ነበር? ይገርማል!»

«እንዴ አበራሽ! ምን እንዲያደርግ ጠብቀሽ ነበር ታዲያ?» ጠየቀቻት ትሩፋት ግርም እያላት፡፡

«የፈለገውን ቢያደርግስ፡፡»

«እኮ ምን!?» ፡፡

«ማንም በሌለበት ጭር ባለ ግቢ -- ጸጥ ረጭ ባለ ቀን ብር እንባርሽን ቢሰብር ኡ!ኡ! ብትይ ማን ይደርስልሽ ነበር?»

«እ--ሃ! ገባኝ---ገባኝ! ለካ ብር እንባሬን ልታስብሪ ነበር ጠፍተሽ የዋልሽው!? እንዲህ ነው ጓደኛ አባክሽ !» አለች ትሩፋት ቅይም ብላ፡፡





«ወሬኛ! አብረን እንሂድ ብዬ ለምኜሽ አልነበረም? እምቢ! ብለሽ ቀርተሽ ያን ቀጥ ያለ የቪላጆ መንገድ ብቻዬን እንድሄድ አልፈረድሽብኝም! የከፋትሽን አይቶ ነው እግዜሩ ፍቅሩን ያዘዘብሽ! ይልቅስ እሺ የምትኝ ከሆነ የጓደኝነቴን ልምከርሽ ቃል ኪዳን እንድትገቢለት ከሆነ የጠየቀሽ ለምን ቃል አትገቢለትም? ለወደፊቱ እንጂ አሁን አያገባሽ፡፡ ምኑ ነው ያስፈራሽ? ልብሽ እስኪትጠፋ ቢሰምሽ እኮ እንቺው ትለምኚው ነበር። 'የሴት ልብ ሩብ ግራም ቅቤ ታክላለች ሲስሟት ትቀልጣለች' የተባለውን አልሰማሽም? ኤዲያ! እሱም አላወቀበትም» አለች አበራሽ፡፡

«ዛሬ አንቺ ልጅ የጤናሽ አይደለም! ለምን አትመክሪውም ነበር ታድያ!»

«እውነት! ትሩፋት ሙች! ፈርቸሽ እንጂ ብመከረው እንዴት ደስ ባለኝ ነበር። በጣም ነው የሚያሳዝነኝ፡፡ እባክሽ ቃል ግቢለትና ልጁ ሕይወቱን ያስተካክል።»

«እሱ የጠየቀው ዝም ብሎ ቃል መግባት ብቻ አይደለም፡፡ ቤትክርስቲያን ሄደን መጽሐፍ ቅዱስ መትተን እንድንማማል ነው ፍላጎቱ። ልጁ አምሯል፡፡ ሽማግሌ ሳይላክ--- ወላጅ ሳይፈቅድ---ወዳጅ ዘመድ ሳይሰማ---ያለ ሰርግ---ሹልክ ያለች ጋብቻ ይሉሻል እንግዲህ ይህች ናት» አለች ትሩፋት፡፡

«ኧረ እባክሽ!? ‹መጽሐፍ ቅዱስ እንምታና እንማማል› አለ?» አለች እበራሽ ግንባሯን ቋጥር አድርጋ።

«ታድያ ጉዱ ከምን ላይ መሰለሽ? አንቺ የደላሽ ተንደርድረሽ እሊጋ ላይ ወጣሽ እንጂ፡፡ እኔ ደግሞ ከልቤ ያልሆነ የውሸት ቃል አልገባለትም ለዚያውም መጽሐፍ ቅዱስ መትቼ። እኔ ለፍቅር አልተፈጠርኩም! አልደላኝም!» አለች ትሩፋት ምርር ብላ፡፡

«ፍቅርን ፈልገሽ የምታመጭውና ሳትፈልጊ የምታስቀሪው አይደለም። እንዲያም ቢሆን ኖሮ ፍቅሩ ይህን ያህል ፊት እየነሳሽው ለማን ብሎ ይንገላታ ይመስልሻል? ልክ ሲርብ እንደሚበላ---ሲጠማ እንደሚጠጣ ሁሉ ፈጣሪ በውስጣችን የፈጠረው ከቁጥጥራችን ውጭ የሆነ በተፈጥሮ ሕግ የሚገዛ የተፈጥሮ ክስተት ነው» አለች አበራሽ ኮስተር ብላ፡፡

«እንግዲያው ልንገርሽ አይደል አበራሽ-- የተፈጥሮ ሕግ እኔን ዘንግታኛለች ማለት ነው።»

«ተፈጥሮ ሂደቷን አዛንፋ ማንንም ረስታ አታውቅም። በጊዜውና በሰዓቱ ሁሉም ነገር ይፈጸማል፡፡ እስቲ ተፈጥሮን አስተውይ መምሸትና መንጋት፤ ከረምትና በጋ ወቅታቸውን ጠብቀዉ ሲፈራረቁ ተሳስተው ያውቃሉ? እጽዋት ሲበቅሉ፤ ሲያብቡና ለፍሬ ሲበቁ---- እንስሳት መሰሎቻቸዉን ሲተኩ ብታስተውይ ምንም ዓይነት ስህተት አታይባቸውም፡፡ ሁሉም በተሰጣቸው ጊዜና ወቅት ሚዛናቸውን ጠብቀው ያከናውናሉ፡፡ አንቺ ግን ትሩፋት ስሜትሽን በትክክል ማጤንና መገንዘብ ተስኖሻል፤ ወይ ደግሞ በእጉል ባህልና በይሉኝታ

ገመድ ተተብትበሽ እየተሰቃየሽ ስሜትሽን በውስጥሽ አምቀሽ ይዘሽዋል:: የተፈጥሮ ሕግ ሁሉንም እኩል ይገዛል። የሚሽራረፈው ሰው ስራሽ ሕግ ነው ወዳጄ። አንቺ ብቻ የተለየሽ ፍጡር ልትሆኚ አትችይም::»

«ከልቤ ነው አበራሽ:: ፍቅሩ ከልጅነት እስከ እውቀት በእኔ የተንሳ ብዙ እንደ ተገላታ እውቃለሁ:: እንዲህ በመሰቃየቱ አዝንለታለሁ:: አንድም ቀን ግን በፍቅር ዐይን አይቼው አላውቅም:: እንዲሁ ስንገናኝ እልፎ እልፎ የመረበሽ ስሜት ይሰማኝ እንደ ሆነ እንጂ ሌላ የተለየ ነገር አሳድሮብኝ አያውቅም:: አንዳንድ ጊዜ ብቻዬን ሆኜ ሳስበው እሱ እንዲህ ሲንገበገብልኝ---አገር ለአገር በየሄድኩበት ሲንከራተተ--- እኔስ ለእሱ ያለኝ ስሜት ምንድነው? እወደዋለሁ? ወይስ እጠላዋለሁ ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ:: በጣም ብዙ ጊዜ እስባለሁ:: መላልሼ ራሴን እመረምረዋለሁ» ብላ ዝም አለች ትሩፋት

«ታድያ ለነዚህ ጥያቄዎችሽ ምን መልስ አግኝተሽላቸው ታውቂያለሽ?»

«ምንም! ምንም መልስ አግኝቼላቸው አላውቅም:: ለነዚህ ጥያቄዎቼ መልስ አለማግኘቴ እኮ ነው ጭንቀቴ:: የአንድ ወገን ፍቅር ብቻ ለትዳር መሰረት ይሆናል ብዬ አላምንም:: ፍቅሩን ሳስብና የወደፊት እጣ ፈንታችንን ለመገመት ስሞክር የተጣመረ ሕይወት ያለን መስሎ አይሰማኝም። ወደ ፊት በትዳር ዓለም እንኖራለን ብዬ አልገምትም። ሁለታችንን እኩል አፋቅሮ የሚያስተሳስር የፍቅር ገመድ ለእኔ አይታየኝም:: ልቦናዬ ይህን እያወቀ የሐሰት ቃልኪዳን ብገባለት ሃጢያት አይሆንብኝም ታድያ? ምን ሁኚ ትይኛለሽ አበራሽ?» ጭንቅ እያላት ነበር የጠየቀቻት::

«ይህን ለእኔ የነገርሽኝን ሁሉ ለእሱ ነግረሽው ታውቂያለሽ ግን? ለምሳሌ እንደማትወጅው ወይም ምንም ስሜት እንደማይሰጥሽ::»

«እንዴት አድርጌ አበራሽ? አዲስ ዘመን እያለን ልጆች ነበርን። ዝም ብሎ ሲረብሸኝ ይመስለኝ ነበር:: ብዙ የትምህርት ቤት ወንድ ጓደኞቻችን በልጅነት መንፈስ እንዲሁ በአንድ ወቅት እየተከታተሉ ቁም ስቅልሽን ያሳዩሽና ኋላ ላይ ጠብ እርግፍ አድርገው ይተውሻል:: የእሱም ከእነሱ አይለይም እያልኩ እሰብ ነበር። እያደግን ከመጣን በኋላ እንዳልነግረው ደግሞ ነገሩን እያከረረው መጣ:: በተለይ ትምህርቱን አቋርጦ ደብረታቦር ሲመጣ በዋዛ እንደማይተወኝና ከበድ ያለ ነገር እንደ ገጠመኝ ታውቆኛል። እዚህ አስመራ ድረስ ይከተለኛል ብዬ ግን በጭራሽ አስቤው አላውቅም።» ብላ ዐይኖቿን በዘዝ አድርጋ በበሩ ወደ ውጭ ለቀቀቻቸው::

«አሁንማ ጫፍ ላይ ደርሷል። እንኳን አንቺን እኔንም ስጋት ላይ ጥሎኛል። ትሩፌ ብትቀበይውም ባትቀበይውም አንድ ሀቅ ልንገርሽ። ወንድን ልጅ የዘልዓለም ባልሽም--





ባሪያሽም አድርገሽ እግብተሽውም--- እየገዛሽውም ለመኖር ከፈለግሽ የወደድሽውን ሳይሆን የወደደሽን እግቢ። ፍቅር አብሮ በመኖር ይመጣል። በመላመድ ይገኛል።»

«ምን እያልሽ ነው አበራሽ? ገና ለገና እሱ ስለአፈቀረኝ ብቻ ትዳርን ያክል ነገር እንዴት ዝም ብዬ እገባበታለሁ? እውነተኛ ፍቅር ካላስተሳሰረው ትዳር አለማግባቱ ሙቶ ጊዜ ይሻላል:: በትዳር ውስጥ ፍቅርና መስማማት ጠፍቶ መፋታት የሚሉት ጣጣ እንዳይመጣ እፈራለሁ:: ከወለድኩ በኋላ ችግር ተፈጥሮ ልጆቼን ለእንጀራ እናት ወይም ለእንጀራ አባት አሳልፌ ከምሰጥ እድሜ ልኬን ያለትዳር በብቸኝነት መኖርን እመርጣለሁ:: ለእኔ እንደሚገባኝ ትዳር ማለት ሰላምና ጦርነት የሚካሄድባት ትንሿ የአለም ክፍል ናት:: ካገባሁ በኋላ ጦርነት በፍጹም አልፈልግም:: ሰላምና ፍቅርን ብቻ ነው የምመኘው:: የአንድ ወገን ፍቅር ደሞ ጦርነትን አስወግዶ ሰላምን ሲያሰፍን አይቻልም:: የጋራ ፍቅር-የጋራ ስምምነትን፣ መቻቻልንና መተሳሰብን ያመጣል ብዬ አምናለሁ:: ያ ሲሆን ደግሞ ጦርነት ይከሰምና ሰላም ትነግሳለች ብዬ እስባለሁ» አለች ትሩፋት::

«ፍቅሩ የሚሉት ልጅ ሕይወትሽን ካላጠፋትና እድሜ ከኖረሽ የተመኘሽውን ትዳር ታገኚ ይሆናል::»

«ከልብ የሚያፈቅሩትን ሰው ካላገኙ ደግሞ ሳያገቡ መኖር እንደሚቻልም አውቃለሁ::

«ፍቅሩ በዋዛ እንደማይተውሽም ልብሽ ያውቀዋል:: እኔም ብሆን ቃል ገብተሽ መሰንበት ስትችይ በአጉል ድርቅና ሕይወትሽን እንድታጭ አልመከርሽም:: ታናናሾችሽን በእርግጥ የምተወጃቸው ከሆነና ልትረጃቸው ሐሳቡ ካለሽ በሕይወትሽ ላይ እየመጣ ካለው አደጋ ማምለጥ ይኖርብሻል::» ጠንከር አድርጋ አስጠነቀቀቻት አበራሽ። የፍቅሩ ጠናን ሁኔታ እንዲህ በዋዛ የሚተውት ጉዳይ ሆኖ አላገኙትም:: እያደር ሁለቱንም ከፍተኛ ስጋት ላይ እየጣላቸው መጥቷል::

ትሩፋት በረጅሙ ተነፈሰች። ዐይኗን በሩቁ ልካ ወደ ውጭ ተመለከተች። ግንቡ አጥር ላይ የማታ ፀሐይ ወርቃማ ጨረሯን ለቃዋለች:: ግቢዉ በወርቃማው ብርሀን ወገግ ብሏል። በትሩፋት ልብ ላይ ግን ጥቁር ደመናውን እያጠላበት አለፈ::

******

ሰሞኑን ደግሞ ከመቼውም ጊዜ በላይ የፖለቲካው ወሬ ተጧጡፏል። ትሩፋት የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች መኖራቸውን ውስጥ ውስጡን ሲወራ ሰምታለች። የኤርትራ ነፃ አውጭ ደርጅቶች የሚባሉ መኖራቸውን ያወቀችው ደግሞ አስመራ ከመጣች በኋላ ነው:: አንዳንዶቹ ኤርትራውያን በተለይ ወጣቶቹ ለመሀል አገር ሰው ያላቸውን ንቀትና ጥላቻ አስተውላላች። ግርም የሚላት ነገር ቢኖር ራሳቸውን እንደ ስልጡን መቁጠራቸው ነበር። በእነሱ አስተሳሰብ ቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአውሮፓ ስልጣኔ ያልገባው ኋላ ቀር ነው::

እድሜ ጠገብ ኤርትራውያን ግን ኢትዮጵያዊ ወገናቸውን ሁሉ ይወዳሉ:: በኢትዮጵያዊነታቸውም ይኮራሉ::

በቅኝ ግዛት መግዛት እንደ ስልጣኔ የሚቆጠርና የሚያኮራ አለመሆኑን ጠንቅቀው ያውቃሉ:: ሲያቀርቡም ሲያርቁም ከልብ ነው:: አሁን ግን የፖለቲካው ትኩሳት ሁሉንም ነገር በፍጥነት እየቀያየረው ይገኛል:: «የመሀል አገር ሰውና ኤርትራዊ» ተብሎ መከፋፈሉን አልወደደችውም:: አንድ በሆነች ኢትዮጵያ ድንበር ፈጥሮ የጎሪጥ መተያየቱ ትሩፋትን ሰላም ነሳት:: ገና ስታያት የወደደቻትን አስመራን----ለሁልጊዜ መኖሪያዋ እንድትሆን የተመኘቻትን አስመራ ከተማን ፍቅሩም ተጨምሮባት ጠላቻት። ሰሞኑን ደግሞ ጥፍት ብሏል። «የት ሄዶ ይሆን?» አለች:: ቶሎ ተመርቃ ይህን አካባቢ መልቀቅ ተመኘች። ከፖለቲካው ውሽንፍር ለማምለጥና ከፍቅሩ ዛቻና ጭቅጭቅ ለመገላገል::

ትሩፋት የአፄ ኃይለሥላሴ ዘውዳዊው የፊውዳል መንግስት መውደቅ አለበት ብላ ታምናለች፤ ግን ደግሞ የማትመልሳቸው ብዙ ጥያቄዎች አሏት:: መጭው መንግሥት ምን ሊመስል እንደሚችል---አልጋው በማን እንደሚወርስና ማን ባለተራ ያገሪቱ ገዢ ሊሆን እንደሚችል አይገባትም::

«ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት እንደ ቻይናና እንደ ሶቭየት ኅብረት ያለ የሶሻሊስት መንግሥት ነው» የሚለው የዚያ የስምንተኛ ክፍል መምህሯ የፖለቲካ መንፈስ ዛሬም ልቧ ላይ ስሩን እንደተከለ ነው:: «መሬት ላራሹ» በሚለው መርህ ትስማማለች:: የአገሪቱ ሀብት እኩል ለዜጎቿ ሁሉ መሆን እንዳለበት ታምናለች:: አንዱ ገባሪ--ሌላው አስገባሪ---አንዱ ጌታ ሌላው ባርያ ሆነው በጋራ አገራቸው ላይ መኖር የለባቸውም ትላለች:: በነፃነት መናገር--በነፃነት መጻፍ--በአጠቃላይ ማንንም ሳይፈሩ በነፃ እንደ ተወለዱ ሁሉ ሀሳብን በነፃነት መግለጽ ተገቢ መሆኑ ይገባታል:: ከዚህ የዘለለ ስለ ሶሻሊስት መንግሥትና መርህ የምታውቀው ነገር የላትም:: በተቋሙ ውስጥ ያሉ መምህራን ደግሞ ከመደበኛ ትምህርታቸው ውጭ ፖለቲካው ያስጨነቃቸው አይመስሉም:: አገሪቱን በሙሉ ሲያጥለቀልቅ ስለ ደረሰው ትኩስ የለውጥ ወሬ ትንፍሽ አይሉም:: ትሩፋት በጣም ይገርማታል:: የተቋሙ መምህራን የተማማሉ ይመስል የአገርን ጉዳይ አንስተው አለመናገራቸው ያን የሒሳብ መምህሯን በየጊዜው እንድታስታውስ ያደርጋታል:: መደበኛ ትምህርታቸውን ብቻ አስተምረው ከፍሉን ለቀው ይወጣሉ:: አገሪቱ አገራቸው እስከማትመስላቸው ድረስ የምሁራኑ ዝምታ ያስፈራል::

ምንም ይሁን ምን ለትሩፋት አንገብጋቢው ነገር ቶሎ ተመርቃ ለምትፈልገው ቁም ነገር መድረስ ነበር:: ሻብያ ይሁን ጀበሀ የተባለ የኤርትራ ሽፍታ ሆነ አገሪቱን በሙሉ ሊያቀጣጥል የደረሰው የሚንቀለቀለው የለውጥ ሰደድ እሳት ይህንን ዓላማዋን ባይበላባት ምርጫዋ ነው:: ፍቅሩ የሚሉት ልጅም በየሄደችበት እየተሟዘዘ «ፍቅር--ፍቅር» የሚለውን የቀልድ ጨዋታውን ቢያቆምላት ትልቅ ውለታ እንደ ዋለላት በቆጠረችለት ነበር::





******

አለተ ቅዳሜ

«ትሩፋት.... ኧረ ትሩፋት! አንቺን አይደለም ወይ የምጣራው? ኧረ ጡር ፍሪ! አውቀሽ እየሰማሽ እታስለፍልፊኝ! ውሃውን ሰውና ከብት ሳይረጋግጠው በጧት ቀድተሽ ይዘሽ ነይ ብያለሁ አንቺ ልጅ:: በጥጋብሽ አምላኪ!...» የሚለው የእንጀራ እናቷ የዘወትር የምሬት ንግግር ከንቅልፏ አባኖ አያስነሳትም:: እስኪበቃት ትተኛለች። ነቅታም ቢሆን አልጋ ውስጥ ሆኗ እየተገላበጠች መቆየት ያስደስታታል::

አበራሽ እንኳ ከመነሳቷ በፊት ፍቅሩ ማልዶ መጣ። ና ያላሉት እንግዳ:: ቀልጠፍ ብላ አልጋዋ ላይ ወረደች አበራሽ። ትሩፋትም እየከበዳትና እየቀፈፋት ተነስታ አልጋዋን እንደ ነገሩ አለባባሰችው። በዚያች ጠባብ እንዲት ክፍል ውስጥ የሌሊት ልብሳቸውን እንኳ መቀየር አልቻሉም። ፍቅሩ አልፎ ሄዶ እንደ ነገሩ ካለባበሰችው ከትሩፋት አልጋ ላይ ተቀመጠ። ወጣ ብለው ፊታቸውን ተጣጥበው ገቡ:: ቤቷ ሁለት አልጋ ተጥሎባት የተረፈው ቦታ እንደ ልብ መዟዟር አያስችልም:: በዚያችው ጠባብ ቦታ አበራሽ ቁርስ ለመስራት ጉድ ጉድ ማለት ጀመረች። ዳቦ በሻይ ተበላ:: ከቁርስ በኋላ «መጣሁ» ብላ ወጣ አለች አበራሽ:: ስትወጣ ትሩፋትን በዐይኗ ጠቀስ አደረገቻት:: መልእከቱ ገብቷታል ትሩፋት:: ፍቅሩ መዳፏን የሚያነብ ይመስል አቀርቅሮ ውስጥ እጇን ይመለከታል። ትሩፋት የሚለውን ለመስማት እንደ ሚዳቋ ጆሮዋን ቀስራ አበራሽ አልጋ ላይ ተቀምጣለች።

«የባህር ኃይል መሰሪያ ቤት ከዘጠነኛ ከፍል ጀምሮ እጩዎችን እንደሚቀበል ማስታወቂያ ላይ አይቼ ተፈትኜ ነበር።» አለ ለዘብ አድርጎ::

«እውነት!? እንዴት ደስ ይላል ። እንዴት ነበር ፈተናው? ውጤት ለመቼ አሏችሁ?» አከታትላ ጠየቀችው ትሩፋት ለመልሱ ጓጉታ።

«አለፍኩ» አላት እንደ በረዶ በቀዘቀዘ ስሜት ውስጥ ሆኖ::

«እንኳን ደስ አለህ» ብላ ዘላ ልትስመው ምንም አልቀራትም ነበር። እንደበረዶ የቀዘቀዘው ስሜቱ ባለችበት ዝ--ም እንድትል አደረጋት እንጂ።

«የምሄደው ግን በአንድ ነገር እርግጠኛ ስሆን ብቻ ነው» ብሎ ረጃጅም ጣቶቹን አንድ ላይ አቆላልፎ አንቋቋቸው። ትሩፋት የጣቶቹ ርዝመት ይገርማታል። የረጅም ሰው ጣቶች ይመስሏታል።

«በእናትህ ፍቅሩ! እነዚያን ምስኪን ቤተሰቦችህን አስባቸው:: ሌላው ሁሉ ይቅር የብቸኛ እናትህን ልፋትና አንግልት አስብ! በአንተ ላይ የጣሉትን ተስፋና ህልማቸውን መና አታስቀረው:: ልታዝንላቸው ይገባል::»

«ትሩፋት ለእናቴ ከምንም በላይ አዝንላታለሁ:: ልፋቷ--ድካሟ--- እንግልቷ--- ብቸኝነቷ አጥንቴ ድረስ ዘልቆ ይሰማኛል:: ግን ምን ላድርጋት? እኔ ራሴ ፈልጌ የሆንኩትን እንዳልሆንኩ ከኔ በላይ አንቺ ታውቂያለሽ:: ይልቅስ በቀደም ጀምረነው አበራሽ በመምጣቷ ሳንቋጨው ተለያየን። አሁንም ጥላን የጠፋችው በነጻነት እንድንወያይ አስባ ይመስለኛል። ዛሬ እንዱን ወስነን መለያየት ይኖርብናል:: ቃል ከገባሽልኝ ተረጋግቼ መማር እችላለሁ። እስመራና ምጽዋ እፍና እፍንጫ ስለሆኑ የምረጋጋ ይመስለኛል። አባከሽ!---አባከሽ! ትሩፋት ተስፋዬን አታጨልሚው» እንባ ተናንቆት የሹክሹክታ ያህል ነበር ንግግሩ። ያለወትሮዋ ዝም ብላ ትኩር ብላ ተመለከተችው:: ዛሬስ እሱ ሲያያት የፈራ ይመስል ዐይኗን ሸሸ:: ከትንሽ ቆይታ በኋላ እሷ መናገር ጀመረች:: ከአፏ የሚወጣው ድምጽ የሷ ለመሆኑ እየተጠራጠረች:: ጎርነን ያለ ከሩ---ቅ የምትሰማው የሌላ ሰው ድምጽ መሰላት::

«ፍቅሩ የኔን ዓላማና ግብ ልንገርህ። ሲጀምር የመምህራን ኮርስ ለመውሰድ የተገደድኩት ታናናሾቼን ለመርዳትና ለማስተማር በመወሰኔ ነው። በእንጀራ እናት ምላስ እየተጠበሱ ካሉበት ኑሮ ማላቀቅ የምችለው እኔ ብቻ በመሆኔ:: ታውቃለህ በትምህርቴ ሰነፍ የምባል ተማሪ አልነበርኩም::»

«የክፍላችን ተፎካካሪ ተማሪ ነበርሽ» አላት ፈገግ ብሎ::

«ዩኒቨርሲቲ መግባቴን ትቼ ትምህርቴን በአጭር ያስቀረሁት ለእነሱ ስል ነው:: ቶሎ ሥራ መያዝ ይኖርብኛል:: እነሱ ተምረው ጥግ ሲይዙልኝ ያቋረጥኩትን ትምህርት የመቀጠል ህልም አለኝ። ትዳር መስርቼ-- ልጆች ወልጄ-- በልጅ መታሰር አልፈልግም። ለዚህ ነው ከአንተም ስሸሽ የኖርኩት። ፍቅር ለምትለው ነገር ትኩረት ስላልሰጠሁት ለእኔ ምንም ማለት አይደለም።»

«እንደሱ አትበይ ትሩፋት--- እንደሱ አትበይ! የበለጠ ትጎጂኛለሽ:: አንቺ በእኔ ቦታ ሆነሽ ቢሆን ኖሮ ፍቅር እንዴት እንደሚያንበረክክ ይገባሽ ነበር:: ምን ያደርጋል? የተያዝኩት እኔ ሆንኩ:: እንዳፈቅርሽ ፈልጌ እንዳልሆነ ያፈቀርኩሽ ደጋግሜ ነግሬሻለሁ:: እባክሽ የቆሰለች ልቤን እየነካካሽ አታድሚብኝ» አለ በጣም ተከፍቶ::

«የአንተንም ስሜት እረዳለሁ:: ሆኖም ግን የሰው ልጅ ስሜቱን መቆጣጠር ይችላል ብዬ እምናለሁ:: አየህ ፍቅሩ የኔና የአንተ ልዩነት የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው::»





«እኔ እላውቅም ትሩፋ! እሱን እኔ አላውቅም::» አለ ራሱን እየነቀነቀ:: «እንዴት አድርጌ ላስረዳሽ ትሩፋት? ስሜቴን መግታት አልቻልኩም! ተሸንፍኩ! በፍቅር ፈተና ወደቅሁ! ከዜሮ በታች ሆንኩ» ሲል ለተመለከተው ያሳዝን ነበር::

«እኔን ደግሞ የአራት እህቶቼና የአንድ ወንድሜ ነገር ከፍቅር በላይ ያሳስበኛል::»

«ወንድም እህቶችሽን መርዳትና ማስተማር መፈለግሽ የተቀደሰ ሐሳብ ነው:: የማይዘመደኝ መምህር ከፍሌ እንኳ አየረዳ አስተምሮኛል:: ልፋቱን ከንቱ አስቀረሁት እንጂ:: ሲጋትሽ ይኸ ከሆነ እኔና እንቺን በፍቅር አብሮ ከመኖር የሚያግደን አይሆንም::»

«ትዳር መስርቶ—ልጆች ወልዶ እማራለሁ ማለት አስቸጋሪ ነው። ብዙዎቹ ቤቶች እየመሰላቸው እግብተው በተግባር ሲያዩት ግን አልተሳካላቸውም:: አንተም ታውቃለህ:: አምስት ልጆችን ከወለደች በኋላ ያቋረጠችውን ትምህርት ለመቀጠል ከእኛ ጋር ስትማር የነበረችውን እትዬ ዙፋንን መቼም አትረሳትም»

«አንዴ ትምህርት ቤት ስትመጣ-- ሌላ ጊዜ ስትቀር ብዙ ትንገላታ ነበር:: በኋላም ከነጭራሹ እቋርጣ ተወችው:: ከትዳር ጋር--- ቤተሰብ ከማስተዳደር ጋር--- ልጅ ከማሳደግ ጋር አልሳካ አላት፡ ትምህርቷን ባለመቀጠሏ ግን ምንጊዜም እያዘነች ትኖራለች:: ትዳር ለሴት ልጅ የኃላፊነት ቀንበር መሸኘን ማለት ነው። እኔ ከዚህ ጭነት በፊት ቤተሰቦቼን መርዳትና መማር እፈልጋለሁ። እንደ እትዬ ዙፋን እየተፀፀትኩ መኖር አልፈልግም::»

«ትሩፋ ለእኔ ከአንቺ መለየት ማለት ከሞት የከበደ ሞት ነው! እስከ ነፍስ መቃብር መውረድ! ለዘለዓለም በጨለማ ውስጥ መዋጥ! ብቻ 'እልፈልግህም' አትበይኝ እንጂ እስከ ዓለም ፍጻሜ ቢሆን እንኳ እጠብቅሻለሁ። የሚያስፈራኝ ከአንቺ መለየት ነው! የሚያስጨንቀኝ ያለአንቺ በዚች ዓለም ላይ መኖርን ሳስብ ነው! አንችም ስቃዬን ታውቂዋለሽ» ሲል እንባዉ ባይኑ ሞልቶ ነበር። ለመጀመርያ ጊዜ እሷም እንባ ባዘሉ አይኖቿ ትኩር ብላ በሀዘኔታ ተመለከተችው።

«እንዲህ እንደምንነጋገረው ቃል ቀላል እንዳይመስልህ? በአጭር ጊዜ ወስጥ የሚሳካ ላይሆን ይችላል:: እልህ አስጨራሽ ትዕግስት ይጠይቅ ይሆናል::»

«የፈለገውን ዓይነት መስዋዕትነት ይጠይቅ። ከቶም ቢሆን አንቺን ከማጣት የማይሻለኝ ነገር አይኖርም። 'እልፈልግህም' ከምትይኝ አንድ ጊዜ ሳይሆን ሺህ ጊዜ ብትገይኝ ይሻለኛል! እፈራለሁ ትሩፋት!! እፈራለሁ!! እድሜ ልኬን ስሸሸው የኖርኩትን ቃል በፈጠረሽ እንዳታሰሚኝ:: ወይም ቃሉን ከመናገርሽ በፊት በምትፈልጊው-- በሸንኩርት መከተፊያ ቢላዋም ቢሆን ልቤ ላይ ወግተሽ ገላግይኝ:: እኔም እስከ መጨረሻዉ እፎይ ልበል::»

«እንዴት ያለው ኃይለኛው ፍቅር ይዞህ ይሆን? ከልጅነት እስከ አሁን ትንሽ እንኳ የማይበርድ:: አለች ለራሷ:: ችግሩን–ሰቃዩን የተረዳችለት መሰላት:: ከልቧ አዘነችለት::

«ፍቅሩ ዓላማና ግቤን ላታስናክልብኝ። አንተም እስከ ዩኒቨርሲቲ የመማር ዓላማ ከኖረህ በመጨረሻው የአንተ ልሆን ቃል እገባልሃለሁ» ስትለው አላመነም። መጀመሪያ ትርፋት ለመሆኗ የተጠራጠረ ይመስል አንገቱን ወደ እሷ ሰገግ እድርጎ ትኩር ብሎ ተመለከታት። ቀጠለና የሞት ሞቱን ከተቀመጠበት አልጋ ላይ ብድግ ብሎ እግሯ ስር ተንበረከከ:: ዝቅ ብሎ እግሯን ሳመ:: ፊቱን ጉልበቶቿ መሀል ቀበረ:: ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ:: ቀስስስ እያለ ያገኘውን የሰውነት ክፍሏን ሲስም ሁሉ እንባው እንደ ጅረት ይወርድ ነበር። ትሩፋት ለመሆኗ ለማረጋገጥ የፈለገ ይመስል በሚንቀጠቀጥ እጁ የደረሰበትን የሰውነት ክፍሏን ሁሉ ይነካካ–ይደባብስ ጀመር። አንዳች ነገር የሰራ አከላቷን ውርር ሲያደርጋት ተሰማት እሷንም:: ኤሌክትሪክ እንደ ያዛት ሁሉ መላ አካሏን የሚነዝር ስሜት:: መዳበስ ቀርቶ ወንዶች ሰላሰቧት ብቻ እራስ ነበር የሚያደርጋት እቅሟ ከዳት። መግነጢሳዊ ኃይል አሳሰበ ከንፈሮቻቸው ተገናኙ:: ገና ከልጅነት እድሜው ጀምሮ እስከ ወጣትነት ጊዜው ለሰንት ዓመት የተሰቃየለትን ትኩስ ትንፋሿን ማገ። እም—ቅ ጭም—ቅ አድርጎ እየተሰገበገበ የከንፈሯን ወለላ እጣጣመ።

ተፈጥሮ ራሷን እስከበረች:: የማይናወጠውን ሕጓን አስመሰከረች:: በሁለቱ ልብ ውስጥ ተነግሮ የማያልቅ ሀሴት ፈጠረች። እጁ አሁንም አላረፈም፤ ያገኘውን የሰውነት ክፍሏን ሁሉ ይነካካል። ይደባብሳል:: ጸጉሯን.፣ ግንባሯን፣ ጀሮዋን፣ እፍንጫዋን፣ አንገቷን፣ ጡቶቿን... ድንገት «... ብር እምባርሽን ቢሰብር ማን ይደርስልሽ ነበር?» የአበራሽ ንግግር ጆሮዋ ውስጥ አስተጋባ። ከገባችበት ጥልቅ የስሜት ባሕር ውስጥ ወጣች:: ከወደቀባት ሰመመን ነቃች:: ኃይሏን እንደ ምንም አሰባስባ ገፋ አደረገችው። በዓለም ላይ ያሉ ቋንቋዎች ሁሉ ሊገልጹት የማይችሉት እውነተኛ ደስታና እርካታ በደቂቃዎች ውስጥ እበቃ! ከጉም በላይ ከሰማየ ሰማያት በመላእከት አጀብ በፍቅር እክናፍ እቅፍ ውስጥ ሆነው ከተንሳፈፉበት ውብ ዓለም ተለዩ:: በሀሴት ከመጠቁበት ድንቅ ዓለም ወደ እዚህ የመከራ ጉዞ ወደ ማይቋጭበት ዓለም ተመለሱ::

«ነገ እሁድ ነው:: ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሄደን ቃል ኪዳናችንን ብናጸና ምን ይመስልሻል?» ፀጥ—ረጭ ብሎ ሰላም የነገሰበትን ዝምታ ሰበረው ፍቅሩ:: ሁለመናዋን ዐይኑ ውስጥ ለማድረግ እየሞከረ።

«የባሕር ኃይሉ ምዝገባህ መቼ ነው?» አለች:: ትንሽ ዝም ብላ ቆይታ:: እፍራለች:: ትክክል ያልሰራች መሰሏት ፀፀት የሰራ አከላቷን ይዞ ይንጣት ጀምሯል:: ድሮም ቢሆን ሰው ወግቶ ማየት አይሆንላትም:: አሁንማ ጭራሹኑ ዐይኖቿን ማሳረፊያ ቦታ አጣች:: እጠገቧ ማንም ባይኖር ወደደች:: ሰዚች ሰዓት ምኞቷ ከሰተቱን ብቻዋን ሆና እንደ ገና እንድታሰበው ነበር





:: የሆነችውን መሆን እንዳልነበረባት እየተሰማት ተቸገረች:: የሆነው ግን ሆኖ አልፏል:: ፍቅሩ ቶሎ ወጥቶ የሚሄድበትን ሰዓት ናፈቀች:: ብቻዋን– መሆን በእጅጉ አሰፈለጋት::

«እሱማ ሰኞ ነው። ምፅዋ ዋናው መሰሪያ ቤት ድረስ እየቀረባችሁ ተመዝገቡ ነው የተባለው» አላት:: እሱ ደግሞ ደስ ብሎታል:: እጅግ ደስ ብሎታል:: የደስታውን መጠን በቃላት መግለጽ ይከብዳል:: ከሰንት ዓመት ተጋድሎ በኋላ ዛሬ በተቀደሰችዋ ቀን ድል ተቀዳጅቷል::

«ጊዜ የለህም። ሰኞ ለመመዝገብ ነገ የጉዞህ ቀን ነው። ዛሬ ለመጓጓዣ የሚሆን ገንዘብ ከዘመድና ጓደኛ ማፈላለግ ይኖርብሃል። እኔም ያለችኝን እሰጥሃለሁ» አለችው ሰበብ ፈጥሮ እንዳይቀር ሰግታ።

«ትሩፌ» አላት በሰስት እያስተዋላት::«ትሩፌ ከዚህ ሁሉ የልፋት ዓመት በኋላ እግዚአብሔር ለዚህ ሲያደርሰን ልናመሰግነው ይገባል ብዬ ነበር:: ቤተክርስቲያን ተገኝተን ለፍጻሜው እንዲያበቃንና የገባነውን ቃል የሚያስጠብቅ ጽኑ ልቡና እንዲሰጠን መጸሰይ አይገባም ትያለሽ?» በልምምጥ ነበር የጠየቃት።

«አታምነኝም ማለት ነው?»

«ከምንም በላይ እምንሻለሁ። የእግዚአብሔር መልካም ፈቃዱ ሆኖ እርዳታውና ጥበቃው እንዳይለየን ብዬ ነው እንጂ::»

«እሱ ሌላ ጊዜ ያደርሰናል። አሁን ጊዜ የለህም።»

«አንቺ ካልሽ እሺ ይሁን» አላት ቅር እያለውም ቢሆን። የሆነው ሁሉ ቅዠት እንጂ በውኑ አልመሰለውም::

******

እስመራ መምህራን ተቋም ግቢ ውስጥ እጬ መምህራት ሰብሰብ ብለው ቆመዋል። የወቅቱ የፖለቲካ ነፋስ በሁሉም ልብ ውስጥ ይነፍሳል። «ዘውዳዊው ፊውዳላዊ የአፄ ኃይለሥላሴ አገዛዝ መውደቅ አለበት። እንደ ቻይናና እንደ ሶቭየት ህብረት ያለ ሕዝባዊ መንግሥት ነው ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት» እያለ ምንጩ የት እንደሆነ ባይታወቅም ሁሉም ወጣት በየአፉ የሚያወራው ትኩስ የፖለቲካ ወሬ ይኸው ሆኗል። ትሩፋት ቶሎ ተመርቃ ሥራ መያዝ ትፈልጋለች:: በሌላ በኩል ደግሞ ለውጥ እንዲመጣም እጥብቃ ትሻለች።

«ሁሉም ኢትዮጵያዊ የአገሪቱን ዳቦ እኩል የመከፋፈል መብት ሊኖረው ይገባል። አንዱ የተንደላቀቀ ኑሮ የሚኖርባት ሌላዉ የሰቆቃ ሕይወት የሚገፋባት አገር መሆኗ ማብቃት

አለበት። ማንም ሰው በነፃነት እንደ ተወለደ ሁሉ በነፃነት መኖር ይገባዋል። በነፃነት መናገር— በነፃነት መጻፍ--- በነፃነት መሰብሰብ— በነፃነት ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብታችን ማስከበር አለብን። ከፍቶናል ብለን ሰላማዊ ሰልፍ ስንወጣ በብሔራዊ ጦር ቆመጥ መቀጥቀጥ አይኖርብንም። ወላጆቻችሁን አሳምኑ። ሕዝቡ ከጎናችን ሊቆም ይገባል። ተማሪ ብቻ ጮሆ ለውጥ አይመጣም» ይል ነበር የሰምንተኛ ክፍል የሒሳብ መምህሯ።

የዘውድ አገዛዙ ወድቆ ለውጥ ቢመጣ ሁሉም ዜጋ ቢያልፍለት ትመኛለች። በተማረችባቸው ትምህርት ቤቶች በተደረጉ ሰላማዊ ሰልፎች ሁሉ ተካፍላለች። ሰልፉ በወታደር ከተበተነ በኋላ ተመልሶ የነበረ መልኩን ይይዛል። አሁንም ሰላማዊ ሰልፍ ሊጠራ ነው እየተባለ ውስጥ ውስጡን ይወራል። መምህሩ ያልተሳተፈበትንና ያላመነበት ሴክተር ሪቪው የተባለው የትምህርት ፖሊሲ ለአገሪቱ እድገትና ስልጣኔ እያመጣም የሚለው ነጥብ ዋና የመወያያ ርዕሰ ጉዳይ ሆኗል። የገበሬው ልጅ ገበሬ ሆኖ ለመቅረት— የሸማኔው ልጅ ሸማኔ ለመሆን ከሆነ የሚማረው ትምህርት የሚያስገኘው እድገትና ለውጥ ከምኑ ላይ ነው? በዚህ የሴክተር ሪቪው የትምህርት ፖሊሲ የአገሪቱ እጣ ፈንታ ውድቀት እንጂ እድገት አይሆንም የሚለው ሀሳብ በተለይ የመምህራን እምነት ነው። በዚህ የተነሳ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አገር አቀፍ የስራ ማቆም አድማ ለማድረግ ለመምህራን በሙሉ ጥሪ አቅርቧል። ግዙፍ አገራዊ የሥራ ማቆም አድማ ሊመቱ ነው እየተባለ ወሬው ይናፈሳል። የአዲስ አበባ ታክሲ ሾፌሮች ሥራ ካቆሙ ሳምንት አልፏቸዋል። እንደ ለውጥ ሐዋርያ ታይተዋል። ወታደሩም የለውጡን ማዕበል ለመቀላቀል በማኩብኮብ ላይ መሆኑ እየተሰማ ነው። አገሪቱ በሙሉ የፖለቲካ ወረርሽኝ ገብቶባታል።

የለውጥ ነፋስ እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ አገሪቱን በሙሉ አዳረሰ። አንደ መለኮት ይታይ የነበረው ዘውዳዊው የኃይለሥላሴ አልጋ ተነቃነቀ። የእከሊሉ ሀብተወልድ ካቢኔ ፈርሶ የእንዳልካቸው ካቤኔ ተተካ። ሕዝብ ግን «የጉልቻ መቀያየር ወጥ አያጣፍጥም» ብሎ ተነሳ። ትልቁ እሳተ- ጎመራ ፈነዳ----!! የካቲት 1966.....

ድንገት ስሟ ተጠራ ወደ ተጠራችበት አቅጣጫ ዞር አለች ትሩፋት። ረዘም ቀጠን ያለ አንድ ጠይም አጭር መምህር ከተቋሙ አዳራሽ ፊት ለፊት ካለው ደረጃ ላይ ቆሞ ከወዳጅ ዘመድ የመጣ ደብዳቤ ያድላል። ትሩፋት ከኋላ ሰለ ነበረች ፖስታው የደረሳት በቅብብል ነበር። አድራሻው ፍቅሩ ጠና ከምጽዋ ይላል ። ፖስታውን ከፍታ ረጅሙን ደብዳቤ በአይኖቿ ገርምማ ፖስት ካርዱ ላይ የተጻፈውን ብቻ አነበበች።

ፍቅርን አዳምና ሄዋን ጀመሩት፣

ማርካንቲዎና ክሊዮፓትራ ሞከሩት፣





ሮሚዮና ጁሊዬት ሞቱለት፣

እኔና አንቺ ደግሞ ውስጡ እንኑርበት።

«ይህን ጥቅስ ደግሞ ከየት አገኘው?» አለች እንቧባ ስትጨርስ በአድናቆት።

## ሁመራ

ሕዝብ የጀመረውን የለውጥ እንቅስቃሴ አጠናክሮ ቀጠለ። የኃይለሥላሴ ፊውዳላዊው አገዛዝ ግብዓተ መሬቱ ሳይፈጸም ግንባሩን እንደማያጥፍ በተለይ ወጣቱ ክፍል በእለት ከእለት እንቅስቃሴው አስመሰከረ። በኢትዮጵያ ምድር ሁሉ አብዮት እንደ ቋያ እሳት ተንቀለቀለ። ዘውዳዊው ስርወ-መንግሥት ተገረሰሰ። ስልጣን ግን ከሕዝብ እጅ አፈትልካ ከባለ መሳርያ እጅ ገባች። ራሱን ደርግ ብሎ የሰየመው የወታደሩ ስብስብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቸኛው ገዢ ሆነ።

ወታደራዊው መንግሥት ደርግ የአውር ድንብሩን ሲሰራቸው ከተነሳባቸው አንዱ «የአገሪቱ ግማሽ ኃይል የሆኑትን ድርብ ጭቁን ሴቶችን መብት እስከብራለሁ» የሚል ነበር። አብዮቱ «ሀ» ብሎ የሴቶችን እኩልነት ያረጋገጠው ግን ባለፈው ስርዓት «ለሴቶች አይመቹም... አደገኞች ናቸው» በተባሉ ቦታዎች ሁሉ ሴቶችን ለሥራ መመደቡ ነበር። በከፍተኛ ሙቀቷ ምክንያት እንደ በረሀ ተቆጥራ ሴት የማይመደብባት ሁመራ በሴቶች እኩልነት ተደፈረች።

ትሩፋት ከተማዋን የወደደቻት ገና ስታያት ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ አይሮፕላን ላይ የወጣችው ወደ ሁመራ ስትሄድ ሲሆን አውሮፕላን ውስጥ ያጋጠማትን መልከ መልካም ጎልማሳ ለውም በፍጹም የሚረሳ አልነበረም። እግዜር ለውብቱ ሲጨነቅለት የዋለ ይመስላል። አይሮፕላኑ ቀጥታ ሁመራ ከመሄድ ይልቅ መተማ ላይ ነበር ያረፈው። እዚያ የሚወርዱ መንገደኞች በመኖራቸው። ከትሩፋት ጎን ተቀምጦ የነበረው ሰው መተማ ላይ ከቀሩት ሰዎች አንዱ ነበር። መንገደኞች ለጥቂት ጊዜ ከአይሮፕላኑ ወርደው እንዲናፈሱ ተፈቅዶላቸው ወደ ውጭ ወጡ። ውጭ የነበረው ነፋስ ግን እንኳን ሊያዝናና ሙቀቱ እፍን ያደርጋል። ይወርድ የነበረው ነበልባል እንደ መንጠር እሳት ከሩቅ ይጋረፋል።

«የሁመራ ሙቀት ከዚህ ይበልጥ ይሆን?» ስትል አሰበች ትሩፋት ወደ አይሮፕላኑ ከንፍ እየተጠለለች። ተናፍሰው ሲመለሱ ከጎኗ የነበረው ቦታ በሌላ ሰው ተይዟል። በጨረፍታ አይታው

«የወንድ ውበት እንደዚህ ያምራል?» ስትል በውስጧ አድንቃዋለች። የአበሻ ክልስ ይመስላል። መቀመጫዋ በመስኮቱ በኩል ስለነበር ይቅርታ ጠይቃ አልፋ ሄዳ ተቀመጠች። የእንግሊዘኛ መጽሔት ይዞ ያገላብጣል። ትሩፋት ፊቷን ወደ መስኮቱ መልሳ ንድፍ ጥጥ መስሎ ከሰሯ የተንጣለለውን የዳመና ቁልል ማድነቅ ጀመረች። ሁሉን ነገር ረስታ ተፈጥሮ ውስጥ ሰመጠች።

«ሕሙ እንገትሽን እንዳያምሽ አንዳንዴም ወደ ፊትም ወደ ጎንም ማዘዋወር ሳይሻልሽ አይቀርም» ሲላት ዞር ብላ ተመለከተችው «አቤት! ጥርስና ከናፍር! ከማንም ላይ አልተፈጠረ» አደነቀች አሁንም ለራሷ።





«እሺ-- አመሰግናለሁ» ብላ ተመልሳ ወደ መስኮቱ ዞር ልትል ነበር።

«ስምሽ ማን ይባላል? እኔ ወርቃፈራሁ እባላለሁ» ሲላት መንተፍረቷን ስሟን ነገረችው።

«ሁመራ ነው የምትኖሪው?» ሲል ደግሞ ጠየቃት።

«በመምህርነት ሙያ ተመድቤ ገና ልኖርባት ነው» አለች።

«አስተማሪ ልትሆኚ!?» በአድናቆት ነበር የጠየቃት፤ መልሷን ሳይጠብቅ «እውነት ለመናገር ገና ተማሪ መሰልሽኝ ነበር» አላት አስተውሎ እየተመለከታት።

«አሁን እንኳ ሠራተኛ ልሆን ነው መሰለኝ» አለች። አንገቷን ደፋ አድርጋ።

«ገና ልጅ ነሽ ምን በወጣሽና ነው እዚህ በረሀ አገር የምትቃጠይው?»

«ለተወሰነ ጊዜ ነው። ብዙ አልኖርም» አለች። ከአንገቷ ቀና ብላ ዐይኗን ፊት ለፊቷ ካለው ወንበር መደገፊያ ላይ ሰከታ።

«ለቀናትስ ቢሆን ለምን ሀሩር ይብላሽ?» አላት ከልቡ እያዘነላት።

«ሌላው ሰውስ እየኖረበት አይደል» አለች። እኔ ከማን እበልጣለሁ በሚል ስሜት።

«ምን አልባት አማራጭ አጥቶ ይሆናላ! እርግጠኛ ነኝ ሌላ ምርጫ ያለው ሰው እዚህ በረሀ ውስጥ ለመቃጠል አይኖርም።»

«እኔም እኮ በእጣ ስለ ደረሰኝ ነው የመጣሁት።»

«አንቺን የመሰለች ገና ለጋ ልጅ እዚህ በረሀ ውስጥ መኖር የለባትም። ለመሆኑ ወባ እንዳለስ ሰምተሻል?» ሲል ጠየቃት።

«ብዙ ጊዜ የምታጠቃው ለሰሊጥና ለጥጥ ለቀማ እርሻ ላይ የሚውሉትን የቀን ሰራተኞችን እንደ ሆነ ሰዎች ሲያወሩ ሰምቻለሁ።»

«ሁመራ በአጠቃላይ በረሀና ለወባ ትንኝ መራባት ተስማሚ የሆነ የአየር ንብረት ያለው አገር ነው። ምን በወጣሽ በልጅነትሽ እዚህ ችግር ውስጥ ትወድቂያለሽ?»

«አሁንማ እንዴ መጥቻለሁ።»

«የምታምኚኝ ከሆነ አዲስ አበባ እኔ በተሻለ ደመወዝ ላስቀጥርሽ እችላለሁ:: ማረፊያ ዘመድ ከሌለሽ ደግሞ ለጊዜው እኔ ቤት ታርፊያለሽ:: ጥሩ ቤት አለኝ:: አትቸገሪም::ሥራ ይዘሽ ስትጠናከሪ ተከራይተሽ የራስሽ ቤት ይኖርሻል» አላት ወርቃፈራሁ:: ስሜቷን ለማንበብ እየሞከረ:: ትሩፋት ቶሎ መልስ አልሰጠችውም:: ዝም ብላ ቆዩች:: መልሷን እንደሚጠብቅ ስታውቅ

«አስቲ አስብበታለሁ» አለች::

«ላግባባሽ አልሞከርም:: ሌላ የተለየ ፍላጎት ኑሮኝ አይደለም:: ልጅነትሽ አሳዝኖኝ ነው ልረዳሽ ያሰብኩት:: የፊሊፕስ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ ነኝ:: ለጊዜው የማርፍበትን ሆቴል አላወቅሁትም:: ምናልባት ከሰነበትኩ ትምህርት ቤትሽ ድረስ መጥቼ ውሳኔሽን አጠይቅሻለሁ:: ለማንኛዉም ይሄ የአዲስ አበባ አድራሻዬ ነው» ብሉ ካርድ ሰጣት:: በአክብሮት ተቀበለችው::

ትሩፋት የተመደበችባት ማርያም ጽዮን ትምህርት ቤትን ልክ እንደ ሁመራ ከተማ ሁሉ ገና ስታያት ነበር የወደደቻት:: ግቢው ለቀቅ ያለ ነው:: በተዘረጋው አሸዋማ ሜዳ ላይ የተሰራው ትምህርት ቤት ጥራቱን የጠበቀ ነው:: በተለይ የተከዜ ወንዝ ከጎኑ መሆኑ ደግሞ ከሁሉም በላይ አስደስቷታል:: የሁመራ በረሀማነት በቆላማዋ አዲስ ዘመን ላደገችው ትሩፋት ያን ያክል ከባድ አልነበረም::

አውሮፕላን ላይ የተዋወቀችው ወርቃፈራሁ ቃሉን ጠብቆ ሐሳቧን ሊጠይቃት ማርያም ጽዮን ትምህርት ቤት ድረስ መጥቶ ውሳኔዋን ጠይቋታል:: እሷ ግን በእጇ የጨበጠችውን ሥራ ትታ መሄዱ አስፈራት:: አመለግና አዲስ አበባ መሄድ እንደ ማትፈልግ ስትነግረው ያልጠበቀው መልስ ነበር:: አዲስ አበባ ብትገባ የአገሪቱ ዋና ከተማ እንደ መሆኗ መጠን የወደፊት ሕይወቷን ለማሻሻል ጥሩ አጋጣሚ እንደሚሆንላት ሊያስረዳት ሞክሯል:: እየሰራች በማታው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ከፍተኛ ትምህርቷን መቀጠል እንደምትችል እየነገረ ሊያሳምናት ጥሯል:: ልጅነቷ አሳዝኖት ከልቡ ሊረዳት አስቦ ነበር:: ሀሳቧን ብትቀይር ብሎ ተመላልሶ ጠይቋታል:: እሷ ግን በጉዞ አጋጣሚ ድንገት አይሮፕላን ውስጥ የተዋወቀችውን ሰው አምና መሄዱ ከበዳት:: ውሳኔዋን እንደማትለውጥ ሲያውቅ እያዘነ ነበር ተሰናብቷት የሄደው:: ወደ አዲስ አበባ ሊመለስ በመጨረሻው ቀን አንድ ስጦታ ሊያደርግላት ወሰነ:: በዚህ በረሀ አገር ባይሆን እንኳ ሙዚቃ እያዳመጠች እንድትዝናና በማሰብ አንድ ፊሊፕስ ቴፕሪከርደር ከተለያዩ የሙዚቃ ካሴቶች ጋር አበረከተላት:: የእጅ ባትሪዎችና ባትሪ ድንጋይ እንኳ አልቀረውም:: እሷ ግን ለብዙ ጊዜ ከማታውቀው ሰው ላይ ይህን ያህል ስጦታ ላለመቀበል ታግላ ነበር:: በጣም አዝኖ ሳለየችው ነበር የተቸገረችለት:: ከዚያ በኋላ ከወርቃፈራሁ ጋር ዳግም አልተገናኙም:: በዚሁ ተለያይተው ቀሩ::





ትሩፋትን ገና ከጅምሩ በዚህ ገጠመኝ የተቀበለቻት ሁመራ ብዙ ነገር አሳይታታለች:: የፀሐይ ነበልባል እንደ እሳት ላንቃ ምላስ አውጥቶ ሲንበለበል ያየችው ሁመራ ነው። ቤት ሳይዘጋ አፉን እንደ ከፈተ የሚያድርበት---ሌባ የማይፈራበት አገር መኖሩን ያወቀችው ሁመራ ነው። እባብ በየቦታው ሲፍለከለክ አይታ ከምታስተምራቸው ሕፃናት ይልቅ እሷ ፈርታ ደንብራ መሳቂያ መሳለቂያ የሆነችበት አገር ቢኖር ሁመራ ነው። በሰም መሬቷ ላይ ትራክተር ሲያጓራ ያየችው ሁመራ በመሄዷ ነበር:: ከዚያ በፊት መሬት በበሬ ጉልበት ሲታረስ እንጂ በትራክተር መኪና ግምሰምሱ ሲወጣ አላየችም:: ሰሊጥና ጥጥ በጀንያ ተሞልቶ--ተሞልቶ በጠራ አውላላ ሜዳ ላይ ሰማይ ጥግ ደረስ ተቆልሎ ያስጠባቂ እንዲሁ ሲውል ሲያድር ካለ ሁመራ የትም አገር አላየችም:: ጥጥ፣ ሰሊጥና ማሽላ ሞልቶ በተትረፈረፈባት አገር ምን ሌባ ተገኝቶ ይፈራል? ይነስ ይብዛ እንጂ አንዱ ያለው ሌላውም አለው:: በትራክተር መኪና ታርሶ ምርት እንደ አፈር ቢዛቅበትም--- በግራር እሾህ ሞጀጅ ተደርጎም የዕለት ጉርስ አይነፍግም ለሙ የሁመራ መሬት:: እንደ ዋዛ ተሰርቶ በልቶ ማደር ከተቻለ ሰርቆ ማን ኃጢያት ይገባል?

ከማርያም ጽዮን ትምህርት ቤት ግቢ ቆሞ ወደ ሰሜናዊ ምስራቅ ቀና ሲሉ ከተከዜ ወንዝ ማዶውን የኡምንሀጀር ከተማ እንደ ፈንድሻ ፍንድቅድቅ ብላ ትታያለች። ትሩፋት በርቀት እያየች የምታደንቃት ይህች ከተማ በኤርትራ ሽምቅ ተዋጊዎችና በደርግ ጦር ሰራዊት መካከል በተካሄደ የወንድማማቾች ፍልሚያ የዶግ አመድ ስትሆን የተመለከተችው ሁመራ በመገኘቷ ነበር። የአንዲት አገር ልጆች በጦርነት ቋያ ተርመጥምጠው ስላማዊውን ኗሪ ሲያርመጠምጡ ሀዘን ልቧን እንደ ቋጥኝ ከብዶት ማርያም ጽዮን ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ቆማ በዐይኗ በብረቱ ተመልክታለች።

ትሩፋት የምትኖረው እዚያው ከምታስተምርበት ማርያም ጽዮን ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ነው:: ከሁመራ ከተማ ሰሜናዊ ምስራቅ የተከዜን ወንዝ ተንተርሳ የተመሰረተችው ማርያም ጽዮን ትምህርት ቤት ከአስመራ በመጡ የካቶሊክ ቄሶች ትተዳደራለች:: ከጣሊያን የካቶሊክ ቤተክርስቲያናት የኢኮኖሚ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ቄሶቹ ነግረዋታል። መንግሥት በውጭ እርዳታ እየተደገፉ የትምህርት አገልግሎት ለሕብረተሰቡ የሚሰጡ ትምህርት ቤቶችን ለማበረታታት በሚል ነው ትሩፋት ማርያም ጽዮን ትምህርት ቤት የተመደበችው። የመሀል አገር ሰው እሷ ብቻ ብትሆንም በፍትር ትኖራለች:: ቋንቋ አላገዳትም:: እንደውም አስመራ የጀመረችውን የትግርኛ ቋቋዋን ለማሻሻል እንደ ጥሩ አጋጣሚ ነበር የወሰደችው። ተፈጥሮዋም ለዚህ ቀና ነው:: ዛሬም ቢሆን እድሜ--ቋንቋ--ዘርና ሀይማኖት ሰው ከመውደድና ከመግባባት አግደዋት አያውቁም:: ከትንሽ ትንሽ--ከትልቁ ትልቅ መሆን ትችልበታለች። ዘር-- ቋንቋ-- ሃይማኖት--ቀለም ብሎ ነገር ሳያግዳት ሰውን በሰውነቱ ብቻ መቅረብና መውደድ የሚችል ልብ አላት::

«ምን እሱ ብቻ! ከዘመኗ ወዲህና ከዘመኗ ወዲያ ካሉ ሰዎች ጋር ያላት መቀራረብና መግባባትስ ቢሆን ከሁሉም ጋር ተስማምቶና ተግባብቶ ለመስራትና ለመኖር ልዩ ስጦታ

ያላት ሰው ናት፡፡ የእሷ ልዩነት ጎልቶ የሚታዬው በአቋም ላይ ሲሆን ነው፡፡ በአንድ ነገር ላይ አምና ድርቅ ካለች መመለሻ የላትም» ይሏታል የሥራ ባልደረቦቿና ጓደኞቿ፡፡

ማርያም ጽዮን ትምህርት ቤት ብቸኛ አማርኛ ተናጋሪ ብትሆንም ችግር አልፈጠረባትም፡፡ ከእሷ ጋር ስድስት ሴቶች ሆነው በሚኖሩበት ቤት ውስጥ ከሁሉም ጋር ተግባብታ ትኖርበታለች፡፡ ከስራ ባልደረቦቿም ጋር ያለችግር ትሰራለች፡፡ ቄሶቹ አለቆቿ ሳይቀሩ በፍቅር ነው የሚያዩዋት፡፡ አንድም ቀን ባይተዋርነት ተሰምቷት አያውቅም፡፡

የማርያም ጽዮን ትምህርት ቤት አስተዳዳሪን «አባቴ» ብለው ይጠሯቸዋል፡፡ በካቶሊክ የቅስና ማእረጋቸው አንጂ አድሜያቸው አርባዎቹ ውስጥ ቢሆን ነው፡፡ ትሩፋት ሁሌ የሚገርማት እ'ኒህ ቄስ የወጣላቸው አጫሽና ጠጭ መሆናቸው ነበር፡፡

«ወይ ጉድ! ቄስ ደግሞ ሲጋራ ያጨሳል? መጠጥ እንዲህ አብዝቶ ይጠጣል? የካቶሊክ ቄሶች መሰልጠናቸው ይሆን?» ትላለች፡፡ እየሰመደቻቸው ስትሄድ ተወቻው እንጂ በመጀመሪያው ሰሞንማ እንደ ሐይማኖት አባት አታያቸውም ነበር፡፡ ጠንካራ ሰራተኛ መሆናቸውን ግን ታደንቃለች፡፡ ከትምህርት ቤቱ ተጨማሪ ከሁመራ ከተማ በግምት ሃያ አምስት ኪሎ ሜትር ሰፊ የእርሻ ቦታ አላቸው፡፡ ትሩፋት በሁመራ ኑሮዋ በጣም ያስደስታት የነበረው ወደ ዚህ የእርሻ ቦታ መሄድ ነበር፡፡ ቄሱ ጥሩ ሾፌር ናቸው፡፡ በአስራ አምስት ቀን አንዴ ግቢው ውስጥ የሚኖሩትን ሰራተኞች ጭነው ይወስዷቸዋል፡፡ በዚያ የእርሻ ቦታ ውስጥ የሌለ የፍራፍሬ ዓይነት የለም፡፡ ሰቁጥር የሚያታክቱ ፍየሎችና በቀን ከሁለት ሊትር በላይ የሚታለቡ ላሞችም አሏቸው፡፡ በዘመናዊ የንብ እነባብ ዘዴ የሚገኘው ማር ቁርስ ላይ ከዳቦ ጋር ቀርቦ አይታለች፡፡ ከእርሻ ቦታቸው ሌሎች ቄሶች መኖራቸውንም ልብ ብላለች፡፡ በደንብ የተቀናጀና የተደራጀ ሥራ እንደሚያካሂዱ ገብቷታል፡፡ ይህን የምድር ላይ ገነት የመሰለ ቦታ መያዛቸውና ማልማታቸው ገርሟታል፡፡ የቄሶቹን የሥራ ባህል አድንቃለች፡፡ እንኳን ይህን ሁሉ ጥቅም ሲሰጥ ዝም ብሎ አካባቢውን ሲመለከቱ ውሉው ቢያድሩ አይሰለችም፡፡ ተፈጥሮ አንዳለች ድንግልናዋን ጠብቃ ትገኝበታለች፡፡ ትሩፋት እዚህ የእርሻ ቦታ በመጣች ቁጥር ውስጡ ሰጥማ መቅረት ያሰኛታል፡፡ ሌላው የሚገርማት ነገር ቢኖር ደግሞ ከቄሶቹ ግቢ ሁልጊዜ ወዘ ልውጥ ሰው አለመታጣቱ ነበር፡፡ የቄሶቹ ቤት የአብርሀምና የሳራን ቤት ይመስል አንዱ ሲመጣ ሌላው ሲሄድ መመልከት የተለመደ ነው፡፡

«ትሩፋት ይቅርታ አድርጊልኝና ባይመለከተኝም--ለምንድን ነው በዚህ እድሜሽ አስተማሪ የሆንሽው ግን? ሳይሽ ልጅ ትመስይኛለሽ። ኮሌጅ መግባት ስትችይ ማለቴ ነው» አላት ሲጋራውን ሳብ ቡልቅ እያደረገ። ሰልካካ ብስል ቀይ ፊቱን ጺም ጨርሶ ሲሸፍነው ምንም ያህል አልቀረውም። የሚታየው ወጣ ያለው ግንባሩ፣ ቀጥ ያለዉ አፍንጫውና የጉንጮቹ ሎሚዎች ብቻ ናቸው። ጠበብ ያለው አፉና ስስ ከንፈሮቹም የጺም ዳዋ ውጧቸዋል።





ይህን ሰው ትሩፋት እንደ ሌሎቹ የቄሶቹ እንግዳ አድርጋ ትመለከተዋለች። ባይሆን እሱ አቀላጥፎ አማርኛ ይናገራል። ከእሷ ጋር ሲሆንማ ተስቶት በትግርኛ አያወራም።

«ለቤተሰቦቼ የመጀመርያ ልጅ ነኝ። ከእኔ በታች አምስት አሉ። ወላጆቻችን ከተለያዩ ቆይተዋል። በእንጀራ እናት ማደግ ደግሞ ምን ያህል እንደሚያንገፈግፍ የሚያውቀው የደረሰበት ብቻ ነው። ለታናናሾቼ ሊደርስላቸው የሚችል ከእኔ በቀር ሌላ ማንም የለም፡፡ ለዚህ ነው ትምህርቴን ከአስረኛ ከፍል አቋርጬ መምህር የሆንኩት» አለችው፡፡ እንደ ተመኘችው ለታናናሾቿ ደርሳላቸዋለች። ጎንደር ከከተማው አቶባርኮ በሚባለው ሰፈር ውስጥ አንዲት ትንሽ ከፍል ተከራይታ ሁሉንም እያስተማረቻቸው ነው። ድልነሳና ራሔል ስምንተኛና ዘጠነኛ ከፍል ደርሰዋል፡፡ ሌሎችም ትንሽ ቢረፍድባቸውም ትምህርት ቤት ገብተዋል፡፡ ዋናው ነገር ትምህርት መጀመራቸው ነው፡፡ የእናቷን አደራ በመወጣቷ ውስጧን ደስታ ውረር ያደርጋታል።

«ቤተሰብ ለመርዳት ያለሽን ፍላጎት አደንቃለሁ፡፡ ኮሌጅ ከጨረሽ በኋላ አይደርስም ነበር ግን? እድሜ ሳይገፋ በፊት መማር አይሻልም ነበር? በተለይ ለሴት ልጅ ሁሉም ነገር በጧት ቢሆን ነበር የሚበጀው፡፡ ያለዚያ ፈተናው ብዙ ነው» አላት፡፡ አምደጺዎን ይባላል ይህ የቄሶቹ እንግዳ፡፡ ከልቡ ነበር የሚያጫውታት፡፡ ትሩፋት ኮሌጅ በመግቢያ እድሜዋ ላይ መምህር መሆኗን አጢኖ፡፡

«ለአጭር ጊዜ ነው እዚህ የምቆየው፡፡ እነሱ ሲደርሱልኝ ኮሌጅ ገብቶ የመማር እቅድ አለኝ» አለች ትሩፋት፡፡

«በእርግጥ ከልብሽ መማር ትፈልጊያለሽ?»

«ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመኝ በስተቀር የወደፊት እቅዴ አንግዲህ እንደ ነገርኩህ ነው፡፡ ታናናሾቼ ራሳቸውን ከቻሉልኝ በኋላ ያቋረጥኩትን ትምህርት የመቀጠል ፍላጎት አለኝ፡፡ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም የገባሁት ከአስረኛ ከፍል ነው፡፡ የአስራ አንደኛንና የአስራ ሁለተኛ ከፍል ትምህርቶችን ከአሁኑ በግሌ ለማጥናት ዝግጅት ላይ ነኝ፡፡» ምኞቷን ሳትደብቅ አጫወተችው።

ሁመራ መቼም አቤት ውስጥ መቀመጥ አይቻልም። ሙቀቱ እንደ በረዶ አቅልጦ ይጨርሳል። ዳስ ውስጥ መቀመጥ ይሻላል። የሁመራ ኗሪዎች «ሸርጋንያ» ይሉታል ዳሱን። የሻይ ጀበና ከምድጃ አይወርድም። ቶሎ ቶሎ ሻይ እየጠጡ ላብ ካልወጣ ወበቁ ትንፋሽ ያሳጥራል። አብዛኛው የሁመራ ሰው ፊሪጅ ከነመፈጠሩም በማያውቅበት በዚያ ዘመን ራሱ ዘዴ ፈጥሮ ዝሁል ውሃ ይጠጣል፡፡ መሬቱ ተቆፍሮ እንስራው ይቀበራል፡፡ አንገቱ ድረስ በአሸዋ ይታቀፋል፡፡ ከፍሪጅ የወጣ የመሰለ ውሃ ለማግኘት አሸዋውን ቶሎ ቶሎ ውሃ ማጠጣት ነው፡፡ በዚህ መልክ መሬት ውስጥ ከተቀበረው እንስራ ውስጥ ያለው ቀዝቃዛ

ውሃ የሁመራ ሙቀት ያየው አይመስልም:: በየትኛውም የሁመራ ኗሪ ቤት ውስጥ በዚህ ዘዴ የቀዘቀዘ ውሃ ይታጣል ማለት ዘበት ነው::

ትሩፋት ከአምደጽዮን ጋር ሸርጋንያው ውስጥ ናት:: የምትጫወተው ረጅም ጊዜ እንደምታውቀው ሆና ነው። ግቢው ውስጥ ሁለቱ ብቻ ቢሆኑም ለምን እንደ ሆነ ባታውቅም አልፈራችውም:: እንግዲያው ወንዶች ከቀረቧቸው የመጨረሻ ማሳረጊያቸው የፍቅር ጥያቄ ነው የሚል ፍራቻ ነበራት። የምትቀርባቸው በጥርጣሬ ነው። ይህንን እንግዳ ሰው ግን ለምን እንዳመነችው ለራሷም አልገባት። ለዚያውም ፍቅሩ መቼ ተረሳት።

«ዩኒቨርሲቲ ለመግባት እርግጠኛ ከሆንሽ መቼ እንደምሄድ ባላውቀውም እንግሊዘኛ፣ ሒሳብ፣ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪና ባይዎሎጂ እኔ አስጠናሻለሁ:: ወደ እዚህ ስመጣ ብዙ መጽሐፎችን ይዤ ነው የመጣሁ» አላት:: በመገረም ትክ ብላ ስታየው አስተያየትዋ ገብቶታል።

«የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአራት ኪሎ የሦስተኛ ዓመት የሳይንስ ተማሪ ነበርኩ» አላት::

«ምስኪን የገና ተመራቂ የሚሉት ነገር አጋጥሞት ተብሮ ይሆን?» ስትል አሰበች:: ሦስተኛ ዓመት ደርሶ አንድ ዓመት ሲቀረው በመበረሩ በውስጧ አዘነችለት ። እሱ ጨዋታውን ቀጠለ::

«ይኸውልሽ እናት አገሬ ስትጥቅ ትግል ጠርታኝ ትምህርቴን አቋርጬ መምጣቴ ነው:: ኤርትራን ከኢትዮጵያ የቅኝ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት ከሚታገሉት ሸምቅ ተዋጊዎች ጋር ለመቀላቀል ነው የመጣሁት» አለ ኮስተር ብሎ:: ትንፋሹን በረጅሙ ለቀቀውና አንገቱን ደፍቶ ጸጥ አለ:: ይኸ ከፊቷ ያለው ሰው ሊሸፍትና ኢትዮጵያን ሊወጋ---ኤርትራን ሊያስገነጥል ሊሄድ መሆኑን እየነገራት ነው:: በእሷ አቅም ምን ልትፈይድ እንደምትችል ማንሰላሰል ያዘች:: አምደጽዮን ገለጻውን ቀጠለ::

«አየሽ ትሩፋት እዚህ ከቄሶቹ ጋር ቆይታ የማደርገው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው:: አንዳንድ አጉል ልማድ ቢኖርብኝ ከትግል ሜዳ እንዳያዘናጋኝ እሱን ለማረቅ» አላት::

«ምን ዓይነት ልማድ?» ጠየቀች ትሩፋት:: «ሲጋራውን ከሆነ እንኳን ልትተወው ባናት ባንቱ እያቦነንከው ነው:: ከዚህ የባሰ ምን መጥፎ አመልና ሱስ ይኖራል?» አማችው በሆዷ::

«ለምሳሌ የሴት አመል ቢኖርብኝ-- ከትግል ሜዳ እንዳያዘናጋኝ ለጥቂት ጊዜ እዚህ ሆኜ ራሴን እፈትናለሁ:: ችግሩን እንዴት መቋቋም እንዳለብኝ እለማመዳለሁ» አለ አምደጺዎን::





«ተፈጥሮ ነው። እንዴት መቋቋም ትችላለህ? ልክ ሲርብ እንደ መብላት ሲጠማ እንደ መጠጣት» የአበራሽ የአንድ ቀን ንግግሯ ትዝ ብሏት ለአምደጺዎን ደገመችለት። የተናገረችው ግን በሙሉ ልብ አልነበረም:: ውስጥ ውስጧን ሌላ ሐሳብ እየተፈታተናት ነበር:: ለፖሊስ ጠቁሞ የማስያዝ ሐሳብ::

«ትክክል ነው:: ተፈጥሮ ነው:: ግን ሰው ስለሆን ደግሞ ለተፈጥሮ ልጓም ልናበጅለት እንችላለን:: ወይም መፍትሔ እንፈልግለታለን:: ከእንስሳ መለየታችን ለዚህ አይደል! ከአቅም በላይ ሲሆን ደግሞ ተንፈስ የሚባልበት የተለያየ ዘዴ አይጠፋም:: በተለይ ለወንድ ልጅ ቀላል ነው:: ሴሲት ተኝቼ የሴት ነገር ባሰብኩ ቁጥር በሕልሜ አቅፌያቸው የማድራቸውን ሴቶች ውብተ አትጠይቂኝ» አለና ፈገግ ብሎ «ከሊዮፓትራን ያስንቃሉ ብልሽ ታምኛኛለሽ? ታድያ ከሕልሜ ስነቃ ደሰሰስ በሚል ርካታ ተጥለቅልቄ ራሴን አገኘዋለሁ:: ከዘዴዎቹ አንዱ ይሄ መሆኑ ነው» አላት ፈገግ ብሎ። ትሩፋት ዘገነናት። እሱም ዓላማውም አስጠሏት::

የአፄ ኃይለሥላሴ ፊውዳላዊው የዘውድ አገዛዝ እንዲለወጥ የአቅሟን ታግላለች። የመሬት ላራሹን መፈክር እንግባ ተሰልፋለች። የኤርትራ ታጋዮች ጥያቄ ከኢትዮጵያ ጭቁን ሰፊ ሕዝብ ጥያቄ የሚለይበት ምክንያት ፈጽሞ አይገባትም። መቼም ጊዜ ገብቷት አያውቅም።

እምደጽዮን ቀና ሰው ነበር:: በሁመራ ቆይታው ምንም ሳይደብቅ የልቡን አጫውቷታል:: ምኞቱን ነግሯታል:: ለከፍተኛ ትምህርት እንድትበቃ የቻለውን ሁሉ ጥሯል:: ትምህርቱን አቋርጦ የመጣበትን ጉዳይ ግን ፈጽሞ የማትቀበለው ነው:: የጊዜ አጋጣሚ ወንድማማች የሆነውን የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ ለእኩይ ዓላማና ስልጣን ሲሉ ከሚያጫርሱ ጥቁር ታሪክ ካላቸው ሰዎች ጋር ወስዶ የዶለው ይመስላታል:: ለዚህ ሳይሆን አይቀርም የግል ሰዕብናውና ዓላማው አብረው አልሄድላት እያሉ የምትጨነቀው:: ብዙ ጊዜ ለፖሊስ ጠቁማ ለማስያዝ ስታስብ እነዚህ ሁለት ነገሮች እየተጋጩባት ውሳኔ ለመስጠት ተቸግራ ብዙ ቆይታለች:: በእጇ ላይ ምንም ማስረጃ አለመኖሩ ደግሞ ሌላው ፈታኝ ጥያቄዋ ነበር:: ፖሊስ ቃሏን ብቻ አምኖ እንደማይቀበላት እርግጠኛ ነበረች:: ቄሶቹ በሁመራ ከተማ ያንን የካቶሊክ ልብሰ-ተክህኖ አዘርፍፈው ሲታዩ ያላቸው ከብርና እምኔታ ከፍ ያለ መሆኑን አይታለች:: ወቅቱ ደግሞ አስቸጋሪ ነበር:: ማንም ማንንም የማያምንበት። ከጥላ የሚሸሽበት-- እርጌው የሞተበት። አዲሱ አብዮት የተወለደበት--- የአንዱ መጨረሻ የሌላው መጀመርያ.....

******

ጥርት ባለው የሁመራ ሰማይ ላይ የምሽት ጨረቃ የብር እንጎቻ መስላ ጉብ ብላለች። አዲስ እንደ ተኮላ ጥሬ ብር ትፈልቃለች። በተንጣለለው የሁመራ አሸዋማ ሜዳ ላይ አልፎ አልፎ ጉች ጉች ብለው የበቀሉት የግራር ዛፎች--- ፍንትው ያለው የጨረቃዋ ብርሃን አርፎባቸው-

--ጥቁር የኮይሳ አፈር ቁልል መሰለው ይታያሉ። ዐይንን ሳያራግቡ ትክ ብሎ ለተመለከታቸው ደግሞ የሚንቀሳቀሱ ጥቁር ግዙፍ አውሬ ነገር መሰለው ፍርሀት ያጭራሉ:: ማዶውን የኡምንሀጀር ከተማ በኤሌክትሪክ ብርሃን የነደደች መሰላ ትታያለች። ትሩፋት አንሶላ ብቻ ጣል ካለበት የገመድ አልጋዋ ላይ ጋደም ብላለች። ፍራሽ መቼም አይታሰብም:: ጥጡ ወይ ስፖንጁ ሞቆ የበረሀ አሸዋ ላይ የተኙ እስኪመስል ድረስ ሙቀቱ ላፍ ያደርጋል:: የሁመራ ሰው ሁሉ የሚተኛው አንሶላ ጣል ካለበት የገመድ አልጋ ላይ ነው:: ትሩፋት አንቅልፍ አልወሰዳት ብሎ ዐይኗን በተከፈተው በር አድማስ ጥግ ድረስ ሰቃዋለች። የምሽቱን የተፈጥሮ ውበት እያደነቀች ዘና ብላለች። ሳታስበው የአምደጽዮን ነገር መጥቶ በሐሳቧ ሰንቅር አለ:: ኢትዮጵያን ለመውጋት እየሸፈተ መሆኑን እየነገራት እንዴት ዝም ብላ እንዲሄድ ታደርጋለች? እርግጥ ለእሷ በጣም ጥሩ ሰው ነው:: ግን ኢትዮጵጵያን የማፈራረስ ተልዕኮ ይዞ ሊሸፍት የተነሳ የአገሯና የወገኗ ጠላት ነው:: አንድ ነገር ማድረግ ይኖርባታል:: ነገ ከተማ መውጣት አለባት:: ቢያንስ ለአንድ ለምታውቀው ሰው ሁኔታውን ማማከር ይኖርባታል:: በሐሳቧ ሁመራ ከተማ የምታውቀው ፖሊስ የሆነ ሰው ብትፈልግ አጣች:: መረጃ ሳትይዝ ለፖሊስ ሄዳ ብትነግር ቄሶቹ ባላቸው ተቀባይነት ምክንያት አመኔታን የምታገኝ አልመሰላትም:: ሌላ ማድረግ ባትችል ግን ከሌላኛው የመንግሥት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር ልትመከርበት እምነው የሚቀበሏት ከሆነም ፖሊስ ጣቢያ ሄዳ ለማመለከት አሰበች::

«አምደጺዮን ከወራሪዋ ጣልያን በምኑ ይለያል? ሁለቱም አገር የማፈራረስ ተልኮ ነው የያዙት» አለች ራሷን ለራሷ «አዎ! ነገ በጧት መሄድና አንድ ነገር ማድረግ ይኖርብኛል:: ብቻ ይንጋ!» ብላ ፎከረች:: በሌላኛው ጎኗ ተገላብጣ ተኛች:: አንቅልፍ ግን አልወሰድሽ አላት:: አንደ ገና ተገላበጠችና ያን ውብ የምሽት ተፈጥሮ ማድነቅ ጀመረች:: ሐሳብ ወጥሮ ይዞት የነበረው አካሏ ዘና መንፈሷ ላላ ማለት ሲጀምር ድንገት አንዲት ላንድሮቨር መኪና ስትበር መጥታ ግቢው ውስጥ ቆመች። ከተደመመችበት የተፈጥሮ ትዕይንት በፍጥነት ወጣችና ዐይኗን መኪናዋ ላይ ጣለች::

በምሽቱ የጨረቃዋ ብርሃን ሲታዩ ጸጉራቸው ጥቁር ድስት የተደፋባቸው የሚመስሉ ሦስት ሰዎች ተከታትለው ከመኪናዋ ላይ ወረዱ። ምን ዐይነት ቀለም እንደ ሆነ መለየት ቢያዳግትም ሱሪያቸው ቁምጣ ነው:: ገንባሌ አድርገዋል። ጫማ ይኑራቸው አይኑራቸው ጥርት ብሎ አሊታያም። መሳሪያ ይዘዋል:: በቀጥታ ወደ ቄሶቹ ቤት አመሩ። ትሩፋት ዐይኗን ሳታራግብ የምሽቱን ድራማ በመደነቅና በመገረም መመልከት ያዘች። ከጥቂት ሰዓታት ቆይታ በኋላ ሦስት ሆነው የገቡት ሰዎች አራት ሆነው ተመለሱ። አራተኛው በቁመቱና ባረማመዱ አምደጺዎን ለመሆኑ አልተጠራጠረችም:: መኪናዋ ውስጥ አንደ ገቡ ፊቷን አዙራ በመጣችበት ፍጥነት ሸመጠጠች። በፍጹም ልታምነው ያልቻለችው ነገር ነበር:: «ወይኔ ተቀደምኩ!» አለች ትሩፋት:: በመዘግየቷ ተናደደች:: የአገሯ ጉዳት ታያት:: ጸጸት ልቧን ቧጠጠው::





ትሩፋት ከዚያች ቀን በኋላ እነዚያ የማርያም ጽዩን ትምህርት ቤት ቄሶች--- ቄስ እንዳልሆኑ ተገነዘበች። እስከ አግር ጥፍራቸው የለበሱት የካቶሊክ ለብሰ--ተክህኖ የፖለቲካ ማስፈጸሚያ ሽፋን እንደ ሆነ ተረዳች። በአጠቃላይ ልብሱም ልብሰ---ቄሶቹም ቄሰ-- ቤተክርስቲያኗም ቤተክርስቲያን---ትምህርት ቤቷም ትምህርት ቤት እንዳልሆኑ አወቀች።

«ለካ ያ ሁሉ ቲያትር የፖለቲካ ማስፈጸሚያ ሽፋን ኖሯል:: ያውም አገርን የመቆራረስና የማፈራረስ ድብቅ ሴራ የሚካሄድበት ሽፋን:: እርሻውም ትምህርት ቤቷም ለካ ኤርትራን ለማስገንጠል ለሚካሄደው ደባ የገንዘብ ምንጭ ኑረዋል» አለች በቁጭት:: ይህንን አገር የማፈራረስ ድብቅ ተንኮልና ሴራ አያየች ሁመራ ማርያም ጽዮን ትምህርት ቤት መቆየት አስጠላት:: ከዚያ አካባቢ መጥፋት ፈለገች። ሳትውል ሳታድር የዝውውር ፎርም ሞልታ ተዝቆ የማያልቀው የሁለት ዓመት የሁመራ ትዝታዋ ይዛ አንበሳሜ ገባች::